ሊያከናውን የሚችልባቸውን መንገዶች ዘርዝሩ:: ለ) አብዛኞቹ የቤተ ክርስቲያን ኮሚቴዎች የሚሠሩበትን መንገድ በዚህ መጽሐፍ ለኮሚቴዎች አሠራር ከተሰጠው መመሪያ ጋር አነጻጽር:: ከእነዚህ መምሪያዎች/አሳቦች የምትስማማባቸውና የማትስማማባቸው የትኞቹ ናቸው? ለምን? ሐ) እነዚህ መመሪያዎች ኮሚቴዎች በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ የሚሠሩበትን መንገድ እንዴት ሊለውጡ ይችላሉ?

3. ሀ) ነገሮችን ማዘግየት የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ውጤታማነት የሚቀንሰው እንዴት ነው? ለ) የቤተ ክርስቲያን መሪ ዎችን ጊዜ የሚያባክኑ ሌሎች ነገሮች ምን ምንድን ናቸው?

4. ሀ) ጥሩ የገንዘብ አያያዝ ሥርዓት አለመኖር በቤተ ክርስቲያን መሪ ላይ ችግር ሲፈጥር የተመለከትከው እንዴት ነው? ለ) ዕዝራ መጀመሪያና በኋላ ኢየሩሳሌም ከደረሰ በኋላ ገንዘቡን በሰ ዎች ፊት የቆጠረው ለምን ይመስልሃል? ይህ መሪዎች ለቤተ ክርስቲያኖቻቸው ጥሩ የገንዘብ አያያዝ ሥርዓት መዘርጋታቸው አስፈላጊ መሆኑን የሚያሳየው እንዴት ነው?

5. ሀ) ስለ ገንዘብ አጠቃቀም ከተገለጹት አጠቃላይ መርሖዎች የምትስማማባቸው የትኞቹ ናቸው? የማትስማማባቸውስ? ለምን? ለ) እነዚህ መርሖዎች አብዛኞቹ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ስለ ቤተ ክርስቲያን የገንዘብ አያያዝ ከሚያስቡት የሚለዩት እንዴት ነው? ሐ) ቤተ ክርስቲያናችሁ ለአባሎቿ ስለ ገንዘብ፣ ስለ ዓላማውና ፀልግስና ስለ መስጠት የምታስተምረውን አሳብ ከልስ:: ቤተ ክርስቲያናችሁ እግዚአብሔር ስለ ገንዘብ ያለውን አመለካከት በተገቢው መንገድ እንድታስተምር ምን ቢደረግ መልካም ነው ትላለህ?



# ትምህርት አሥራ ስምንት

## አንደኛ ቀን

ምናልባትም በቤተ ክርስቲያን መሪዎችና ምእመናን መካከል ያለውን መተማመን የሚያከስመው ትልቁ ነገር የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የቤተ ክርስቲያንን ገንዘብ የሚይዙበት መንገድ ሳይሆን አይቀርም:: ስለሆነም፣ ምእመናን ለእግዚአብሔር ሥራ እንድንጠቀምበት የሚሰጡትን ገንዘብ በፍጹም ታማኝነት ለአገልግሎት ማዋሉ ወሳኝ ነው:: በገንዘብ አጠቃቀማችን ዙሪያ ምእመናን እንዲያውቁ የማንፈልገው ነገር ካለ፣ ይህ የእግዚአብሔ ርን ገንዘብ በታማኝነት ያለመጠቀማችንን የሚያሳይ ነው:: አንድ ቀን የተደበቀው ነገር ይታወቅና መተማመን ይጠፋል:: አንድ ጊዜ ይህ መተማመን ከጠፋ ደግሞ፣ ለመሪዎች ይህንኑ መተማመን መልሶ ማግኘቱ ከባድ ነው:: ታማኞች ወይም ግልጾች ባለመሆናችን ምክንያት የእግዚአብሔር መንግሥት የተፈለገውን ያህል እንዳታድግ የሰይጣን መሣሪያ በመሆን እናገለግላለን:: ይህም የሚሆነው በታማኝነት ጉድለቱ ሳቢያ ምእመናን ገንዘብ መስጠታቸውን ስለሚያቆሙ ነው::

> 1ኛ ጥያቄ:- ሀ) መሪዎች በተሳሳተ የገንዘብ አያያዛቸው የሰይጣን መሣሪያ ዎች ሲሆኑ የተመለከትከው እንዴት ነው? ለ) መሪዎች የቤተ ክርስቲያንን ገንዘብ በምሥጢራዊ መንገድ የሚይዙት ለምንድን ነው? ይህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አመራር አለመሆኑን አብራራ::

**(ማስታወሻ:- በዚህ መጽሐፍ ውስጥ መሠረታዊ የሂሳብ አያያዝ ዘዴዎችን ብቻ እናብራራለን:: ቤተ ክርስቲያኒቱ ትልቅ በምትሆንበት ጊዜ፣ በሂሳብ አያያዝ የሠለጠነ ሰው ብቃት ያለው የፋይናንስ ሥርዓት መመሥረት ይኖርበታል:: ከዚህ በታች የቀረቡት አሳቦች እንግዲህ ቤተ ክርስቲያናችሁ ብቃት ያለው የፋይናንስ ሥርዓት እስክታዘጋጅ ድረስ ሊያገለግሉ የሚችሉ አሳቦች የሚገኙበት ነው:: የገንዘብ አስተ ዳደሩ የአንተ ሥራ ባይሆን እንኳን፣ ቤተ ክርስቲያን መልካም**

**የገንዘብ አጠቃቀም እንድትመሠርት ማበረታታት ትችላለህ። ቀለል ያለ የገንዘብ አያያዝ ሥርዓት ከተመሠረተ በኋላ፣ ሌሎች እምብዛም ሥልጠና የሌላቸው ሰዎች በቀላሉ ይህን ሥርዓት በመከተል በጥሩ ሁኔታ የቤተ ክርስቲያኒቱን ገንዘብ ሊያንቀሳቅሱ ይችላሉ።)**

## የቤተ ክርስቲያንን ገንዘብ ለማስተዳደር የሚያግዙ አንዳንድ አሳቦች

1. የቤተ ክርስቲያንን ገንዘብ በባንክ ቤት ወይም በሁለት ቁልፎች በተቆለፈ ሳጥን ውስጥ ማስቀመጥ ያስፈልጋል።

አንድ ሰው ውድ ንብረት ካለው፣ ማንም እንዳይሰርቅበት በማሰብ በጥሩ ሁኔታ ያስቀምጠዋል። ለግል ንብረታችን ከፍተኛ ጥንቃቄ የምናደርግ ከሆነ፣ ለእግዚአብሔር ንብረት የበለጠ ጥንቃቄ ማድረግ የለብንም? ብዙ ምእመናን ለእግዚአብሔር ሥራ ገንዘብ የሚሰጡት ከጉሮሮአቸው ነጥቀው ነው። ይህ ገንዘብ በአግባቡ ሳይጠበቅ ቀርቶ ሲባክን፣ እነዚህ ሰዎች ተስፋ ይቆርጣሉ። በመሆኑም፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የእግዚአብሔርን ገንዘብ ሌቦች ከማይደርሱበት ቦታ ማስቀመጥና አላግባብ ከሚባክንበት መንገድ መጠበቅ ይኖርባቸዋል።

የሚቻል ከሆነ፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አብዛኛውን የቤተ ክርስቲያን ገንዘብ ባንክ ቤት ውስጥ ማስቀመጥ ይኖርባቸዋል። መባው እንደ ተሰበሰበ፣ ገንዘቡ ተቆጥሮ ባንክ ቤት መግባት አለበት። በኢትዮጵያ ውስጥ አሁን ብዙ ባንክ ቤቶች እየተከፈቱ ስለሆነ፣ ቤተ ክርስቲያኖች ገንዘባቸውን ለማስቀመጥ ይህ ጥሩ አጋጣሚ ነው። በእነዚህ ባንክ ቤቶች የሚቀመጠው ገንዘብ በሁለት ሰዎች ስም ፊርማ ገንዘብ የሚወጣበትን ዘዴ የሚከተል መሆን አለበት። (ማስታወሻ፡- የባንክ ቤት የሂሳብ ደብተሩ በግለሰብ ስም ሳይሆን፣ በቤተ ክርስቲያኒቱ ስም ቢከፈት መልካም ነው። ይህ በሚሆንበት ጊዜ፣ ደብተሩን ለመክፈት ከቤተ ክርስቲያን ልዩ ደብዳቤ መጻፍ ሊያስፈልግ ይችላል።) ብዙውን ጊዜ ገንዘቡን የማውጣት ሥልጣን የሚኖራቸው የቤተ ክርስቲያኒቱ የሽማግሌዎች ሰብሳቢና ገንዘብ ያዡ ናቸው። ይሁን እንጂ፣ በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ የተወሰነ ሥልጣን ያለው ሰው ካልፈረም ከሚል ግትርነት ይልቅ፣ ጥሩ የሚሆነው ገንዘብ ማውጣት በሚያስፈልግበት ሰዓት ሊገኝ የሚችል ታማኝ ሰው እንዲፈርም ማድረጉ ነው። ገንዘቡን በፍጥነት ከባንክ ቤት የሚያወጣ ሰው ክሌለ፣ የቤተ ክርስቲያኒቱ ሥራ መስተጓጎሉ የማይቀር ነው። በመሆኑም፣ ገንዘብ ፈርመው እንዲያወጡ የሚመደቡ ሰዎች ብዙውን ጊዜ ወደ ሌላ አካባቢ የማይሄዱና በቅርብ ሊገኙ የሚችሉ መሆን አለባቸው። እነዚህ ሰዎች ከቤተ ክርስቲያን አቅራቢያ የሚኖሩ መሆን አለባቸው።

በቅርብ አካባቢ ባንክ ቤት ክሌለ፣ ቤተ ክርስቲያኒቱ ጠንካራ የእንጨት ወይም የብረት ሳጥን ማሠራት አለባት። ይህ ሳጥን ሁለት ቁልፎች ሊኖሩት ይገባል። አንደኛው ቁልፍ ሽማግሌዎች ገንዘቡን እንዲጠብቁ ኃላፊነት ለሰጧቸው ሁለት ሰዎች መሰጠት አለበት። (የማይገኝ ካልሆነ በቀር፣ ከሁለቱ ሰዎች አንዱ ገንዘብ ያዥ መሆን አለበት።) በሳጥኑ ላይ አነስተኛ ቀዳዳ ማበጀቱ ጥሩ ነው። ይህ የቤተ ክርስቲያን መሪው ሁለተኛውን ቁልፍ የያዘውን ግለሰብ መጥራት ሳያስፈልገው በየሳምንቱ የሚሰበሰበውን ገንዘብ በቀዳዳው እንዲያስገባ ያስችለዋል። ገንዘብ ለቤተ ክርስቲያን ሥራ በሚያስፈልግበት ጊዜ ቁልፉን የያዙት ሁለቱ ሰዎች አብረው ሳጥኑን በመክፈት ገንዘብ ማውጣት አለባቸው።

2. የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች አገልግሎቶች ወይም መሪዎች ከሰብሳቢው ወይም ከቦርዱ ፈቃድ ሳይጠይቁ ገንዘቡን ማውጣት ስለሚችሉባቸው መንገዶች መመሪያ ማዘጋጀት አለባቸው።

ቤተ ክርስቲያን ገንዘቡ «እንዳይጠፋ» ወይም አላግባብ «እንዳይባክን» በማድረግና ሥራዎቿን በአግባቡ በማከናወን መካከል ያለውን ሁኔታ ሚዛናዊ ማድረግ አለባት። ገንዘቡ እንዳይባክን ካለን ፍላጎት የተነሣ እያንዳንዱ ገንዘብ በሽማግሌዎች ሰብሳቢ እየጸደቀ እንዲወጣ ብናደርግ፣ መጋቢው የእግዚአብሔርን ሥራ ለማከናወን ችግር ይገጥመዋል። ገንዘቡን ለመጠበቅ ያለን ፍላጎት የእግዚአብሔርን ሥራ ሊገድበው ይችላል። ብዙውን ጊዜ ገንዘብ

በሚፈለግበት ጊዜ የቤተ ክርስቲያን መሪው ስለማይገኝ፣ ሥራው ይዘገያል ወይም ሳይከናወን ይቀራል:: (ለምሳሌ፣ አንድ ትልቅ እንግዳ ይመጣና ምግብ ለመግዛት የሚያስችል ገንዘብ ለማውጣት ይቸግራል:: አንድ ሰው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ይታመምና ለመርዳት የሚያስችል ገንዘብ ማግኘት ሳይቻል ይቀራል::) ወይም የቤተ ክርስቲያን ሠራተኞች ደመወዝ ጥየቃ ወደ ገንዘብ ያዥ ይመጣሉ:: ነገር ግን የቤተ ክርስቲያን መሪው ሩቅ አገር ስለ ሄደ፣ ሳይከፈላቸው ይቀራል::

በሌላ በኩል፣ የቤተ ክርስቲያን ሠራተኞች ያለ ገደብ ገንዘብን እንዲጠቀሙ አንፈልግም:: ይህ የእግዚአብሔር ገንዘብ አላግባብ እንዲባክን ሊያደርግ ይችላል:: ለአገልጋዮችም አላስፈላጊ ፈተናን ያስከትላል:: የቤተ ክርስቲያን ገንዘብ በአግባቡ ቁጥጥር ሊደረግለት ባለመቻሉ የተከሰቱ ብዙ አሳዛኝ ነገሮች አሉ:: ሰዎችን በጣም ማመን እነዚሁ ሰዎች በኃጢአት እንዲወድቁና በቤተ ክርስቲያን መሪዎችና በምእመናን መካከል የነበረው መተማመን እንዲጠፋ ያደረገባቸው ሁኔታዎች አሉ:: ይህ ደግሞ ምእመናን ለመስጠት እንዲያመነቱ ያደርጋቸዋል::

2ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ገንዘብን ከሚገባው በላይ መቆጣጠር የእግዚአብሔርን ሥራ ሊያደናቅፍ የሚችልባቸውን መንገዶች ግለጽ :: ለ) ገንዘብን በሚገባ አለመቆጣጠር የገንዘብ ብክነትና ግለሰቦች ገንዘብ ለመስረቅ እንዲፈተኑ ሊያደርግ የሚችልባቸውን መንገዶች ዘርዝር::

ገንዘቡ እንዳይባክንና የቤተ ክርስቲያኒቱ አገልግሎት በአግባቡ እንዲካሄድ ለማድረግ ሽማግሌዎች ሊያደርጉ የሚችሏቸው ነገሮች አሉ::

ሀ. ሥራ የሚበዛባቸው የቤተ ክርስቲያን መሪዎች መደበኛ ወጭዎችን ለአገልጋዮች በውክልና ቢሰጡ መልካም ነው:: ቤተ ክርስቲያን በየወሩ የሚከፈሉ መደበኛ ወጭዎች አሏት:: (ለምሳሌ፣ የስልክ፣ የመብራት፣ የደመወዝ፣ ወዘተ. . . ወጭዎች::) እነዚህ ወጭዎች አዲስ ስላልሆኑ፣ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌው እነዚህን ክፍያዎች ስለ መፈጸም ውሳኔ መስጠት አያስፈልገውም:: ለምሳሌ፣ የቤተ ክርስቲያኒቱ ሠራተኞች በየወሩ ደመወዝ የሚከፈላቸው



ከሆነ፣ ሥራ የሚበዛበት የቤተ ክርስቲያን መሪ ሊከፈላቸው እንደሚገባ ወይም እንደማይገባ ለመወሰን በስፍራው መገኘቱ አስፈላጊ አይደለም:: ያልተለመዱ ወጭዎች በሚያጋጥሙበት ጊዜ ግን የቤተ ክርስቲያን መሪው ማጽደቅ አለበት::

3ኛ ጥያቄ፡- የቤተ ክርስቲያን መሪውን ውሳኔ ሳይጠብቁ ሊከፈሉ የሚችሉትን የአገልግሎቶች ወይም የቤተ ክርስቲያን «መደበኛ» ወጭዎች ዘርዝር::

ለ. የቤተ ክርስቲያን ቦርዶች ግለሰብ አገልጋዮችና መሪዎች ምን ያህል ገንዘብ ቦርዱ ማጽደቅ ሳያስፈልገው ሊያስተዳድሩ እንደሚችሉ መወሰን አለባቸው:: ገንዘብን የመቆጣጠሩ ደረጃ የሚወሰነው ቦርዱ ለግለሰቡ በሰጠው የሥልጣንና የኃላፊነት ደረጃ ሊሆን ይገባል:: የግለሰቡ የአመራር ደረጃ ከፍተኛ ከሆነ፣ በርከት ያለ ገንዘብ የማስተዳደር ሥልጣን ሊሰጠው ይገባል:: ወንጌላዊው የቤተ ክርስቲያን መሪው ሳያጸድቅ ለአገልግሎቱ የተወሰነ ገንዘብ የማዋል ሥልጣን ሊሰጠው ይችላል:: የቤተ ክርስቲያን መሪው ደግሞ ከዚያ የበለጠ ገንዘብ የማስተዳደር ሥልጣን ሊሰጠው ይችላል:: የአውራጃ ኃላፊው የተወሰነ የገንዘብ ኃላፊነት ሊኖረውና የቀጣና ኃላፊው ደግሞ ሌላ የገንዘብ ኃላፊነት ሊኖረው ይችላል:: (ለምሳሌ፣ የቤተ ክርስቲያን ቦርዶች እንደሚከተለው የገንዘብ ገደብ ሊያደርጉ ይችላሉ:: የቤተ ክርስቲያን ጸሐፊ በወር 20 ብር ያህል ከቤተ ክርስቲያን ጋር ለተያያዙ ሥራዎች ልታውል ትችላለች:: እነዚህም ስኳር፣ ሻይ ቅጠል፣ ወዘተ. . . መግዛት ሊሆኑ ይችላሉ:: ወንጌላዊው አገልግሎቱን ለማካሄድ የሚያስችል በወር 50 ብር ያህል ሊሰጠው ይችላል:: የቤተ ክርስቲያን መሪው ደግሞ ለደመወዝ፣ ለልዩ ልዩ ክፍያዎች፣ ለድሆች ምጽዋት ለመስጠት እስከ 500 ብር ሊሰጠው ይችላል:: እንዲህ ዓይነት መመሪያ መኖሩ አገልጋዮች ገንዘብን ለመጠቀም የተወሰነ ነጻነት እንዲኖራቸውና በውክልና የተሰጣቸውን አገልግሎት እንዲያስተዳድሩ ያስችላቸዋል:: እንዲሁም ደግሞ መቼ ከእርሱ በላይ ካለው አካል ድጋፍ መጠየቅ እንዳለበትም እንዲገነዘብ ያስችለዋል::

ለምሳሌ፣ ለቤተ ክርስቲያን የአገልግሎት ዘርፍ የጸደቀ በጀት ካለ፣ ልምድ ያላቸው አገልጋዮች በሥራቸው ክልል እስከ ተወሰነ የገንዘብ መጠን ድረስ ውሳኔ መስጠት መቻል አለባቸው:: የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አገልጋዩ ያቀረበላቸውን የሥራ ዕቅዶችና በጀት ካጸደቁ ወዲያ፣ አገልጋዩ ለሁለተኛ ጊዜ ወደ መሪዎቹ መመለስ ሳያስፈልገው ለሥራው ማካሄጃ ገንዘብ ሊሰጠው ይገባል:: ለአገልጋዮች ሥራውን እንዲያካሂዱ እየተጠየቁ ለሥራው የሚያስፈልገውን ገንዘብ እንዳያንቀሳቅሱ መደረግ ተስፋ የሚያስቆርጥ ነገር ነው:: በየወሩ ደመወዝ እንዲከፍል የተጠየቀ ሰው ይህንኑ ለማድረግ በየወሩ ወደ ለብላቢው መሄድ ካለበት፣ ይህ እድካሚ ይሆንበታል:: ወይም ደግሞ ለኮንፍረንስ ምግብ እንዲያዘጋጁ ቢጠየቁና ለምግቡ የሚያስፈልጉትን ነገሮች ለመግዛት በተደጋጋሚ ወደ መሪው ዘንድ መመላለሱ ጥሩ ስሜት አይፈጥርላቸውም:: አስተዋይ የቤተ ክርስቲያን መሪ ለሰዎች ሥራን በውክልና በሚሰጥበት ጊዜ ለሥራው የሚያስፈልገውን ገንዘብም እንዲቆጣጠሩ ያደርጋል::

ግለሰቡ የተሰጠውን ሥራ ከማከናወኑ በፊት ወደ እርሱ እንዲመጣ በማድረግ «ቁጥጥር» ከማካሄድ ይልቅ፣ አስተዋይ የቤተ ክርስቲያን መሪ ግለሰቡ ገንዘቡን ለመያዝ የሚታመንበትን መንገድ ይፈጥራል:: ከዚያ በኋላ ገንዘቡ አገልግሎት ላይ ስለ ዋለበት መንገድ ሪፖርት (ደረሰኞችን ጨምሮ) እንዲሰጠው ያደርጋል:: ገንዘቡ አላግባብ የባከነበት መንገድ ካለ፣ የቤተ ክርስቲያን መሪው አጋጣሚውን ተጠቅሞ ግለሰቡ በተሻለ መንገድ ገንዘቡን የሚገለገልበትን መንገድ ሊያሳየው ይችላል::

(ማስታወሻ:- የቤተ ክርስቲያን ቦርዶች መሪዎች ገንዘብ የሚያንቀሳቅሱበትን የተወሰነ ሥልጣን ቢሰጡም፣ መሪዎቹ ገንዘቡን የተገለገሉበትን መንገድ የሚያሳዩበት የተጠያቂነት መንገድ መኖሩ ወሳኝ ነው:: ጸሐፊዋ ለወሰደችው 20 ብር ሪፖርት ማቅረብ አለባት:: ወንጌላዊው 50ውን ብር እንዴት እንደ ተገለገለ ያስረዳል:: የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌው ለ500 ብሩ ሪፖርት ያቀርባል:: 50ም ሆነ 500 ብር ማባከኑ ትክክል አይደለም:: ስለሆነም፣ የቤተ



ክርስቲያንን ገንዘብ የሚይዙ ሰዎች የእግዚአብሔርን ገንዘብ በአስተዋይነት ለመጠቀማቸው ተጠያቂነት ሊኖራቸው ይገባል::)

> 4ኛ ጥያቄ:- ለቤተ ክርስቲያናችሁ ለገንዘብ አጠቃቀም ከሁሉም የሚሻለው ምን ዓይነት የሥልጣን ተዋረድ ይመስልሃል? ለ) የሽማግሌዎች ስብሳቢ በስንት ብር ላይ ሥልጣን ሊኖረው ይገባል? ሐ) ስለ ገንዘብ አጠቃቀም የሽማግሌዎች ቦርድ ማጽደቅ ያለበት መቼ ነው?

ሐ. የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በቤተ ክርስቲያን ቢሮ ውስጥ ከወንጌላዊው ወይም ከመጋቢው ቁጥጥር ሥር አነስተኛ የሂሳብ መዝገብ ሊያኖሩ ይችላሉ:: የዚህ አነስተኛ ገንዘብ (በእንግሊዝኛ ብዙውን ጊዜ «ፔቲ ካሽ» የሚባለው) መጠን የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ በሥሩ ለሚካሄዱት ሥራዎች በሚያወጣው ገንዘብ መጠን ሊወሰን ይገባል:: ይህንን አነስተኛ ገንዘብ በአገልጋዩና በቤተ ክርስቲያን መሪዎች መካከል ችግር በማይፈጥር መልኩ በማስተዋል ለመጠቀም የሚከተሉትን ነገሮች ማድረጉ ጠቃሚ ይሆናል:-

1) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በሽማግሌዎች የተወሰነ አነስተኛ ገንዘብ የሚንቀሳቀስበት የሂሳብ ደብተር ማዘጋጀት አለባቸው:: የገንዘብ አያያዙ ለችግር እንዳይጋለጥ መጠኑ ከፍተኛ መሆን የለበትም:: ነገር ግን በእያንዳንዱ ወር ውስጥ የሚከናወኑትን ቀጣይነት ያላቸው አገልግሎቶች ለመሸፈን የሚበቃ መሆን አለበት:: የገንዘቡ መጠን የሚወሰነው በቤተ ክርስቲያኒቱ አቅምና ለቤተ ክርስቲያኒቱ መደበኛ አገልግሎት በሚውለው የገንዘብ መጠን ይሆናል:: እዚህ ላይ ለማለት የተፈለገው አገልጋዮች ሥራ የሚበዛባቸው የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ገንዘብ እስኪሰጧቸው ሳይጠብቁ፣ ሽማግሌዎች ያጸደቁላቸውን መደበኛ አገልግሎቶች ማካሄድ እንዲችሉ ነው::

2) አነስተኛውን ሂሳብ የሚቆጣጠረው ግለሰብ በየቀኑ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚገኝ መሆን አለበት:: ግለሰቡ በቅርብ የማይገኝ ከሆነ፣ የቤተ ክርስቲያኒቱ አገልግሎት መደናቀፉ የማይቀር ነው:: በሌላ በኩል፣ ገንዘቡ በብዙ ሰዎች እጅ የሚገባ ከሆነ፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ለጠፋው ገንዘብ አንዱን

ግለሰብ ተጠያቂ ሊያደርጉት አይችሉም፡፡ ለዚህም ምክንያቱ ጥፋቱ የማን እንደ ሆነ የማይታወቅ በመሆኑ ነው፡፡

3) የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ገንዘቡን እንዴት ሊጠቀሙ እንደሚችሉ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ግልጽ መመሪያዎችን ማዘጋጀት አለባቸው፡፡ ለምሳሌ፣ አገልጋዮቹ አስክሪብቶ፣ ወረቀት፣ ለእንግዶች ሻይ፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉትን ድሆች ለመርዳት፣ ለስልክ፣ ለውኃና ለመብራት፣ ወዘተ. . . የተወሰነ ገንዘብ እንዲጠቀሙ ማድረግ ይቻላል፡፡ ነገር ግን ከፍተኛ ገንዘብ የሚጠይቁ ወጪዎች ሲያጋጥሙ፣ ሽማግሌዎች ማጽደቅ እንዳለባቸው መግለጹ አስፈላጊ ይሆናል፡፡ ወርሐዊ ደመወዝ መክፈል የሽማግሌዎች ሰብሳቢ ኃላፊነት ሊሆን ይችላል፡፡ ግልጽ መመሪያ መኖሩ አገልጋዩ ገንዘቡን ለምን አገልግሎት ሊያውል እንደሚችል በሚገባ ያሳየዋል፡፡ እንዲሁም ደግሞ መሪው አገልጋዩ ገንዘቡን በትክክል አልተጠቀመም የሚል ክርክር ውስጥ ሳይገቡ የገንዘቡን አወጣጥ በአግባቡ እንዲከታተል ያስችለዋል፡፡ ግልጽ መመሪያዎች ብዙውን ጊዜ በመሪዎችና አገልጋዮች መካከል ሰላምና አንድነት እንዲፈጠር ያደርጋሉ፡፡ በተቃራኒው ግልጽ መመሪያዎች አለመኖራቸው አለመግባባቶችን ያስከትላል፡፡ ምክንያቱም አገልጋዩ ገንዘቡን ሊጠቀም ስለሚገባው መንገድ መሪ ውና አገልጋዩ የተለያዩ ግንዛቤዎች ሊኖሯቸው ስለሚችል፡፡ ግልጽ መመሪያዎች አገልጋዩ የቤተ ክርስቲያንን ገንዘብ ለምን ጉዳይ ሊጠቀምበት እንደሚችል እንዲያውቅ ይረዳዋል፡፡ ይህ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችም አገልጋዩ ገንዘቡን በምን ሥራ ላይ እንዳዋለ ለመከታተል ያመቻቸዋል፡፡ ግልጽ መመሪያዎች በቤተ ክርስቲያን መሪዎችና አገልጋዮች መካከል ሰላምና ስምምነት እንዲኖር ያደርጋሉ፡፡ የመመሪያዎቹ አለመኖር ግን በአሳብ መለያየትን ሊያመጣ ይችላል፡፡

4) የቤተ ክርስቲያን አገልጋዩ በወሩ ውስጥ የገንዘቡን እንቅስቃሴ የሚያሳይ የሂሳብ መዝገብ ማዘጋጀት አለበት፡፡ የሚቻል ሲሆን፣ ለሚያከናውናቸው ግዥዎች ሁሉ ደረሰኝ ሊኖረው ይገባል፡፡ ገንዘቡን ያወጣበትን ሁኔታ በሚገባ የሚያሳይ የሂሳብ



መዝገብ ከሌለው፣ ለተደረገው ወጪ ከኪሱ እንደሚከፍል ማወቅ አለበት፡፡ ይህ አገልጋዩ ጥሩ የገንዘብ አያያዝ እንዲከተል ያግዘዋል፡፡

5) በየወሩ መጨረሻ ላይ፣ የቤተ ክርስቲያን መሪው የገንዘቡን እንቅስቃሴ በተመለከተ ከአገልጋዩ ጋር መነጋገር አለበት፡፡ በወሩ ውስጥ ወጪ የተደረገውን ገንዘብ በመመልከት ይህ ሽማግሌዎች ካወጡት መመሪያ ጋር መስማማት አለመስማማቱን ማረጋገጥ አለበት፡፡ የቤተ ክርስቲያን መሪው የአገልጋዩ የገንዘብ አጠቃቀም አስተዋይነት ያለበት አይደለም ብሎ ካሰበ፣ ለአገልጋዩ ሥልጠና በመስጠት የእግዚአብሔር ገንዘብ ክብክነት የሚድንበትን መንገድ መፈለግ አለበት፡፡ ይሁን እንጂ፣ አገልጋዩ የሚሰጠውን ሥልጠናና መመሪያ ባለመከተል ገንዘብ የሚያባክን ከሆነ፣ የገንዘቡ አያያዙ ለሌላ ሰው መስጠት አለበት፡፡

6) ያለፈውን ወር የገንዘብ አያያዝ ከመረመረ በኋላ፣ የቤተ ክርስቲያን መሪው ለቀጣዩ ወር አሁንም አነስተኛ በጀት በአገልጋዩ እጅ እንዲቀመጥ ያደርጋል፡፡

***ለምሳሌ፡-*** *በትልቅ የከተማ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሽማግሌዎች 500 ብር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ባለ ሳጥን ውስጥ እንዲቆለፍና መጋቢው እያወጣ ለተለያዩ ወጪዎች እንዲያውል ይስማማሉ እንበል፡፡ ከዚህ ገንዘብ ላይ አንሥቶ ለመብራትና ለውኃ መክፈል የመጋቢው ኃላፊነት ይሆናል፡፡ የእነዚህ ወጪዎች ሂሳብ 150 ብር ሊሆን ይችላል፡፡ ሽማግሌዎች ለቤተ ክርስቲያን ሠራተኞችና ጎብኘ ዎች ሻይ እንዲዘጋጅ ተስማምተዋል፡፡ የዚህ ሂሳብ 50 ብር ሊሆን ይችላል፡፡ ድንገተኛ የሕክምና ወጪ የሚያስፈልጋት ድሀ የቤተ ክርስቲያን አባል ትመጣለች፡፡ ሽማግሌዎች አገልጋዩ ድንገተኛ ችግር ለሚደርስባቸው አባላት እስከ 20 ብር እንዲሰጥ ስለ ፈቀዱለት፣ ይህንኑ 20 ብር ለእርሷ ይሰጣታል፡፡ በወሩ መጨረሻ ላይ መጋቢው 220 ብር አውጥቷል፡፡ የሽማግሌዎቹ ሰብሳቢ ደ ረሰኞቹን ከተመለከተና ገንዘቡ የወጣበትን ሁኔታ ከመረመረ በኋላ፣ ለሚቀጥለውም ወር መጋቢው ለትናንሽ ወጪዎች እንዲጠቀምበት ከገንዘብ ቤት 220 ብር እንዲሰጠው ያደርጋል፡፡*

> 5ኛ ጥያቄ:- ሀ) ለቤተ ክርስቲያናችሁ አነስተኛ የገንዘብ ሥርዓት ለማዘጋጀት ብትፈልግ፣ የቤተ ክርስቲያናችሁ ቢሮ ወይም መጋቢው ምን ያህል ብር ሊይዝ ይገባል? ለ) ከዚህ በጀት በየወሩ ክፍያ መደረግ ያለበት ለምን ምን ነገሮች እንደ ሆነ ግለጽ:: ይህ በወር ስንት ብር እንደሚፈጅ ገምት:: ምን ያህል አነስተኛ ገንዘብ እንደሚያስፈልግ ይህ የሚያሳይህ እንዴት ነው?

3. ለሚፈጠሩት ችግሮች መፍቻ ብቻ ሳይሆን ስልታዊ የሆነ የገንዘብ አመዳደብ ተጠቀም::

ብዙ ቤተ ክርስቲያኖች ለአስፈላጊ አገልግሎቶች ገንዘብ ባለመመደብ ይሳሳታሉ:: ስልታዊ ምደባ ከመከተል ይልቅ፣ አንድ ችግር ሲከሰት ለችግሩ መፍቻ ከእጃቸው ላይ ያለውን ገንዘብ ያወጣሉ:: ይህንን በምናደርግበት ጊዜ፣ ገንዘቡን የምናውለው ስልታዊ ጠቀሜታ ላላቸው አገልግሎቶች ሳይሆን፣ አምብዛም አስፈላጊ ላልሆኑ ነገሮች ሊሆን ይችላል:: አስተዋይ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የሚፈጠሩ ችግሮች የገንዘብ አወጣጡን እንዲወስኑ ከማድረግ ይልቅ፣ የእግዚአብሔርን ገንዘብ እንዴት በስልታዊ መንገዶች እንደሚጠቀሙ ዕቅድ ያወጣሉ:: ባለ አደራዎች እንደ መሆናችን መጠን፣ የእግዚአብሔር ገንዘብ መንግሥቱን ለመገንባት በሚጠቅሙ ነገሮች ላይ እንዲውል የምንችለውን ጥረት ሁሉ ማድረግ ይኖርብናል:: በትምህርት ዘጠኝ ውስጥ በሳል በሆነች ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሁሉም ዓይነት የአገልግሎት ዘርፎች (የወንጌል ስርጭት፣ ማስተማር፣ ድሆችን መርዳት) መዘጋጀት እንዳለበት ገልጸናል:: ይህ ማለት እያንዳንዱ የአገልግሎት ዘርፍ እግዚአብሔር በሚፈልገው መንገድ ለማደግ ገንዘብ ያስፈልገዋል ማለት ነው:: እያንዳንዱ አገልግሎት ራእዮቹንና ዕቅዶቹን በሚያዘጋጅበት ጊዜ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ለእያንዳንዱ አገልግሎት በጀት ሊመድቡና በዚያው መጠን ክፍያ ሊፈጽሙ ይገባል:: የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ካልተጠነቀቁ፣ አንድ ወይም ሁለት የአገልግሎት ዘርፎች ብቻ ገንዘቡን ሁሉ ሙልጭ አድርገው ሊጠቀሙ ይችላሉ:: ገንዘቡ ሁሉ ለአጣዳፊ



ነገሮች ይውልና አስፈላጊዎቹን አገልግሎቶች ለማካሄድ የገንዘብ እጥረት ሊከሰት ይችላል::

4. ቤተ ክርስቲያኒቱ ለቀጣዩ ዓመት ገንዘቧን ለምን ምን ነገሮች እንደምታወጣ የሚያሳይ በጀት አዘጋጅ::

ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ ሽማግሌዎች በዓመቱ ውስጥ የሚፈጽሟቸውን የሂሳብ ጉዳዮች አስመልክተው በጀት ማዘጋጀት አለባቸው:: ባለፈው ዓመት ገቢ ላይ በመመሥረት በቀጣዩ ዓመት ምን ያህል አሥራትና መባ ሊገባ እንደሚችል በእምነት ማቀድ አለባቸው:: ከዚያም ለዓመቱ ወርሐዊ በጀት ማዘጋጀት ያስፈልጋቸዋል:: ይህ በጀት የሚከተሉትን አምስት አካባቢዎች የሚዳስስ መሆን አለበት:-

ሀ. መክፈል ያለባቸውን ወጪዎች በሙሉ:: ለምሳሌ፣ የሠራተኞች ደመወዝ፣ የመብራት፣ የስልክና የውኃ ወጪዎች፣ የቢሮ ወጪዎች፣ የቦርድ ስብሰባ ወጪዎች የመሳሰሉት መታሰብ ያለባቸው ናቸው:: እነዚህን የግድ «መክፈል ያለባቸውን» ወጪዎች ካሰላ በኋላ፣ ቦርዱ ለእነዚህ ወጪዎች ቅድሚያ እንዲሰጥ ይወስናል::

ለ. እጅግ ስልታዊ ለሆኑ አገልግሎቶች ገንዘብ መመደብ:: አብያተ ክርስቲያናት ለዐበይት የአገልግሎት ዘርፎቻቸው ገንዘብ የሚመድቡባቸው የተለያዩ መንገዶች አሉ:: አንዳንዶች የአገልግሎት ዘርፉ ኃላፊዎች (ለምሳሌ፣ መጋቢ፣ ወንጌላዊ፣ የሰንበት ትምህርት ቤት ዳይሬክተር) ዓመታዊ ዕቅዶቻቸውን እንዲያቀርቡ ይጠይቃሉ:: እያንዳንዱ አገልጋይ ዕቅዱን ካቀረበ በኋላ፣ በዕቅዱ ስልታዊነትና ቤተ ክርስቲያኒቱ ወጪዎቹን ለመሸፈን በመቻሏ ጉዳይ ላይ ይወያያሉ:: ብዙውን ጊዜ በዕቅዱ ላይ የሚጠየቀው ገንዘብ ከቤተ ክርስቲያኗ አቅም ሊበልጥ ስለሚችል፣ የቤተ ክርስቲያኒቱ መሪዎች ውይይት አድርገው ሚዛናዊ የገንዘብ መጠን ለየአገልግሎቱ እንዲመደብ ያደርጋሉ:: ሌላው አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት የሚጠቀሙበት የገንዘብ አመዳደብ በመቶኛ ላይ የተመሠረተ ነው:: ለምሳሌ፣ ከአስራትና ምጽዋት ገቢ ከሆነው

ገንዘብ 15 በመቶውን ለብሔራዊ የወንጌል አገልግሎት፣ 15 በመቶ ለአካባቢው የወንጌል አገልግሎት ለመስጠት፣ 20 በመቶ ለመንፈሳዊ እድገት (ለደቀ መዝሙርነት ትምህርት)፣ 10 በመቶ ለአምልኮ፣ 10 በመቶ ድሆችን ለመርዳት፣ 20 በመቶ ለአጠቃላይ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎትና ለድንገተኛ ጉዳዮች መመደብ ይቻላል:: የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የትኛውንም ዓይነት አመዳደብ ቢከተሉ፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሚዛናዊ ፕሮግራም ለማካሄድ እንዲቻል ገንዘቡ እንደ አምልኮ ወይም የወንጌል ስርጭት ባለው አንድ ዘርፍ ላይ ብቻ ሳይሆን፣ ለሁሉም የአገልግሎት ዘርፎች እንዲዳረስ ማድረግ አለባቸው::

ሐ. የተወሰነውን ገንዘብ ለቀጣይ ዓመታት ማስቀመጥ:: ለምሳሌ፣ ቤተ ክርስቲያን የሕንጻ ግንባታ የማካሄድ ዓላማ ካላት፣ ከአሁኑ ገንዘብ መቆጠብ ያስፈልጋታል:: ወይም ደግሞ በየጊዜው የጥገና ሥራዎችን ማካሄድ ሊያስፈልግ ይችላል:: እንደ ድምፅ ማጉያ ያሉ ዕቃዎች ሊያረጁና ሊበላሹ ስለሚችሉ፣ እነርሱን ለመተካት የሚያስችል ገንዘብም ማስቀመጡ ተገቢ ነው:: ለእንደዚህ ዓይነት ነገሮች ዕቅዶችን የማናወጣ ከሆነ፣ በቀላሉ ሊጠገን የሚችል ጊታር ተበላሽቶ ቁጭ ሊል ይችላል:: ሕንጻውም ለዓይን አስቀያሚ ሆኖ ሊገኝ ይችላል:: ይህ ደግሞ ጥሩ ምስክርነት የሚያሳይ አይደለም:: በጥሩ ሁኔታ ወዳልተያዘ ቤተ ክርስቲያን መምጣት የሚፈልግ ማን ነው?

መ. ሳልተጠበቁ ጉዳዮች የተወሰነ ገንዘብ ማስቀመጥ:: እንበልና አንድ ዛፍ በቤተ ክርስቲያን ሕንጻ ላይ ይወድቃል:: ጣሪያውን ለማሳደስ ወይም ገንዘብ የሌለውን የታመመ አገልጋይ ለማሳከም ገንዘብ ያስፈልጋል:: አስተዋይ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሁልጊዜም ለእንዲህ ዓይነት ነገሮች ገንዘብ ማስቀመጥ አለባቸው::

ሠ. እምብዛም አስፈላጊ ሳልሆኑ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎቶች ተጨማሪ ገንዘብ ወጪ የሚደረግባቸውን ሁኔታዎች መወሰን:: አልፎ አልፎ እግዚአብሔር ከገመትነው በላይ በገንዘብ ይባርከናል:: የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ይህንን እግዚአብሔር



የሰጣቸውን ተጨማሪ ገንዘብ እንዴት በጥበብና ስልታዊ በሆነ መንገድ ሊጠቀሙበት እንደሚችሉ መወሰን ይኖርባቸዋል::

> 6ኛ ጥያቄ:- ሀ) ቤተ ክርስቲያናችሁ «የግድ ልትከፍላቸው» የሚገቡ ወጪዎች ምን ምንድን ናቸው? ለ) በቤተ ክርስቲያናችሁ ገንዘብን የሚጠይቁ ስልታዊ አገልግሎቶች የትኞቹ ናቸው? ለዚህ ጉዳይ ለምን ቅድሚያ መስጠት እለበት ብለህ እንደምታስብ ግለጽ:: ሐ) እምብዛም አስፈላጊ ያልሆኑና ዳሩ ግን ቤተ ክርስቲያናችሁ ለእግዚአብሔር ክብር ገንዘብ ልትከፍል የሚገባት አንዳንድ ተግባራት ምን ምንድን ናቸው? መ) ከእነዚህ መካከል በአሁኑ ጊዜ የቤተ ክርስቲያናችሁ ገንዘብ በብዛት የሚውለው በየትኞቹ አገልግሎቶች ላይ ነው?

5. በዓመቱ መጨረሻ አካባቢ የገንዘብ ችግር እንዳይከሰት ጥንቃቄ ማድረግ::

እግዚአብሔር ከሰጠን ስጦታዎች አንዱ ለወደፊት የማቀድ ችሎታ ነው:: ለምሳሌ፣ ተጨማሪ የቤት ግንባታ ለማካሄድ በማሰብ ገንዘብ እንቆጥባለን:: ቤተ ክርስቲያን ለመገንባት በምናስብበት ጊዜ፣ ግንባታውን ከመጀመራችን በፊት ገንዘብ እንቆጥባለን:: በተመሳሳይ ሁኔታ፣ የቤተ ክርስቲያን አስተዋይ መሪዎችም አስፈላጊዎቹን ወጪዎች በማሰብ አስቀድመው ለዚሁ ጉዳይ ገንዘብ ይመድባሉ:: ለምሳሌ፣ መሪዎች ቤተ ክርስቲያናቸው አያደገች ስለሆነ፣ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ በቤተ ክርስቲያን ሕንፃ ላይ ተጨማሪ ክፍል መሥራት እንደሚያስፈልጋቸው ይገነዘባሉ:: ክፍሉን መሥራት እስከሚያስፈልጋቸው ድረስ ቆይተው ከዚያ በኋላ ገንዘብ ሊጠይቁ ይችላሉ:: ነገር ግን የሚሻለው ለሁለት ዓመታት ያህል በየወሩ አነስተኛ ገንዘብ በማስቀመጥ የተወሰነ ያህል ገንዘብ እንዲኖር ማድረግ ነው:: ይህ በተለይ ለመደበኛ የቤተ ክርስቲያን ሕንፃ ጥገና አስፈላጊ ነው:: ብዙ ማኅበረ ምእመናን ውብ ሕንፃ ይገነባሉ፣ ነገር ግን ቤተ ክርስቲያኑን ቀሰም መቀባት ወይም ዝናብ የግድግዳውን ጭቃ በሚያጥብበት ጊዜ መጠገን የሚችሉበትን ገንዘብ አያስቀምጡም:: ብዙም ሳይቆይ እነዚያ ያምሩ የነበሩ ሕንፃዎች የማያምሩ ይሆናሉ፣ ለጥገና የሚሆን ገንዘብም አይኖርም:: ወይም ደግሞ አንድ ቤተ ክርስቲያን ለአምስት ዓመታት የሚቆይ አንድ ኮምፒውተር ይኖረው ይሆናል:: የቤተ ክርስቲያን መሪዎች

በየዓመቱ የተወሰነ ገንዘብ ካላስቀመጡ፣ አንድ ቀን ኮምፒውተሩ ይበላሻል፣ ቤተ ክርስቲያንም አዲስ ኮምፒዩተር የምትገዛበት ገንዘብ አይኖራትም። የዕቅድ አለመኖር ብዙውን ጊዜ ለቤተ ክርስቲያን አላስፈላጊ የሆነ መከራ ይፈጥርባታል። ልክ በልብሳችን ላይ ያለን ትንሽ ቀዳዳ እስኪሰፋ ድረስ ሳንጠብቅ ወዲያውኑ መስፋቱ ቀላል እንደሚሆነው ሁሉ፣ ቤተ ክርስቲያናችንን ለመጠገን የሚያስፈልገውን ገንዘብ ማስቀመጡም ኋላ ለከፍተኛ ጥገና ገንዘብ ከመፈለግ ያድነናል።

6. ውስብስብነቱ በቤተ ክርስቲያናችሁ ፍላጎት መሠረት የሚወሰን ጥሩ፣ ቀለል ያለ የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት አዘጋጅ።

ሀ. ገንዘብ እንዳይባክን ለመከላከል ቁልፉ የእግዚአብሔርን ገንዘብ በሚገባ ለማስተዳደር የሚያስችለን ቀለል ያለ፣ ግን ግልጽ መረጃዎችን የያዘ የገንዘብ አያያዝ ዘዴ ማዘጋጀት ነው። ስለዚህ፣ የቤተ ክርስቲያን የገንዘብ አያያዝ ሥርዓት መዘጋጀት ያለበት በቤተ ክርስቲያኒቱ ወይም በቤተ ክርስቲያን ጽ/ቤት ፍላጎት መሠረት ነው። አንዲት ቤተ ክርስቲያን አነስተኛ ከሆነች እና ያላትም ገንዘብ አነስተኛ ከሆነ፣ ለዚያ ቀለል ያለ የሂሳብ መዝገብ አያያዝ ሥርዓት በቂ ነው። አነስተኛ ቤተ ክርስቲያን መሪዎቿ ሊጠቀሙበት እስከማይችሉ ድረስ ውስብስብ የሆነ የገንዘብ አያያዝ ሥርዓት አያስፈልጋትም። ነገር ግን የቤተ ክርስቲያን ጽ/ቤት ለብዙ የእግዚአብሔር ገንዘብ ኃላፊ ከሆነ፣ ሁሉንም ገንዘብ በደንብ ሊይዝ የሚችል ይበልጥ የተጠናከረ የገንዘብ አያያዝ ሥርዓት መዘርጋት ያስፈልገዋል። እግዚአብሔር ለሕዝቡ ገንዘብ የሚሰጠው በደንብ ማስተዳደር እስከ ቻሉ ድረስ ብቻ ነው ሲል አንድ መሪ ተናግሯል። ስለዚህ፣ እግዚአብሔር ለመንግሥቱ ጥቅም የምናውለው ብዙ ገንዘብ እንዲሰጠን ከፈለግን፣ እግዚአብሔር ሊሰጠን የሚፈልገውን ገንዘብ በታማኝነት የምናስተዳድርበትን ችሎታ ማሳደግ አለብን።

ለ. እስከ ተቻለ ድረስ እያንዳንዱ ክፍያ ደረሰኝ ሊኖረው ይገባል። ለምሳሌ፣ የቤተ ክርስቲያኒቱ መጋቢ ለሚጠቀሙበት ኩራዝ ላምባ ቢገዛ፣ ግለሰቡ ላምባውን በሚገዛበት ጊዜ ደረሰኝ



ለማግኘት መሞከር ይገባዋል። ወይም የቤተ ክርስቲያን ሠራተኛው ደመወዝ በሚቀበልበት ጊዜ፣ ገንዘቡን ስለ መቀበሉ ደረሰኝ መፈ ረም ይኖርበታል። ሆኖም ግን፣ አንዳንድ ጊዜ ለእያንዳንዱ ነገር ደ ረሰኝ ማግኘት አይቻልም። ደረሰኝ በማይኖርበት ጊዜ፣ ገንዘቡን ወጪ ያደረገው ሰው ገንዘቡን እንዴት እንደ ተጠቀመበት ማስረዳት ይገባዋል። ያለ ደረሰኝ የሚከናወኑ በርካታ ግዢዎች በሚኖሩበት ጊዜ፣ አንዳንድ ቤተ ክርስቲያናት ከዚህ በታች የተመለከተውን ዓይነት ወርሐዊ ፎርም ያዘጋጃሉ።

| ወር______________ | | | |
|---|---|---|---|
| ቀን | የግዢው ዓላማ | የገንዘቡ መጠን | ፊርማ |
| 1/1/98 | ለሠራተኞች ስኳር መግዣ | 12.00 | |
| 15/1/98 | ለኩራዝ (ለፋኖስ) ላምባ መግዣ | 3.00 | |
| 17/1/98 | ለተጋባዥ ሰባኪ ምግብ | 15.00 | |
| 29/1/98 | ለሽማግሌዎች ስብሰባ ምግብ የሚሆን ቅመማ ቅመም እና ማጣፈጫ ዎች | 8.45 | |
| ድምር | | 38.45 | |

አንድ ነገር የተገዛበት ቀን በመጀመሪያው ዓምድ ውስጥ እንደ ተመዘገበ ልብ በል። በወሩ የመጀመሪያው ቀን ስኳር ተገዛ፣ በአሥራ አምስተኛው ቀን ላምባ፣ ወዘተ. . . በሁለተኛው ዓምድ ውስጥ፣ የተገዛው ዕቃ ስም ዝርዝር ተመዝግቧል፣ በሦስተኛው ዓምድ ውስጥ የወጣው ገንዘብ መጠን፣ እንዲሁም በአራተኛው ዓምድ ውስጥ፣ ዕቃዎቹን የገዛው ግለሰብ ፊርማውን ያኖራል። በቅጹ ግርጌ በዚያን ወር የወጣው ገንዘብ ጠቅላላ ድምር ይሰፍራል።

ይህንን ቅጽ የሚሞላው ሰው ብዙ ነገሮችን በጥቅሉ አንድ ላይ ከሚያሰፍር እያንዳንዱን ግዢ መጻፉ አስፈላጊ ነው:: ይህ ቅጽ ሁለት አስፈላጊ ተግባራትን እንደሚሰጥ አስታውሱ:: በመጀመሪያ፣ መንፈስ ቅዱስ ገንዘብ የማባክንን ፈተና ለማቃለል ይጠቀምበታል:: ዕቃዎችን እንድንገዛበት የተሰጠንን ገንዘብ የሆነ ሰው እንደሚቆጣጠረው ካወቅን፣ የተወሰነውን ለራሳችን የማስቀረቱ ዕድል በጣም ዝቅተኛ ይሆናል:: ሁለተኛ፣ ሁሉም ሰው የእግዚአብሔር ገንዘብ በሚገባ ጥቅም ላይ እየዋለ መሆኑን እንዲያውቅ በማድረግ ታማኝነታችንን የምናስመሰክርበት መንገድ ነው:: ወጪዎችን ብቻ አጠቃልለን የምናስቀምጥ ከሆነ፣ ሰዎች ጥቂት ገንዘብ እንደ ወሰድን እንዲያስቡ ስለሚያደርጋቸው፣ ስማችንን ያጎድፈዋል:: ስለዚህ፣ በኮንፈረንስ ወቅት 200 ብር ወጪ አድርገናል ብሎ ከመፈረም ይልቅ፣ ሸቀጣ ሸቀጦቹን የገዙት ሰዎች የሸቀጦቹን ዝርዝር (ለምሳሌ፣ ስኳር፣ ቅመማ ቅመማ፣ ጤፍ፣ ሥጋ፣ ምስር፣ ወዘተ . . . ቢያቀርቡ ይመረጣል::)

ሐ. እያንዳንዱ የአገልግሎት ክፍል የራሱ የሂሳብ መዝገብ ሊኖረው ይገባል:: ለምሳሌ፣ አንድ ትልቅ ቤተ ክርስቲያን ለወንጌል ስርጭት፣ ለአስተዳደር፣ ለሰንበት ትምህርት ቤት ፕሮግራም፣ ለድሆች እርዳታ፣ እና ለመሳሰሉት የተለያዩ የሂሳብ መዝገቦች ያስፈልጋት ይሆናል:: ቤተ ክርስቲያኒቱ እንደ የቤተ ክርስቲያን ሕንፃ ግንባታ፣ የልማት ፕሮጀክት፣ የሙዚቃ መሣሪያ ግዢ እና ለመሳሰሉት የአጭር ጊዜ ፕሮጀክቶች የተለየ የሂሳብ መዝገብ መክፈት ያስፈልጋት ይሆናል:: አነስተኛ ቤተ ክርስቲያን በአሥራትና መባ መልኩ ለሚሰጡ ለተወሰነ ፕሮጀክት ተብለው ተለይተው ያልተሰጡ ገንዘቦችን የምትይዝበት አንድ አጠቃላይ የሂሳብ መዝገብ ብቻ ያስፈልጋት ይሆናል::

አዲስ ቤተ ክርስቲያን እንደ መገንባት፣ የመዘምራን ልብስ መግዛት ወይም የሙዚቃ መሣሪያዎችን መግዛት የመሳሰሉ የአጭር ጊዜ ፕሮጀክቶች የየራሳቸው የሂሳብ መዝገብ ያስፈልጋቸዋል:: የአጭር ጊዜ ፕሮጀክቶች የሂሳብ መዝገብ የሚያስፈልጋቸው ሀ) ሁሉንም ገንዘብ ካልተቀበልንና ካልከፈልን፣



ወይም ለ) ፕሮጀክቱ እስኪጠናቀቅ ብቻ ነው:: ስለዚህ፣ ወጣቶች ለጊታር መግዣ የሚያስፈልግ ገንዘብ አዋጥተው አንድ ሰው እንዲገዛው ከላኩ፣ የሂሳብ መዝገቡ አስፈላጊ አይሆንም:: የሚያስፈልገው ጊታሩ በስንት ብር እንደ ተገዛ የሚያሳይ ደረሰኝ ብቻ ነው:: ነገር ግን ወጣቶቹ ለብዙ ወራት ለጊታር መግዣ የሚያስፈልግ ገንዘብ ሲያሰባስቡ ከቆዩ፣ ጊታሩን ለመግዛት የሚያስችል ገንዘብ እስኪገኝ ድረስ የሂሳብ መዝገብ ማዘጋጀቱ አስፈላጊ ይሆናል:: ጊታሩ ከተገዛ በኋላ፣ ሂሳቡ ይዘጋል::

*7ኛ ጥያቄ፦ ቤተ ክርስቲያናችሁ ለዋና ዋና አገልግሎቶቿ የሂሳብ መዝገብ አያያዝ ለማዘጋጀት ለየትኞቹ አገልግሎቶች የሂሳብ መዝገብ ማካሄድ እንዳለባት ግለጽ::*

መ. ከዚህ በታች የተመለከተውን የሂሳብ መዝገብ ተመልከት:: ይህ የሂሳብ መዝገብ ናሙና የሂሳብ መዝገብ ማዘጋጀት ከሚቻልባቸው መንገዶች አንዱን የሚያሳይ ነው:: (ገንዘብ ስንቀበል ወይም ስንሰጥ ሁልጊዜም በዚህ ቅጽ ላይ መመዝገብ እንዳለብን አስታውስ::)

| የቤተ ክርስቲያን አጠቃላይ ሂሳብ | | | | | መስከረም 2000 |
|---|---|---|---|---|---|
| ቀን | ምክንያት | የደረሰኝ ቁጥር | ገቢ | ወጪ | ከወጪ ቀሪ |
| 1/1/99 | ከ30/12/98 የዞረ ሂሳብ | | | | 3000.00 |
| 1/1/99 | ለሠራተኞች ስኳር | ቅጽ | | 12.00 | 2988.00 |
| 7/1/99 | መባ | | 85.45 | | 3073.45 |
| 14/1/99 | መባ | | 74.35 | | 3147.80 |
| 15/1/99 | ለፋኖስ ጋዝ መግዣ | ቁጥር 124 | | 3.00 | 3144.80 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 17/1/99 | ለአንግዳው ሰባኪ የምግብ ወጪ | ቅጽ | | 45.55 | 3099.25 |
| 21/1/99 | መባ | | 91.35 | | 3190.60 |
| 28/1/99 | አሥራት | | 525.00 | | 3190.60 |
| 28/1/99 | መባ | | 65.35 | | 3780.95 |
| 29/1/99 | ለሽማግሌዎች የምግብ ዝግጅት ወጪ | ቅጽ | | 8.45 | 3772.50 |
| 30/1/99 | ለወንጌላዊ ደመወዝ | ቅጽ | | 350.00 | 3422.50 |
| ድምር | | | 841.50 | 419.00 | 3422.50 |

*ይህ ሠንጠረዥ የሚከተሉትን ነገሮች ያሳያል፡-*

*1) የሁሉም ወርሐዊ የገንዘብ ቅጽ የመጀመሪያው መስመር የሚያሳየው በቀድሞው ወር ቅጽ ላይ የነበረውን ቀሪ ሂሳብ ነው:: ይህ በዚህ ቅጽ ውስጥ በ30/12/99 የተጻፈው የገንዘብ መጠን ነው::*

*2) መጀመሪያው ዓምድ ገንዘቡ ገቢ ወይም ወጪ የተደረገበት ቀን ነው::*

*3) ምክንያት የሚለው ገንዘቡ ገቢ ወይም ወጪ የተደረገበትን ምክንያት ያሳያል::*

*4) የደረሰኙን ቁጥር የሚጠይቀው ዓምድ ስክፍያው ደረሰኝ ከተገኘ የደረሰኙ ቁጥር የሚመዘገብበት ነው:: ካልሆነ፣ ደረሰኝ ሳልተገኘለት ወጪ የተሞላውን «ፎርም» መግለጽ ይቻላል:: ይህ ኦዲተሩ ገንዘብ በትክክል መውጣቱን ለማረጋገጥ ቅጹን ፈልጎ እንዲያጣራ ያስችለዋል::*

*5) የገቢ ዓምድ ከአሥራትና መባ የተገኘውን ገቢ የሚያሳይ ነው::*

*6) የወጪ ዓምድ ደግሞ የሆነ ነገር ለመግዛት ወይም ደመወዝ ለመክፈል የወጡ ወጪዎች የሚመዘገቡበት ነው::*



*7) «ከወጪ ቀሪ ሂሳብ» ከወጪ የተረፈውንና በሳጥን ወይም በባንክ ቤት ያለውን ገንዘብ ያሳያል:: ይህ የገንዘብ መጠን ገቢ ሲጨምር ይጨምራል:: ወጪው ሲጨምር ግን ይቀንሳል:: ይህ የቤተ ክርስቲያን መሪው በእያንዳንዱ መዝገብ ውስጥ ምን ያህል ገንዘብ እንዳለ እንዲያውቅ ያስችለዋል::*

*8) «ድምር» ደግሞ የገቢውን ድምር፣ የወጪውን ድምር፣ እንዲሁም የቀሪውን ገንዘብ ድምር ያሳያል:: በእነዚህ ሦስት ድምሮች አማካኝነት ሂሳቡ ትክክል መሆን አለመሆኑን ማረጋገጥ ይቻላል:: በመጀመሪያው ላይ በቅጹ ላይ ያለውን ገንዘብ (3000) በገቢው ላይ (841.50) ብትደምር እና የወጪውን ድምር (419.00) ብትቀንስ፣ ቀሪውን ሂሳብ (3422.50) ታገኛለህ::*

*ትክክለኛ የሂሳብ አያያዝ ለመከተል እያንዳንዱ አገልግሎት እንዲህ ዓይነት ቅጽ ማዘጋጀት አለበት:: ለምሳሌ፣ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ፣ የወንጌል አገልግሎትና የሥልጠና ዘርፍ፣ የቤተ ክርስቲያን ሕንጻ ግንባታ ወይም የመዘምራን ልብስ ግዢ እያንዳንዳቸው እንዲህ ዓይነት ቅጽ ማዘጋጀት አለባቸው:: (ማስታወሻ፡- ቤተ ክርስቲያን ለሕንጻ ግንባታ ገንዘብ ካሰባሰበች፣ ለዚሁ ሥራ ልዩ ቅጽ ማዘጋጀት አለባት:: ለመዘምራን ልብስ ወይም ለሙዚቃ መሣሪያዎች መግዣ የሚሰባሰበውም ገንዘብ የየራሱ ቅጽ ላይ መመዝገብ አለበት:: ቤተ ክርስቲያን ከአጠቃላይ ሂሳቧ መለየት የምትፈልጋቸው የወንጌል ስርጭት፣ ድሆችን የመርዳት ሂሳቦች ለብቻቸው መመዝገብ አለባቸው::)*

*8ኛ ጥያቄ፡- ሀ) በወረቀት ላይ ከላይ የተመለከተውን የሚመስል ሠንጠረዥ ሥራ:: ለ) ለቀጣዩ ወር ያለህን ገንዘብ ተመልከት:: (ቤትህ ወይም ባንክ ቤት ውስጥ ስንት ብር እንዳለህ አረጋግጥ::) ገንዘብ በምታወጣበት ጊዜ ሁሉ በሠንጠረዥ ላይ ቁጥሩን አስፍር:: ገንዘብ በምታገኝበት ጊዜ (ደመወዝ ወይም ከሆነ ሰው ስጦታ ስትቀበል) በገቢ ዓምድ ላይ አስፍር::*

*ሠ. በእያንዳንዱ የሂሳብ ቅጽ ላይ የተገለጸው የገንዘብ ድምር በባንክ ውስጥ ወይም በሳጥን ውስጥ ካለውና በቤተ ክርስቲያን ቢሮ ወይም በቤተ ክርስቲያን መሪው እጅ ካለው ገንዘብ ጋር እኩል መሆን አለበት:: ይህ ካልሆነ፣ የሂሳብ አሠራሩ ትክክል አይደለም*

መሪዎች አሥራትን ስለ መስጠት ማስተማር ሊያስፈልጋቸው ይችላል:: እግዘአብሔር ለሥራው በልግስና የማይሰጡትን ሰዎች እምብዛም አይባርካቸውም:: የሂሳብ ሪፖርቱ የቤተ ክርስቲያን መሪ ዎች በሚቀጥሉት ወራት ውስጥ የሚኖራቸውን ገንዘብ በማወቅ ለቀጣይ ሥራዎች (የስድስት ወራት ወይም የአንድ ዓመት) በጀት እንዲያዘጋጁ ያስችላቸዋል:: ሕዝቡ በወር 100 ብር የሚሰጥ ከሆነ፣ የቤተ ክርስቲያኒቱ መሪዎች በወር 200 ብር የሚፈጅ ተግባር ለማከናወን ማቀድ አያስፈልጋቸውም::

ሐ. የሂሳብ ሪፖርት ቦርዱና መሪዎች የእግዚአብሔር ገንዘብ መልካም ባለአደራዎች መሆን አለመሆናቸውን እንዲመዝኑ ያስችላቸዋል:: ሪፖርቱ የእግዚአብሔር ገንዘብ ከጥቅም ላይ እየዋለ ያለበትን ሁኔታ የሚያሳይ መሆን አለበት:: የቤተ ክርስቲያን መሪ ዎች እነዚህ ወጪዎች የእግዚአብሔርን መንግሥት በከፍተኛ ደ ረጃ በሚያስፋፉ ጉዳዮች ላይ መዋላቸውን ማረጋገጥ አለባቸው:: አብዛኛው ገንዘብ ዘላለማዊ ጠቀሜታ ካላቸው ነገሮች ይልቅ በአነስተኛ ጉዳዮች (ለምሳሌ፣ ከምስክርት ይልቅ ለሽማግሌዎች ምግብና ትራንስፖርት) የሚውል ከሆነ፣ መሪዎች በጉዳዩ ላይ ተነጋግረው መፍትሔ ማግኘት አለባቸው::

ስለ ሁሉም አገልግሎቶች መረጃ የሚሰጥ የሂሳብ ሪፖርት ብዙ ዝርዝር ጉዳዮችን ሳያነሣ በሚከተሉት ነጥቦች ላይ ትኩረት ቢሰጥ የተሻለ ነው:-

ሀ. በሁሉም የቤተ ክርስቲያኒቱ የሂሳብ አካባቢዎች ስላለው ገንዘብ ጠቅለል ያሉ አሳቦችን ማቅረብ:: በመሆኑም በአጠቃላይ ሂሳብ፣ በወንጌል ስርጭት፣ በሕንጻ ግንባታ፣ ወዘተ. . . ምን ያህል ገንዘብ እንዳለ መግለጽ አለበት::

ለ. ሪፖርቱ በሚያካትተው ጊዜ ውስጥ የተገኘው አጠቃላይ ገቢ መጠቀስ አለበት:: ይህ በአሥራት፣ በመባና በልዩ ስጦታዎች የተገኘን ገንዘብ የሚያካትት ሊሆን ይችላል::

ሐ. በዚህ ጊዜ ውስጥ ምን ያህል ገንዘብ ወጪ እንደ ተደረገ የሚያሳይ መግለጫ:: ሪፖርቱን የሚያቀርበው ሰው ዋና ዋናዎቹን



ወጪዎች መግለጹ መሪዎች በምን ምን ጉዳዮች ላይ አብዛኛው ገንዘብ እንደሚውል እንዲገነዘቡ ያስችላቸዋል:: (ለምሳሌ፣ ለደመወዝ 500 ብር፣ ለምግብ 100 ብር፣ መብራትና ውኃ 45 ብር፣ ወዘተ. . .)

መ. የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ማወቅ ያለባቸው «አዝማሚያዎች»:: ይህ ሰዎች ብዙ ገንዘብ መስጠት ወይም አለመስጠት መጀመራቸውን የሚያሳይ ሊሆን ይችላል:: ወይም ደግሞ ይህ የገንዘብ ሹሙን የሚያሳስቡትን ነገሮች የሚያሳይ ሊሆን ይችላል:: ለምሳሌ፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከመጠን በላይ ገንዘብ እያወጡ ከሆነ፣ የሂሳብ ሹሙ ስለ ጉዳዩ ለሽማግሌ ዎች ማሳወቅ አለበት:: ይህም ሽማግሌዎቹ በገንዘብ አወጣጡ ላይ ቁጠባ እንዲደረግና በአጭር ጊዜ ውስጥ ሊደርስ የሚችለውን የገንዘብ እጥረት ለመከላከል እንዲችሉ ያስችላቸዋል::

9ኛ ጥያቄ:- ስለ ሰማኸው አንድ የሂሳብ ሪፖርት አስብ:: ሀ) ሪፖርቱ የቤተ ክርስቲያኒቱን የገንዘብ ሁኔታ ለመረዳት ጠቃሚ ነበር? ለምን? ለ) ሪፖርቱ በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ እንዴት ገንዘብ ከአገልግሎት ላይ እንደሚውል የተወሰነ ግንዛቤ እንዲኖርህ አድርጓል? ሐ) ከላይ የተ ጠቀሱት ነጥቦች ሪፖቱን እንዴት ያሻሽሉታል ብለህ ታስባለህ?

10ኛ ጥያቄ:- የሂሳብ ሹሙ ቤተ ክርስቲያኒቱ ምን ዓይነት የሂሳብ አያያዝ ዘዴ እንደምትከተል እንዲነግርህ ጠይቀው:: ሀ) የገንዘብ አያያዙ ጠቃሚ ገጽታዎች ምን ምንድን ናቸው? ለ) አገልጋዮች ገንዘብ ሲፈልጉ በቀላሉ እንዲያገኙ የሚያደርግ፣ ለአጠቃቀም ቀላል የሆነና በተመሳሳይ ጊዜ ገንዘብን ከምዝበራ የሚታደግ ምን ዓይነት የገንዘብ አያያዝ ዘዴ መጠቀም ይበጃል ትላለህ? (በሳምንታዊ ስብሰባ ላይ በዚህ ጉዳይ ላይ ተወያያችሁ::)

## ሁለተኛ ቀን

እንግዳወርቅ በጣም የተሳካለት ወንጌላዊ ነበር:: ወንጌል ወዳልደ ረሰበት ቦታ ተልኮ ሲሄድ፣ በአጭር ጊዜ ውስጥ ብዙ አብያተ ክርስቲያናትን ለመትከል ቻለ:: ከአራት ዓመታት በኋላ ወደ ትልቅ ከተማ ሄደ:: በዚያም ብዙ ሰዎች በክርስቶስ በማመናቸው ቤተ ክርስቲያኒቱ በከፍተኛ ደረጃ አደገች:: ከብዙ ዓመታት በኋላ፣

ውጤታማ የቤተ ክርስቲያን ተከላ ተግባር ያከናወን አንድ ሚሲዮናዊ (የወንጌል መልእክተኛ) ነበር:: በብዙ ወሳኝ ቦታዎች አገር በቀል ወንጌላውያንን በኃላፊነት ሾመ:: ሰዎች ካመኑ በኋላ የወንጌል መልእክተኛውና ወንጌላዊው ሰዎች እግዚአብሔር ከመካከላቸው አንድ ሰው እንዲያስነሣና ይህም ሰው ሥልጠና ወስዶ እንዲያስተምራቸው እንዲጸልዩ ያበረታቷቸዋል:: ሕዝቡ አንድ ሰው ይመርጡና ለሁለት ዓመታት በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ስንቅ እያቀበሉ ያስተምሩታል:: ሠልጣኙ ስለ ቤተ ክርስቲያን አመራርና የመጋቢነት አገልግሎት ተምሮ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ይመለሳል:: ወንጌላዊው ወደ ሌላ ቦታ ይሄድና ከላይ ያደረጋቸውን ነገሮች እዚያ ይደግማል:: በጥቂት ዓመታት ውስጥ ከ50 በላይ አብያተ ክርስቲያናት ተመሠረቱ:: ለአንድ ሚሲዮናዊ ወይም ወንጌላዊ ቤተ ክርስቲያን መትከሉ ብቻ በቂ አይደለም:: አገልግሎቱን ይዘው የሚቀጥሉትን ሰዎች ማዘጋጀቱም ወሳኝ ነው:: የሚያሳዝነው፣ ብዙ ወንጌላውያን ይህንን ባለማድረጋቸው፣ እነርሱ ሲሄዱ አገልግሎቱ ይቆማል::

> *13ኛ ጥያቄ:- ሀ) መሪዎች ከሄዱ በኋላ የሚተካቸውን ሰው ባለማዘጋጀታው አገልግሎቶች ወይም አብያተ ክርስቲያናት ሲቸገሩ የተመለከትክበትን ሁኔታ ግለጽ:: ለ) የቀድሞዎቹ መሪዎች ከመልቀቃቸው በፊት የሚተካቸውን ሰው ለማዘጋጀት ምን የተሻለ ተግባር ሊፈጽሙ ይችሉ ነበር?*

2. ጳውሎስ እርሱ ከሄደ በኋላ ሰዎች የመሪነቱን አገልግሎት ይዘው እንዲቀጥሉ አስተምሯቸዋል::

ጳውሎስ ውጤታማ የወንጌል መልእክተኛ ከሆነባቸው ምክንያቶች አንዱ ባገለገለባቸው አካባቢዎች ሁሉ የሚተኩትን ወጣቶች ማሠልጠኑ ነበር:: ለምሳሌ ያህል፣ ሉቃስ፣ ጢሞቴዎስና ሲላስ አብረውት ይጓዙ ነበር:: በዚህ ጊዜ ጳውሎስ ከአብያተ ክርስቲያናት ጋር እንዴት እንደሚሠራ ለመማር ቻሉ:: ከዚያም ሰዎች የእርሱን አገዛ በሚፈልጉበት ጊዜ እነርሱን ይልካቸው ነበር (ለምሳሌ፣ የሐዋ. 17:14፤ 1ኛ ቆሮ. 4:17):: ጳውሎስ ሲታሰርና በኋላም ሲሞት፣ እንደ ጢሞቴዎስ ያሉ ሰዎች ስራ አገልግሎቱን



ይዘው ቀጠሉ:: ዛሬም አመራር ለመስጠትና አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናትን ለማስተማር ስጦታ ያላቸው ሰዎች ያስፈልጉናል:: ውጤታማ ቤተ ክርስቲያን ሁልጊዜም የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ማስተማር የሚችሉ ስጦታ ያላቸው መሪዎች አሏት::

3. ጳውሎስ ታማኝ መሪዎች የቀጣዩን ትውልድ መሪዎች እንዴት ማሠልጠን እንዳለባቸው አስተምሯቸዋል::

ጳውሎስ ጢሞቴዎስ ሌሎችን ሊያስተምሩ የሚችሉትን የታመኑ ሰዎች እንዲያስተምር ሲጠይቅ ይህን ማለቱ ነበር (2ኛ ጢሞ. 2:1-2):: ጳውሎስ ወጣቱ ጢሞቴዎስን አስተምሮታል:: አሁን ሌሎች ወጣቶች እንዴት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንደሚያገለግሉ ማስተማር የጢሞቴዎስ ተራ ነበር:: ቤተ ክርስቲያን ከትውልድ ትውልድ ጤናማ ሆና ልትሸጋገር የምትችለው ትልልቆቹ አገልጋዮች ለወጣቶቹ ተገቢውን ትምህርትና ሥልጠና ሲሰጡ ብቻ ነው:: ውጤታማ መሪዎች መሆን አለመሆናችን የሚወሰነው በዚሁ የሚተኩንን ሰዎች ለማዘጋጀት በመቻላችን ወይም ባለመቻላችን ላይ ነው::

> *14ኛ ጥያቄ:- ሀ) ጳውሎስ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ያዘጋጀበትን መንገድ ዛሬ መሪዎችን ከምናዘጋጅት መንገድ ጋር አነጻጽር:: የሚመሳሰሉት የትኞቹ ነገሮች ናቸው? ለ) ዛሬ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አዳዲስ መሪዎችን ለአገልግሎት ለማዘጋጀት ምን የተለዩ ተግባራትን ሊፈጽሙ ይችላሉ? ሐ) ብዙ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አገልግሎቱን የሚረከቡ ስጦታ ያላቸው ሰዎች በቅርበት አብረዋቸው እንዳይሠሩ የሚፈልጉት ለምንድን ነው? መ) ይህ ፍርሃት ስለ ቤተ ክርስቲያን አመራር ያላቸውን አመለካከት በተመለከተ ምን ያሳያል?*

## አመራር እግዚአብሔር በፈለገው መንገድ እንዳይካሄድ የሚከላከሉ ባህላዊ ግንዛቤዎች

*የመንፈሳዊ መሪ ባሕርያት* በሚለው አንደኛ መጽሐፋችን ውስጥ እንደ ተመለከተው፣ ባህላችን ብዙውን ጊዜ መሪ ማለት ምን እንደ ሆነ የሚሰጣቸው ፍችዎች አሉት:: በተጨማሪም ባህል አንድ ሰው ለአመራር ብቁ ስለሚሆንበት መንገድም የራሱ የሆኑ መመዘኛዎች አሉት:: ስለሆነም፣ የተለያዩ ባህላዊ የአመራር

ዝግጅት ግንዛቤዎችን በመመርመር እነዚህ እግዚአብሔር መሪ ዎችን ከሚያዘጋጅባቸው መንገዶች ጋር መመሳሰል አለመመሳሰላቸውን እንለያለን።

1. አመራር በእድሜ ላይ ይመሠረታል።

በብሉይ ኪዳን ዘመን እንደ ነበሩት አይሁዶች ሁሉ፣ በባህላዊ የአፍሪካ ማኅበረሰቦች ውስጥም የሕዝብ መሪዎች ሽማግሌዎች ናቸው። ይህ ሽማግሌ የሚለው ቃል በእድሜ ገፋ ያለን በሳል ሰው የሚያመለክት ነው። በአንድ በኩል ይህ አመለካከት ትልቅ ጥበብ ያነገበ ነው። አንድ ሰው ጥበብ ያለው መሪ ለመሆን፣ ልምድ ያስፈልገዋል፤ ብስለትም ያስፈልገዋል። ብዙውን ጊዜ እነዚህ ባሕርያት የሚመጡት ከእድሜ ጋር ተያይዘው ነው። ከሮብዓም ታሪክ ውስጥ እንደምንመለከተው፣ የአዛውንት አማካሪዎች ጥበብ አመራሩ በሕዝብ ላይ እንዳይከብድ የሚጠይቅ ነበር። ወጣቶቹ አማካሪዎች ግን በሥልጣን ላይ ያተኮረ ምክር በመስጠታቸው፣ የእርስ በርስ ውጊያ መቀስቀሱን እንመለከታለን። (1ኛ ነገሥ. 12 አንብብ።)

ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስን ስንመለከት፣ እግዚአብሔር በእድሜ ላይ ላተኮረው አመራር ትኩረት እንደማይሰጥ እንረዳለን። ኢየሱስ አገልግሎቱን ሲጀምር 30 ዓመቱ ነበር። ሐዋርያው ዮሐንስ ከደቀ መዛሙርት አንዱ ሆኖ የተመረጠው ገና በታዳጊ ወጣትነቱ ነበር። ስለዚህ፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አንድ ሰው መሪ የሚሆነው ይህን ያህል እድሜ ሲሆነው ነው የሚባልበት መንገድ የለም። ሁልጊዜም ወሳኙ መንፈሳዊ ባሕርይና ብስለት ነው። በእድሜ መግፋቱ ብቻ አንድን ሰው ጠቢብ ወይም መንፈሳዊ አያደርገውም።

በተለይ በገጠሩ አካባቢ ሰዎች ለመሪነት የሚመረጡት የእድሜን ጉዳይ ባገናዘበ መንገድ ነው። ምእመናን ብዙውን ጊዜ የሚመርጡት በእድሜ ገፋ ያሉትን ሰዎች ነው። ይህ የሚደረገው እነዚህ ሰዎች ለአመራር የሚያስፈልገውን መንፈሳዊ ባሕርይ ወይም ክህሎቶች የማያሳዩ ሆነው ሳለ ነው። በአመዛኙ ሽማግሌ



መሪዎች እግዚአብሔር በስጦታ የካናቸውን ወጣቶች የሚመለከቱት በጥርጣሬ ነው። እነዚህ በሳልና መንፈሳዊ ወጣቶች ወደ መሪነት ደረጃ እንዳይደርሱ ይከላከሏቸዋል።

የሚገርመው በብዙ የከተማ አብያተ ክርስቲያን ሰዎች ለአመራር ያላቸው አስተሳሰብ ከዚህ የተለየ መሆኑ ነው። ወጣቶች ሽማግሌዎችን ይጠራጠራሉ። በእድሜ መግፋት የወቅቱን ሁኔታ እንዳለማወቅ ወይም ዘመናዊ እንዳለመሆን ይቆጠራል። ስለዚህ ወጣቶችን ለአመራር የሚመርጡ ብዙ አብያተ ክርስቲያናት አሉ። እነዚህ ደግሞ እግዚአብሔር መሪዎች በሳልና መልካም መንፈሳዊ ስም ያላቸው እንዲሆኑ የሚፈልግ መሆኑን ይዘነጋሉ። ብዙ ወጣቶች ደግሞ እነዚህን ነገሮች ለማግኘት ገና እድሜያቸው ያልፈቀደላቸው ናቸው። በሳል ባሕርይ ስለማይኖራቸው፣ እነዚህ ወጣት መሪዎች በቤተ ክርስቲያን ላይ ከፍተኛ አደጋ ሊያስከትሉ ይችላሉ።

> 15ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ይህን ዓይነት የአመራርና የአገልግሎት አስተሳሰብ እንዴት እንደ ተመለከትክ ግለጽ። ለ) እግዚአብሔር በእድሜ የገፉትን ሰ ዎች ወደ አመራር የማሳደግ የተለመደ አሠራር የማይከተል ስለ መሆኑ አብራራ። ሐ) ለቤተ ክርስቲያን መሪዎችና ምእመናን ከእድሜ ይልቅ በመንፈሳዊ ባሕርይና ብስለት ላይ ትኩረት ማድረግ አስፈላጊ የሚሆነው ለምንድን ነው?

2. በቤተሰብ ውርስ ወይም በበኩርነት የሚተላለፍ አመራር።

በብዙ ማኅበረሰቦች ውስጥ፣ አመራር ከአባት ወደ በኩር ወንድ ልጁ ይተላለፋል። በመሆኑም፣ ብዙ ሰዎች ለአመራር የሚመርጡት የመሪዎችን ልጆች ነው። በአንድ በኩል፣ ይህ ልንረዳ የምንችለው አስተሳሰብ ነው። ልጆች ወላጆቻቸው ሲመሩ አይተው የተሻለ አመራር ሊሰጡ ይችላሉ ተብሎ ይታሰባል።

ነገር ግን፣ እግዚአብሔር ይህንን በአይሁዶች ሳይቀር የተለመደውን የአመራር ዓይነት እንደ አስፈላጊ ነገር አይመለከተውም። ብዙውን ጊዜ በብሉይ ኪዳን ውስጥ እግዚአብሔር በኩር ያልሆነውን ልጅ ለመሪነት ሲመርጥ እንመለከታለን። ለዚህ ነው እግዚአብሔር ከያዕቆብ ይልቅ ዔሳውን፣ ከታላላቆቹ ይልቅ ዳዊትን

የመረጠው:: እንዲሁም እግዚአብሔር አይሁዶች አመራርን ከአባት ወደ ልጅ የሚያስተላልፉበትን መንገድ አላከበረውም:: ከሙሴ ልጅ ይልቅ ኢያሱ ነበር የተመረጠው:: ሐዋርያት ከሞቱ በኋላ የአንዳቸውም ልጅ የቤተ ክርስቲያን መሪ አልሆነም:: እግዚአብሔር አመራር በአንድ ነገድ ውስጥ እንዲወሰንም አልፈለገም:: ኢያሱና ሙሴ፣ ዳዊትና ሳኦል ከተለያዩ ነገዶች የተገኙ ሰዎች ነበሩ:: አብዛኞቹ ሐዋርያት ብዙ ሰዎች ከሚንቋቸው የፍልስጥኤም ገጠራማ አካባቢዎች የተገኙ ነበሩ:: ለእግዚአብሔር ወሳኙ ነገር የግለሰቡ መንፈሳዊ ባሕርይ እንጂ ቤተሰባዊ ውርሱ አልነበረም:: (1ኛ ሳሙ. 16:7 አንብብ::) በአዲስ ኪዳን ውስጥ የአንድ ቤተሰብ አባላት በመሆናቸው ለተወሰኑ ሰዎች መንፈስ ቅዱስን እንደሚሰጥ የሚያሳይ መረጃ አይገኝም::

ስለሆነም፣ ባህላዊ አስተሳሰባችን ዛሬ መሪዎችን የምንመርጥበት መንገድ እንዳይቆጣጠር መጠንቀቅ አለብን:: ቤተ ክርስቲያን የመሠረቱ ብዙ ሰዎች ሲሞቱ ልጃቸው ቤተ ክርስቲያኒቱን እንዲያስተዳድሩ ይፈልጋሉ:: ወይም ደግሞ ሽማግሌዎች ልጆቻቸውን ወደ መዘምራን ቡድን፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት፣ ወዘተ. . . ለማስገባትና ቦታ ለማስያዝ ይፈልጋሉ:: ለዚህም ዓላማ መሳካት ውሳኔዎችን ያጣምማሉ:: መንፈስ ቅዱስ ለወደደው ሰው የአመራር ስጦታ ከሰጠ፣ እኛም መምረጥ ያለብን እንዲህ ዓይነት ስጦታ ያላቸውን ሰዎች ነው:: ያ ሰው የወንጌላዊ ወይም የቤተ ክርስቲያን መሪ ልጅ ሊሆን ይችላል፤ ሳይሆንም ደግሞ ይችላል:: ስለሆነም፣ አንድን ሰው ለአመራር መምረጥ ያለብን ልቡንና መንፈሳዊ ስጦታዎቹን በመመልከት መሆን አለበት:: ይህ ካልሆነ፣ መንፈስ ቅዱስ በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ ለማከናወን የሚፈልገውን ሥራ እንቃወማለን::

| |
|---|
| 16ኛ ጥያቄ:- ሀ) የቤተ ክርስቲያን መሪ ወይም የወንጌላዊ ልጅ በመሆኑ ምክንያት አንድ ሰው ለአመራር የተመረጠበትን ሁኔታ ግለጽ:: ለ) እንዲህ ዓይነቱ የአመራር ግንዛቤ ቤተ ክርስቲያንን የሚጎዳው እንዴት ነው? |

3. አመራር በትምህርት ላይ የሚደገፍ ነው::



ዛሬ በዓለማችን፣ ትምህርት የአመራር መመዘኛ ሆኗል:: የትምህርት መመዘኛ ባህላዊ የአፍሪካውያንን የአድሜ መስፈርትነት እያስቀረ መጥቷል፡ አንድ ሰው ለአመራር በሚታሰብበት ጊዜ ብዙዎች በቀዳሚነት የሚያነሡት ጥያቄ «ምን ያህል ተምሯል?» የሚል ነው:: አንድ ሰው ዲፕሎማ ወይም ዲግሪ ካለው፣ ጥሩ መሪ ይሆናል ተብሎ ይታሰባል:: ለአገልግሎትም እንዲህ ዓይነቱን አስተሳሰብ እንከተላለን:: የሥነ-መለኮት ትምህርት አንድን ሰው ለአገልግሎት ወይም አመራር ብቁ ያደርገዋል ብለን እናስባለን::

ትምህርት አንድ ሰው በተሻለ ሁኔታ እንዲያገለግል ወይም እንዲመራ የሚያግዝ መሣሪያ መሆኑ ይታወቃል:: ነገር ግን እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን አመራር ትምህርትን እንደ ዋንኛ መስፈርት አይመለከተውም:: እንዲያውም፣ ጳውሎስ እግዚአብሔር በአመዛኙ ሰዎች «ያልተማሩ» ናቸው የሚላቸውን ሰዎች እንደሚጠቀም ይናገራል:: እግዚአብሔር ሥራውን የሚያከናውነው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል እንጂ በሰዎች ጥበብ አለመሆኑን ለዓለም ለማሳየት ይፈልጋል:: (1ኛ ቆሮ. 1:18-31 አንብብ::) መማር የአመራርን ክህሎት እምብዛም አይሰጠንም:: የአገልግሎትን ክህሎት የምናገኘው በማገልገል ነው:: ስለሆነም እግዚአብሔር ሰዎችን ወደ አገልግሎትና አመራር የሚያነሣው በአገልግሎታቸው ልምድና ክህሎት እንዲያገኙ በማድረግና ከታች ወደ ላይ በማንሣት ነው (ማቴ. 25:14-30)::

| |
|---|
| 17ኛ ጥያቄ:- ሀ) ሰዎች መሪዎችን በሚመርጡበት ጊዜ ትምህርትን እንደ ዋንኛ መስፈርት ሲመለከቱ ያየኸው እንዴት ነው? ለ) ትምህርት ለአገልግሎት ወይም አመራር ምን ዓይነት ጥቅሞችን ሲያስገኝ ተመልክተሃል? ሐ) በሳል መንፈሳዊ ባሕርይ የሌላቸው የተማሩ መሪዎች ወይም አገልጋዮች በቤተ ክርስቲያን ላይ ምን ዓይነት ችግሮችን ሲያመጡ ተመልክተሃል? |

4. ሌሎች የአመራር ችሎታቸውን እንዳያሳድጉ በመከላከል መሪዎች የአመራር ስፍራቸውን ይዘው ለመቆየት ይሞክራሉ::

በባህላዊ አስተሳሰብ፣ አንድ ሰው ከመሪነት ኮርቻ ላይ ከወጣ በኋላ፣ ተመልሶ ተራ ምእመን መሆኑ ከባድ ችግር ነው። ይህ መብቱ የነበረውን ክብር እንደ ማጣትና እንደ ሹም ሽር የሚቆጠር ነው። በዚህም ምክንያት፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከመሪነታቸው ላለመውረድ የሚችሉትን ጥረት ሁሉ ያደርጋሉ። ከመሪነት እንዲወርዱ ከተደረገ በኋላ እንኳን፣ ቦታቸውን የያዙትን ሰዎች ለመቆጣጠር በሚያደርጉት ጥረት አሁንም የቤተ ክርስቲያኒቱ መሪዎች መስለው ለመታየት ይሞክራሉ። በቤተ ክርስቲያን መሪነት ሲሠሩ የቆዩና በድምጽ ብልጫ እንዲወርዱ የተ ደረጉ ሰዎች ብዙውን ጊዜ መራራ ስሜት ልባቸው ውስጥ አጎልብተው ወደ ቤተ ክርስቲያን ከመሄድ ይቆጠባሉ።

ይህ በመሪነት የመቀጠል ፍላጎት አሁን ቦታውን የያዙት ሰዎች ላለመልቀቅ የሚቻላቸውን ሁሉ ጥረት እንዲያደርጉ ይገፋፋቸዋል። እግዚአብሔር በስጦታ የባረካቸው ወጣቶች በምእመናን ዘንድ ተ ወዳጅነትን እያገኙ ሲመጡ ከተመለከቱ፣ ያ ሰው ወደ መሪነት እንዳይደርስ የሚችሉትን ማስናከያ ሁሉ ያደርጋሉ። ስጦታ ያላቸውን ሰዎች ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጅ አይልኩም። ይልቁንም፣ ተመልሶ ቢመጣም መሪነቴን አያናጋውም ብለው የሚያስቡትን ደካማ ያለ ሰው ይልካሉ። በስጦታ የተካነውን ግለሰብ ስም የሚያጠፋ የፈጠራ ወሬ በማስራጨት ወይም የአገልግሎት በሮችን ጥርቅም አድርገው በመዝጋት ተስፋ ቆርጦ ቤተ ክርስቲያኒቱን ለቅቆ እንዲሄድ የሚያደርጉም እንዳሉ ይታወቃል።

እንዲህ ዓይነቱ ሰው ለራሱ መንግሥት እንጂ ለእግዚአብሔር መንግሥት ከሁሉም የላቀውን ነገር እንደማይፈልግ ግልጽ ነው። ከክርስቶስ መንግሥት ይልቅ የሚያስበው የራሱ ክብር ነው። ከዚህ ይልቅ ክርስቶስ እውቅና እያገኘ ሲመጣ አይቶ «እርሱ ሊልቅ እኔ ግን ላንስ ያስፈልጋል» ያለውን የመጥምቁ ዮሐንስን አመለካከት መያዙ ምንኛ ጠቃሚ ነው (ዮሐ. 3:27-30)።

*18ኛ ጥያቄ:- ሀ) እንዲህ ዓይነት ባህላዊ የአመራር ግንዛቤ ቤተ ክርስቲያንን ሲጎዳ የተመለከትክበትን ሁኔታ ግለጽ። ለ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች መሪነታችንን ይነጥቁናል በሚል ፍርሃት ስጦታ ያላቸውን*



*ወጣቶች ሲገፉ የተመለከትከው እንዴት ነው? ሐ) የቤተ ክርስቲያን መሪ ዎች ከቦታቸው ለመነሣት ባለመፈለጋቸው ምክንያት የሚፈጠረውን ችግር ለመፍታት ምን ቢደረግ ጥሩ ነው ትላለህ?*

5. መሪዎች የሌሎች መሪዎችን ድክመት በማጉላት የራሳቸውን የአመራር ችሎታ ለማስየት ይሞክራሉ።

አንድ ሰው ጥሩ መሪ መሆኑን የሚያሳየው እንዴት ነው? በአንዳንድ ባህሎች መሪዎች ጥሩነታቸውን የሚያስዩት የበፊት መሪዎችን ስም በማጉደፍና ያከናወኗቸው ተግባራት በሙሉ አርባና-ቢስ መሆናቸውን በመግለጽ ነው። ለዚህም ነው አንዳንድ መንግሥታት የቀድሞዎቹ የመንግሥት ባለሥልጣናት ምንም ነገር ለአገራቸው እንዳልሠሩ በመግለጽ የሚተቿቸው። የዚህ ዓይነቱ አመለካከት ቤተ ክርስቲያን ውስጥም ይታያል። አዳዲስ መሪዎች ወይም አገልጋዮች ሲመረጡ፣ ከእነርሱ በፊት ያገለገሉትን ሰዎች ስም በማጥፋት የራሳቸውን ጥሩነት ለማሳየት ይፈልጋሉ። ወይም ደግሞ የበፊት አገልጋዮችና መሪዎች ያደረጓቸውን ስምምነቶችና ዕ ቅዶች ሁሉ ይሰርዛሉ።

ይህ እግዚአብሔር በታሪክ ሁሉ ሕዝቡን እንደሚቆጣጠር አለማመናችንን ያሳያል። አንድን ሰው ከአመራር ስፍራ ላይ የሚያስቀምጠው እግዚአብሔር ነው ብለን ካመንን (ሮሜ 13:1-2 አንብብ)፣ የበፊቱን መሪ ሥራዎች በሙሉ እርባና-ቢስ ናቸው ማለቱ እግዚአብሔር ግለሰቡን ከመሪነት ቦታ ላይ ሲያስቀምጥ ምንም አያውቅም ነበር እንደ ማለት ነው። ይህ በርግጥ ግለሰቡን ሳይሆን የእግዚአብሔርን ሥራ ለመቃወም የሚደረግ ጥረት ነው። የአንድን ሰው ሥራ ለማበላሸት መሞከር፣ ግለሰቡን በዚያ ቦታ ላይ ያስቀመጠውን የእግዚአብሔርን ሥራ ለማበላሸት እንደ መሞከር ነው። እግዚአብሔር ከመሪዎቹ የፈለገው ይህንን አይደለም። እግዚአብሔር የበፊት መሪዎችንና አገልጋዮችን ለሥራቸው ይጠይቃቸዋል። እኛንም ለሥራችን ይጠይቀናል። ፍላጎታችን መሆን ያለበት ጠንካራ ጎኖችን በመጠበቅና ድክመት ያለባቸውን አካባቢዎች በማስደግ መንፈስ ቅዱስ የጀመረውን ተግባር መቀጠል ነው።

6. መሪዎች ስጦታ ያላቸውን ሰዎች ለውጤታማ አገልግሎት እንዳያሳድጉ ሁሉንም ሰው በእኩል ደረጃ መመልከት አለባችሁ የሚለው ባህላዊ አመለካከት ተጽዕኖ ያሳድርባቸዋል::

በአንዳንድ ባህሎች መሪዎች በሰዎች መካከል ልዩነት ማሳየት እንደሌለባቸው ይታመናል:: ስጦታ ያለውና የሌለው፣ ተግቶ የሚሠራውና የማይሠራው ሁሉ እኩል መታየት አለበት:: ይህ አመለካከት አንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ ስጦታ ያለውን ወጣት መርጦ በመወሰድና ከእርሱ ጋር በቂ ጊዜ በማሳለፍ ለእግዚአብሔር ውጤታማ አገልግሎት እንዳያበረክት ያደርገዋል:: አንድን ሰው መርጠን ከእርሱ ጋር በቂ ጊዜ ብናሳልፍ፣ ሰዎች በእኛ ላይ ከመናደዳቸውም በላይ ልዩ ትኩረት ባገኘውም ሰው ይቀናሉ::

አንድ ሰው የቤተሰባችን ወይም የጎሳችን አባል በመሆኑ ላይ ተመሥርቶ አድልዎ መፈጸሙ በርግጥ ስሕተት ነው:: ነገር ግን መሪዎች መንፈሳዊ ሰዎችን ወደ አመራር እንዲያሳድጉ መጽሐፍ ቅዱስ ያበረታታል:: ከብዙ ሰዎች መሐል ሙሴ ኢያሱን መርጦ ረዳቱ አድርጎታል:: በአመራርም አሠልጥኖታል:: ከብዙ ደቀ መዛሙርት መካከል ክርስቶስ 12ቱ ሐዋርያቱ እንዲሆኑ መርጧቸዋል:: ከ12ቱ መካከል ሦስቱ (ጴጥሮስ፣ ያዕቆብና ዮሐንስ) ከእርሱ ጋር ልዩ ጊዜ እንዲያሳልፉ አድርጓል:: ከሦስቱ መካከል ከሐዋርያው ዮሐንስ ጋር ልዩ ግንኙነት ነበረው:: መጠሪያውም «ኢየሱስ ይወደው የነበረ ደቀ መዝሙር» የሚል ነበር (ዮሐ. 13:23):: እግዚአብሔር ሁሉንም ሰው እኩል እንደማያስተናግድ ግልጽ ነው:: ለሰዎች የተለያየ ደረጃ ያላቸውን ስጦታዎች ይሰጣል:: አንዱ ከሌላው በተሻለ ሁኔታ የሚሰብከውም ለዚሁ ነው:: ስለዚህ፣ ሁሉም ሰው እኩል መታየት አለበት የሚለው መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተሳሰብ አይደለም::

መሪዎችን በእግዚአብሔር መንገድ ማዘጋጀት ካለብን፣ ይህንን ሁሉም ሰው እኩል መታየት አለበት የሚለውን ባህላዊ አስተሳሰብ መስበር አለብን:: የመጪውን ትውልድ መሪዎች ለማሠልጠን ከመረጥን፣ እግዚአብሔር መንፈሳዊ ስጦታዎችን የሰጣቸውንና በመንፈሳዊ ባሕርይ የማደግ ፍላጎት ያላቸውን ሰዎች መፈለግ አለብን:: ከእነርሱ ጋር የቅርብ ግንኙነት በማድረግ ውጤታማ አገልግሎት እንዲሰጡና መንፈሳዊ ባሕርይ እንዲኖራቸው ጥረት በምናደርግበት ጊዜ፣ የመጭውን ትውልድ መሪዎች ለማሳደግ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር አብረን እየሠራን መሆናችን መታወቅ አለበት:: በዚህ ጊዜ ልክ እንደ ጳውሎስ አገልግሎቱን ይዘው የሚቀጥሉ የራሳችን ጢሞቴዎሶችና ሲላሶች ይኖሩናል ማለት ነው:: ባህላችን ይህንን የማይደግፍ ከሆነ፣ ባህላችን ትክክል ስላልሆነ እርሱን ትተን የእግዚአብሔርን መንገድ መከተል አለብን::

19ኛ ጥያቄ:- ሀ) በሰዎች መካከል አድልዎ የማሳየት ፍርሃት መሪዎች ስጦታ ያላቸውን ወጣቶች በአመራር እንዳያሳድጉ ተጽዕኖ ያሳደረባቸው እንዴት ነው? ለ) መሪዎች ስጦታ ያላቸውን ወጣቶች ለአገልግሎት በሚያሳድጉበት ጊዜ ከሰዎች የሚደርስባቸውን ቅንዓት እንዴት ማስወገድ ይቻላል?

## በእግዚአብሔር መንገድ ለአገልግሎት የተዘጋጁ መሪዎች በማይመረጡበት ጊዜ ቤተ ክርስቲያን ትጎዳለች

እግዚአብሔር አንድን ሰው ወደ ከፍተኛ የመሪነት ደረጃ ማንሣቱ ሰዎች አንድን ሰው ለከፍተኛ አመራር ደረጃ ከሚያደርሱበት መንገድ የተለየ ነው:: እግዚአብሔር ሰዎች የእርሱን የቤተ ክርስቲያን አመራር ደረጃ ያሳሟሉትን ሰዎች እንዲመርጡ ይፈቅድላቸዋል:: ሰዎችን የጎሳችን አባላት፣ የተማሩ ወይም በማኅበረሰባችን ውስጥ ከፍተኛ ታዋቂነት ያላቸው በመሆናቸው ምክንያት ለቤተ ክርስቲያን አመራር ልንመርጥ እንችላለን:: ነገር ግን ሰዎቹን እግዚአብሔር በራሱ መንገድ ለአገልግሎቱ ካላዘጋጃቸው፣ እነዚህ ሰዎች የእግዚአብሔርን መንግሥት እድገት ያደናቅፋሉ:: የሚመሩት እንደ ዓለም እንጂ እንደ ክርስቶስ አይደለም:: ይህ ደግሞ ቤተ ክርስቲያኖቻችን በጸብ፣ በቅንዓት፣ በጎሰኝነትና በትዕቢት እንዲዳከሙ ያደርጋል:: እግዚአብሔር የምንፈልገውን ዓይነት ቤተ ክርስቲያን ልንሆን የምንችለው እግዚአብሔር የሚፈልገውን ዓይነት መሪዎችን የማዘጋጀት መንገድ ከተረዳንና በዚሁ መንገድ ወንዶችንና ሴቶችን ለአገልግሎት የምንመርጥ ከሆነ ብቻ ነው::

የቤተ ክርስቲያን ምእመናን በተሳሳቱ ልባዊ ፍላጎቶች ተነሣሥተው ሰዎችን ለከፍተኛ አመራር ደረጃ ሊመርጡ የሚችሉት ለጊዜው ብቻ ነው። ነገር ግን የዚህ ዓይነቱ መሪ እንደ ባህር ዛፍ ቅጠል ነው። አመራራቸው ለጊዜው ይማሟቅና ወዲያው ይከስማል። እንዲህ ዓይነት መሪዎች በቤተ ክርስቲያን ላይ ብዙ ችግሮችን ስለሚያመጡ፣ ወዲያው ይቀየራሉ። ነገር ግን ባለማቋረጥ መንፈሳዊነትን፣ የአገልጋይነትን ልብ፣ እንዲሁም ታማኝነትን የሚያሳዩ ሰዎች በሥልጣን እያደጉ ይሄዳሉ። ስብዙ ዘመንም ለእግዚአብሔር ክብር ያገለግላሉ።

| |
|---|
| 20ኛ ጥያቄ፡- ሀ) መንፈሳዊ ባሕርይ ወይም በቂ የአመራር ክህሎቶች የሌሉት ሰው በሚመራበት ጊዜ በቤተ ክርስቲያናችሁ ምን ችግር ተፈጠረ? ለ) መንፈሳዊና ክህሎት ያለው መሪ በሚመራበት ጊዜ የተከሰቱትን ነገሮች ግለጽ። |

## እግዚአብሔር የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን እንዴት እንደሚያዘጋጅ

የምእመናን መንፈሳዊ እድገትና የአገልግሎት ውጤታማነት የሚወሰነው በቀዳሚነት በቤተ ክርስቲያን መሪዎች ነው። አብያተ ክርስቲያናት እምብዛም ከመሪዎቻቸው ችሎታ በላይ አያድጉም። መሪዎችን ለቤተ ክርስቲያን ማዘጋጀትን በተመለከተ ወሳኙ ጉዳይ እግዚአብሔር ለክብሩ የሚጠቀምባቸው ሰዎች አድርጎ ማሳደግ ነው። ሰዎች በግል ሲያድጉ፣ በአመራር ችሎታቸውም ያድጋሉ።

በዘመናችን፣ ለአመራር ትልቁ መሰፈርት የሆነ መደበኛ ሥልጠና ማግኘት ነው ብለን እናስባለን። ስለሆነም ሰዎች መሪዎች እንዲሆኑልን ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት እንልካቸዋለን። ነገር ግን፣ ትምህርት ብቻውን አንድ ሰው ጥሩ የቤተ ክርስቲያን መሪ እንዲሆን አያበቃውም። ብዙውን ጊዜ እግዚአብሔር አንድን መሪ የሚያዘጋጀው፣ ሀ) በሕይወቱ ውስጥ በሚያጋጥማቸው ሁኔታዎች አማካኝነት በሚያከናውናቸው ነገሮች፣ ለ) በሚወስዳቸው የግል ምርጫዎች፣ ሐ) ለእግዚአብሔር አገልግሎት ባለው አመለካከት፣ እና መ) በሌሎች አማካኝነት እግዚአብሔር በሚሰጠው ትምህርት ውህደት ነው። የቤተ ክርስቲያን ራስ



የሆነው ክርስቶስ በግለሰቦች ሕይወት ውስጥ በመሥራት ሕዝቡን እንዲመሩ ያዘጋጃቸዋል። ነገር ግን፣ አንድ ሰው እግዚአብሔርን ለማገልገል ብሎ እንዲቀየር አያስገድደውም። ግለሰቡ መንፈስ ቅዱስ የሚያደርጋቸውን ነገሮች በማጤን ከእግዚአብሔር ሥራ ጋር መተባበር አለበት። ስለሆነም፣ የመንፈሳዊ አገልግሎት ዝግጅት የእግዚአብሔር ምርጫና ዝግጅት ከግለሰቡ ስምምነት ጋር የሚዋሃድ ነው።

1. ሰዎች ልጆቹን እንዲመሩ ለማዘጋጀት የእግዚአብሔር ድርሻ።

ሀ. ለአንዳንድ ሰዎች ተፈጥሯዊ የመምራት ችሎታ ይሰጣል። ዳዊት በእናቱ ማኅፀን የሠራው እግዚአብሔር መሆኑን ተናግሯል (መዝ. 139፡13)። እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ ግለሰብ ልዩ አካልና ባሕርይ መፍጠር ብቻ ሳይሆን፣ ለእያንዳንዱ ሰው ልዩ የተፈጥሮ ስጦታዎችንም ይሰጣል። አንዳንድ ሰዎች ገና ከወጣትነታቸው ጀምሮ ከፍተኛ የመሪነት ችሎታ አላቸው። በትናንሽ ልጆች መካከል ብዙውን ጊዜ አንዱ ልጅ ሌሎች እርሱ የሚፈልጉትን ነገር እንዲያደርጉ የሚመራበትን ሁኔታ እናያለን። አስተዋይ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከወጣቶቻቸው መካከል ማን እንዲህ ዓይነት የተፈጥሮ ስጦታ እንዳለው ማጤን አለባቸው። ወጣቶች አሳቦችንና ምሪት ለማግኘት ወደ ማን ነው የሚሄዱት? እነዚህ እግዚአብሔር ስጦታ የሰጣቸው ልጆች ናቸው። ከዚያም በቤተ ክርስቲያን መሪዎች እነዚህ ወጣቶች በአመራር ችሎታቸው የሚያድጉባቸውን መንገዶች መፈለግ አለባቸው። ምንም እንኳን በተፈጥሮ የመሪነት ችሎታ ያላቸው ሰዎች የተወሰኑ ቢሆኑም፣ ሁሉም ሰዎች በተወሰኑ የሕይወት ክፍሎቻቸው መሪዎች ናቸውና በተሻለ ሁኔታ የአመራርን ተግባራት እንዲያከናውኑ ሊማሩ ይችላሉ። አንድ ደራሲ እንዳለው፣ «አብዛኞቹ መሪዎች በሰዎች ዓይን ፊት ተራ ሰዎች ነበሩ።»

ለ. እግዚአብሔር ብዙውን ጊዜ ሰዎችን በመሪነት ለማሳደግ ቤተሰብን ይጠቀማል። እግዚአብሔር ልጆቻቸው እግዚአብሔርን እንዲከተሉና እርሱን በማገልገል በዓለም ላይ ለውጥ እንዲያመጡ በሚያበረታቱቸው መንፈሳዊ ወላጆቻቸው ይጠቀማል። ወላጆች

ልጆቻቸው እግዚአብሔርን በማዳመጥ አንድ ቀን ሕዝቡን እንዲመሩ ይመክሯቸዋል። ይህንን በሳሙኤል ሕይወት ውስጥ እንመለከታለን። እናቱና በኋላም ዔሊ ሳሙኤል ለእግዚአብሔር ድምጽ ንቁ እንዲሆን አስተምረውታል (1ኛ ሳሙ. 1-3)። በኋላም ሳሙኤል ከነገሥታት ዘመን በፊት እስራኤልን ከገዙት ታላላቅ መሳፍንት አንዱ እንዲሆን አስችሎታል። እግዚአብሔር ልጆቻቸው እርሱን እንዲያገለግሉ የሚያበረታቱትን ወላጆች እንዴት እንደሚጠቀም መመልከቱ አስደናቂ ነገር ነው። የብዙ ወንጌላውያንና መጋቢያን ልጆች ሕይወታቸውን ለሙሉ ጊዜ አገልግሎት ሲሰጡ እናያለን። ወላጆች ልጆቻቸው ሕይወታቸውን ለሌሎች መሥዋዕት እንዲያደርጉ፣ ለእንግዶች ቸርነትን እንዲያሳዩ፣ ሥልጣንና ክብር ሳይፈልጉ እንዲያገለግሉ፣ ወዘተ. . . ያስተምሯቸዋል። ይሁን እንጂ፣ ብዙ ወላጆች የእነርሱ ሚና ልጆቻቸው ውጤታማ መሪዎች እንዲሆኑ በማድረጉ በኩል ምን ያህል ከፍተኛ እንደ ሆነ አይገነዘቡም። ብዙውን ጊዜ ልጆቻችን ትናንሽ ናቸው ብለን በማሰብ ሌሎች ትልልቅ ሰዎችን በማገልገሉ ላይ እናተኩራለን። ይህም ልጆቻችንን ለመንፈሳዊ አገልግሎት እንዳናዘጋጃቸው ያደርገናል።

21ኛ ጥያቄ:- ሀ) መንፈሳዊ ወላጆች ልጆቻቸው እግዚአብሔርን በመሥዋዕትነት እንዲያገለግሉ በማድረግ አዎንታዊ ተጽዕኖ ሊያሳድሩባቸው የሚችሉት እንዴት ነው? ይህ ትምህርት በልጆች ላይ የሚያመጣው ተጽዕኖ ምንድን ነው? ለ) ብዙ ወላጆች ሆን ብለው ልጆቻቸው እግዚአብሔርን በታማኝነት እንዲያገለግሉ የማያበረታቱት ለምን ይመስልሃል? ሐ) ዛሬ ብዙ ክርስቲያኖች ልጆቻቸው ወንጌላዊ ወይም መጋቢ እንዳይሆኑና ዳሩ ግን ከፍተኛ ዓለማዊ ትምህርት አግኝተው ጥሩ ሥራ እንዲይዙ የሚፈልጉት ለምንድን ነው? መ) ይህ ወላጆች እግዚአብሔርን ስለ ማገልገል ምን ዓይነት አመለካከት እንዳላቸው ያሳያል?

ሐ. እግዚአብሔር ሰዎች በብስለት እንዲያድጉ ለማገዝ በሕይወት ውስጥ የተማሯቸውን ትምህርቶች ይጠቀማል። በተለይም አስቸጋሪ ጊዜያትን በመጠቀም የሰውን ባሕርይ ይቀርጻል። አንድ መሪ እንደ ጻፈው፣ «እግዚአብሔር አንድን ሰው በጥልቀት ከመጉዳቱ በፊት እምብዛም አይጠቀምበትም።» ባሕርይ የሚገነባው



በትግል ሲሆን፣ የሚገለጸውም በፈተና ነው። እነዚህ ፈተናዎች ደግሞ ውድቀትን ወይም ቀውስን የሚያመለክቱ ወይም የግል ችግሮችን የሚያሳዩ ሊሆኑ ይችላሉ። (ለምሳሌ፣ ሙሴ አጥርቶ የመናገር ችግር ነበረበት፣ ጳውሎስ ደግሞ የሥጋ መውጊያ ነበረበት)። እነዚህ ችግሮች አብዛኞቹ ሰዎች ዋጋ የለኝም ብለው እንዲያስቡ ወይም መራራ እንዲሆኑና እግዚአብሔርን የማገልገል ፍላጎታቸው እንዲከስም ሊያደርጉ ይችላሉ። ነገር ግን፣ ሰዎች እነዚህን ችግሮች በመንፈሳዊ መንገዶች ቢይዟቸው፣ እግዚአብሔር እነዚህን ነገሮች በመጠቀም ውጤታማ መሪዎች እንዲሆኑ ያስችላቸዋል። እግዚአብሐር ሽንፈት የመሰላቸውን ሁኔታ የሚማሩበት ገጠመኝ አድርጎ ሲለውጥ ይመለከቱና፣ ደካሞች በሚሆኑበት ጊዜ በእግዚአብሔር ኃይል ላይ ይደገፋሉ (2ኛ ቆሮ. 12:7-10)። እግዚአብሔር ለአንድ ሰው ያዘጋጀው አገልግሎት ትልቅ በሚሆንበት ጊዜ ከፍተኛ ኃላፊነት ለመስጠት ብዙ ያስጠብቀዋል። እግዚአብሔር የመሪውን ባሕርይ በመቅረጽ ብዙ ጊዜያትን ያሳልፋል። እግዚአብሔር አንድን ሰው በመሪነት ለመሾም አይቸኩልም። ሙሴ እስራኤላውያንን ለ40 ዓመታት የመምራት ዕድል ከማግኘቱ በፊት ለ80 ዓመታት መጠበቅ ነበረበት። ዳዊት የእስራኤል ንጉሥ ለመሆን ከተቀባ ከ20 ዓመታት በኋላ ነበር ንግሥናውን የተረከበው።

22ኛ ጥያቄ:- ሀ) አንድ የምታውቀው ውጤታማ መሪ እንዴት በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ እንዳለፈና ይህ ደግሞ እንዴት የተሻለ መሪ እንዲሆን እንዳስቻለው ግለጽ። ለ) አንዳንድ ሰዎች ችግር በሚደርስባቸው ጊዜ ለምን መራራ እንደሚሆኑና ሌሎች ደግሞ ይህንን አጋጣሚ ተጠቅመው ለምን በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንደሚያድጉ ግለጽ። ሐ) በሕይወታቸው ውስጥ የሚከሰተውን ውጤት የሚወስነው አመለካከት ምንድን ነው?

መ. እግዚአብሔር እያንዳንዱ አማኝ እርሱንና ቤተ ክርስቲያኑን እንዲያገለግል መንፈሳዊ ስጦታ ይሰጠዋል። ከመንፈሳዊ ስጦታዎች አንዳንዶቹ የአገልግሎት ስጦታዎች ናቸው። ለአንዳንዶች የወንጌል ሰባኪነትን፣ ለሌሎች የማስተማርን፣ ለሌሎች የማስተዳደርን፣ ወዘተ. . . ስጦታዎች ይሰጣል (ሮሜ 12:3-8፤ 1ኛ ቆሮ. 12:27-28፤ ኤፌ. 4:11-13)። በቤተ ክርስቲያን

መሪዎች እገዛ ስጦታዎቹን ማወቅና ማጎልበት የእያንዳንዱ አማኝ ኃላፊነት ነው።

ሐ. እግዚአብሔር ግለሰቡን ለማሳደግና በታማኝነት ለማገልገል ፈቃደኛ መሆኑን ለመፈተን የአገልግሎት ዕድሎችን ደረጃ በደረጃ ያሳድግለታል። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የምናደርገው ማንኛውም ነገር እግዚአብሔር የሰጠን የአገልግሎት ዕድል ተደርጎ መታየት አለበት። ለኮንፍረንስ እንጨት እንድንፈልጥ ነው የተጠየቅነው? ይህ እግዚአብሔር በደስታ መሥራታችንን ለመፈተን የሚሰጠን ዕድል ነው። መባ እንድንሰበስብ ተጠይቀናል? ይህ እግዚአብሔር እንድናድግ ለማገዝ የሚሰጠን የአገልግሎት ዕድል ነው። በልጆች የሰንበት ትምህርት ቤት ውስጥ እንድናስተምር ተጠይቀናል? ይህ እግዚአብሔር እርሱን እንዴት እንደምናገለግልና ይህንኑ ተግባር በታማኝነት መወጣታችንን ለመመልከት የሰጠን የአገልግሎት ዕድል ነው። እግዚአብሔር የመረጣቸውን ሰዎች ለአገልግሎት ለመሾም ቀስ በቀስ በአገልግሎት ሂደት ውስጥ ያሳድጋቸዋል።

| |
|---|
| 23ኛ ጥያቄ:- እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ ላለህ አገልግሎት እንዴት እንዳዘጋጀህ አስብ። ሀ) እግዚአብሔር የሰጠህንና ለአገልግሎትህ የሚጠቅሙህን ባሕርያት ዘርዝር። ለ) አንተን ለአገልግሎት ለማዘጋጀት እግዚአብሔር እንዴት ወላጆችህን እንደ ተጠቀመ ግለጽ። ሐ) አጋጣሚዎችንስ ለዚሁ ዓላማ የተጠቀመው እንዴት ነበር? መ) እግዚአብሔር እንድታገለግለው ምን ዓይነት መንፈሳዊ ስጦታዎችን ሰጥቶሃል? ካላወቅክ፣ አንዳንድ ጓደኞችህ ምን ዓይነት መንፈሳዊ ስጦታዎችን በአንተ ላይ እንዳዩ እንዲነግሩህ ጠይቃቸው። ሠ) እግዚአብሔር በምን ምን አገልግሎቶች እንድትሳተፍ ዕድል ሰጥቶሃል? እያንዳንዱ አገልግሎት አሁን ወዳለህበት ደረጃ ለማደግ እንዴት አስተዋጽኦ እንዳደረገልህ ግለጽ። |

**2. ለአገልግሎት ለመዘጋጀት የግለሰቡ ኃላፊነት።**

በዋናነት ሰውን መርጦ ለአገልግሎት የሚያዘጋጀው እግዚአብሔር ነው። የቤተ ክርስቲያኑ ራስ የሆነው እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያኑን እንዲመራለት የፈለገውን ሰው የመምረጥ መብት አለው። እግዚአብሔር ወደ ብስለት እንድናድግና እንድናገለግለው



ለማድረግ የተለያዩ ሁኔታዎችን ይጠቀማል። ነገር ግን እግዚአብሔር በመሣሪያነት እንዲጠቀምብን ራሳችንን የማዘጋጀት ኃላፊነት አለብን።

ሀ. እግዚአብሔር ለአንድ ሰው ዕድሉን በሚሰጥበት ጊዜ፣ ችሎታዎቹን ለማሳደግ ዓለማዊ ትምህርትን መከታተል አለበት። የማታ ትምህርት በብዙ ቦታዎች ስለሚሰጥ፣ ሰዎች ተጨማሪ ትምህርት ለማግኘት ሊጠቀሙበት ይችላሉ። እግዚአብሔር የተማረን ሰው ሊጠቀም ይችላል። ነገር ግን በዓለማዊ ትምህርት ላይ ከመጠን በላይ መተማመን የለብንም። እግዚአብሔር መንፈሳዊ ጥበብ ከዓለማዊ ጥበብ እንደሚልቅ ለማሳየት ብዙ ጊዜ ያልተማሩትን ሰዎች ሲጠቀም እንመለከታለን። (1ኛ ቆሮ. 1:18-19 አንብብ።) ይሁን እንጂ፣ ትምህርት እግዚአብሔርን ለማገልገል ጠቃሚ የሆኑትን ክህሎቶች እንደሚያስገኝ አይካድም። (ማስታወሻ: - አንድ ሰው ትምህርትን የሚመለከተው የምስክር ወረቀት የማግኛ ቦታ አድርጎ ከሆነ፣ የትምህርትን ዓላማ ስቷል ማለት ነው። የትምህርት ዓላማ በሕይወትና በትምህርት የሚጠቅሙንን ክህሎቶች ማስጨበጥ እንጂ፣ አንዳች «ብጣሽ ወረቀት» ይዞ መምጣት አይደለም። ብዙ ተማሪዎች እግዚአብሔርን ለማገልገል የሚያስችሉትን ክህሎቶች ከማሳደግ ይልቅ የምስክር ወረቀቱን በማግኘቱ ላይ ስለሚያተኩሩ፣ እግዚአብሔር የሚሰጣቸውን ዕድል ሳይጠቀሙ ይቀራሉ።) በትምህርት አማካኝነት የማንበብ ክህሎት በማግኘታችን መጽሐፍ ቅዱስንና ሌሎች መጻሕፍትን በማንበብ መንፈሳዊ እውቀትን እናገኛለን። በቂ የሂሳብ እውቀት ሲኖረን፣ የቤተ ክርስቲያንን ገንዘብ በአግባቡ ለማስተዳደር እንችላለን። መልክዓ ምድርን በሚገባ ስናውቅ፣ እግዚአብሔር በዓለምና በአገራችን ምን እያደረገ እንዳለ፣ ይህ ደግሞ በቤተ ክርስቲያናችን ላይ ምን ዓይነት ተጽዕኖ እንደሚያመጣ እንረዳለን።

ለ. እግዚአብሔር ለሚሰጠን አገልግሎት መንፈሳዊ ባሕርይንና ብስለትን በመመዘኛነት ይጠይቃል። (ማስታወሻ:- ይህንን የመንፈሳዊ መሪ ባሕርያት በሚለው የዚህ መጽሐፍ የመጀመሪያ ክፍል ውስጥ አጥንተናል።) አንድ ሰው እግዘአብሔር

እንዲጠቀምበት ክፈለን፣ በመንፈሳዊ ብስለት እያደገ መሆኑ (በጸሎት እና በእግዚአብሔር ቃል ጥናት አማካኝነት) እና መንፈሳዊ ባሕርይ እያሳየ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት:: እግዚአብሔር ብዙውን ጊዜ የምንናገረውን (የጸሎት ለዎች ወይም ቃሉን የምናውቅ ነን የምንል) ዓይነት ሰው መሆናችንን ለመፈተን በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ እንድናልፍ ወይም ፈተናን እንድንጋፈጥ ያደርጋል:: በዚህም በባሕርይ እያደግን መሆናችንን ያረጋግጣል:: እርሱን በሚያስከብር መንገድ ምላሽ ክሰጠን (ለምሳሌ፣ ዳን. 1:8-21)፣ አገልግሎታችንን ያሳድጋል:: እግዚአብሔር ብዙውን ጊዜ ሰውን ለመጠቀም ወይም ሳለመጠቀም በሦስት የባሕርይ ክፍሎች ላይ ትኩረት ያደርጋል:-

*1) ታማኝነት:-* ይህ እንዲህ ዓይነት ሰው ነኝ የምንለውን ሆነን መገኘታችንን የሚያሳይ ነው:: ከሰዎች ጋር ስንሆንና ብቻችንን ስንሆን፣ የተለያዩ ነገሮችን ይሆን የምናደርገው? ቢመችም ባይመችም፣ ሁልጊዜ ትእዛዛቱን እንጠብቃለን? በገንዘብ እያያዛችን፣ ቃላችንን በመጠበቅ (ከሰዎች ጋር ያለንን ቀጠሮ በማክበር ጭምር)፣ ለቤተ ክርስቲያን ቅጾችን በመሙላት፣ ወዘተ. . . ታማኞች ነን:: ቃላችንን በጥንቃቄ የማንጠብቅ፣ በገንዘብ ጉዳይ ጥብቅ ካልሆንን እግዚአብሔር ሕዝቡን ለመምራት አይታመንብንም:: ትሑት መሆናችንን ያያል:: ማንም አያየንም ብለን በምናስብበት ጊዜ ምን ዓይነት ባሕርይ እንደምናሳይ ይመለከታል:: በንጹሕ ልብ እርሱን ለማገልገል መፈለጋችንን ወይም በአገልግሎቱ ስም ጥቅምና ክብር ለማግኘት መፈለጋችንን በማጤን የወንጌላዊነት ወይም የእረኝነት ጥሪያችንን ይመረምራል:: በታማኝነት መኖርን እስክንማር ድረስ እግዚአብሔር ወደ ታላቅ የመሪነት ደረጃ አያሳድገንም::

*2) ታዛዥነት:-* መሪዎች እግዚአብሔርን በመስማትና ፈቃዱን በማወቅ የታዛዥነት ምላሽ መስጠታቸው ወሳኝ ነው:: እግዚአብሔር ሲናገረን መስማታችንን ይፈትናል:: ከዚያም በአስቸጋሪ ጊዜያት ሳይቀር እርሱን ለመታዘዝ መፍቀዳችንን ያያል:: በእኛ ላይ በኃላፊነት ያስቀመጣቸውን ሰዎች



መታዘዛችንንም ያያል:: ብዙውን ጊዜ ከበላያችን ያለው ሰው ጥሩ ሲሆን፣ ጥሩ ደመወዝ ሲከፈለን፣ ወይም የምናከናውነው ሥራ በሰዎች ዘንድ ተቀባይነት ሲያገኝና በባህሉም ዘንድ ተወዳጅ በሚሆንበት ጊዜ መታዘዙ ቀላል ነው:: ነገር ግን አለቃችን ደግ ሳይሆን ሲቀር፣ ለጥረታችን ምንም ዓይነት ደመወዝ ሳናገኝ፣ ወይም ሰዎች እግዚአብሔር የሚያዝዛቸውን ነገር ሳይወዱት ሲቀሩና ይህ በባህላችን ሰዎች የማያደርጉት ሲሆንም እንታዘዛለን? በዚህ ጊዜ የእግዚአብሔር ባሪያዎች በመሆን ፈቃዱን እንፈጽማለን ወይስ የሌሎች ሰዎች ፍላጎት ባሪያዎች እንሆናለን? (ገላ. 1:10):: በሥልጣን ላይ ያሉት ሰዎች እግዚአብሔር የሚፈልገውን ተግባር እያከናወኑ አይደሉም የሚል አስተሳሰብ በሚኖረን ጊዜ ለእነርሱ ታማኞች በመሆን እንጸልይላቸዋለን፣ ወይስ በሐሜት ስማቸውን እናጠፋለን? እግዚአብሔር ሌሎችን በምናዝበት ደረጃ ላይ የሚያስቀምጠን መጀመሪያ እርሱን ስንታዘዝ ነው::

*3) እውነትን ማወቅ:-* በእግዚአብሔር ፊት እውነት የሆነውን ነገር ከቃሉ እንብበን ሰማወቅ እንችላለን? ቃሉን በማጥናት ሕይወታችንን በቃሉ ላይ ለመመሥረት ራሳችንን ሰጥተናል? በእግዚአብሔር ቃል እውቀት ለማደግ የምንሰጠው ጊዜ በጣም ትንሽ ነው? ለእውነቱ ግድየለሽ በመሆን በሰላም አብረን ለመኖር ስንል ሌሎች ሰዎች ከሚሉት አሳብ ጋር እንስማማለን? የሐሰት ትምህርቶችን ሳንጋፈጥ ወደ ቤተ ክርስቲያናችን እንዲመጡ እናደርጋለን? እግዚአብሔር ለእውነቱ ምን ያህል ራሳችንን የሰጠን መሆናችንን በሚያጣራበት ጊዜ መንፈሳዊ መሪዎች እውነትን ለሌሎች የሚያስተምሩ ሆነው ይገኛሉ::

24ኛ ጥያቄ:- ሕይወትህን መርምር:: ሀ) በታማኝነት ፈተና ላይ ያለህ ውጤት ምን እንደሚመስል ግለጽ:: እግዚአብሔር ታማኝነትህን የፈተነው እንዴት ነው? ታማኝ ሰው ለመሆን ማደግ የሚያስፈልግህ በምን በምን ጉዳዮች ነው? ለ) ታዛዥ መሆንህን እያሳየህ ያለኸው እንዴት ነው? እግዚአብሔርንና በአንተ ላይ ሥልጣን ያላቸውን ሰዎች በበለጠ ለመታዘዝ መስተካከል ያለባቸው የሕይወትህ ክፍሎች ምን ምንድን ናቸው? ሐ) በእውቀትና በእውነት እንዴት እያደግክ ነው? በዚህ በኩል በበለጠ ለማደግ ምን እያደረግክ ነው?

ሐ. አንድ ሰው በባሕርይና በብስለት በሚያድግበት ጊዜ እግዚአብሔርም የግለሰቡን የኃላፊት ደረጃ ያሳድጋል። እግዚአብሔር ብዙውን ጊዜ ምንም ዓይነት ልምድ የሌለውን ሰው አንሥቶ ክአገልግሎት ላይ አያስቀምጠውም። (ይህ የመሪነት ልምድ የሌለውን እንደ የዲግሪ ምሩቅ እንሥተን ኃላፊነት ክምንሰጥበት አሠራር የተለየ ነው።) በእያንዳንዱ የአገልግሎት ደረጃ እግዚአብሔር ታማኝነታችንን ለማየት ይፈልጋል። በእግዚአብሔር ዓይን ለተጨማሪ ኃላፊነት መብቃታችንን የሚያሳየው ትልቁ ነገር ታማኝነታችንን ነው። ብዙውን ጊዜ እግዚአብሔር የአንድን ሰው አመራር ሰማሳደግ አምስት ነገሮችን ይጠቀማል።

*1) እግዚአብሔር ግለሰቡ በተለያዩ አገልግሎቶች እንዲሳተፍ ይመራዋል።* እነዚህ አገልግሎቶች የዝማሬ፣ ምጽዋት መሰብሰብ፣ ጽዳትና ወንበሮችን ማስተካከል የመሳሰሉትን ተግባራት የሚያካትቱ ሊሆኑ ይችላሉ። እግዚአብሔር ግለሰቡ በትናንሽ ነገሮች መሪዎችን ለመርዳት ራሱን «ዝግጁ ማድረጉን» ያያል። በትናንሽ ነገሮች ለማገልገል የማይፈልግ ሰው እምብዛም ለመሪነት አገልግሎት አይመረጥም። በእነዚህ አነስተኛ ነገሮች እግዚአብሔር ሁለት ነገሮችን ይመረምራል። <u>አንደኛ</u>፣ ግለሰቡ ሰማገልገል ፈቃደኛ ነው ወይ? ማንም ሰው ወደ ትምህርት ቤት ሄዶ በወንጌላዊነት ወይም በመጋቢነት በመሠልጠን የእግዚአብሔር ሕዝብ አገልጋይ መሆንን ሊማር አይችልም። የአገልጋይ ልብ የሚታወቀው ሌሎችን ለመርዳት በማለብ ጊዜውን በመስጠቱ፣ ዝቅተኛ ሥራዎችን በመሥራቱና በመሳሰሉት ነው። <u>ሁለተኛ</u>፣ ግለሰቡ ሥራውን «በታማኝነት» ይወጣል ወይ? ወንበሮችን በማስተካከሉና በማጽዳቱ በኩል ጥሩ ሥራ ይሠራል? በጊዜ በመምጣትና መዝሙሮችን በማጥናት የመዘምራን ቡድኑን በሚገባ ያዘጋጃል ወይስ የይድረስ ይድረስ አገልግሎት ነው የሚሰጠው?

*2) እግዚአብሔር ግለሰቡን ወደ ተወሰኑ አገልግሎቶች ይመራል።* ግለሰቡ ሳልዳኑት፣ የዳኑትን ደቀ መዛሙርት ለማድረግ፣ ሰዎች ቃሉን እንዲያውቁ ለመርዳት፣ ወዘተ. . . ሸክም ሊሰማው ይጀምራል። እግዚአብሔር ሕዝቡን ለማገልገል ራሱን



ይሰጥ እንደ ሆነ ለመመልከት በልቡ ውስጥ ይሠራል። ይህ ነገር እያደገ ሲሄድ ክርስቲያኖች ብዙውን ጊዜ «ጥሪ» ወደሚሉት ነገር ይጎለብታል። እግዚአብሔር እምብዛም በቤተ ክርስቲያን የማይሳተፍን ሰው ለአገልግሎት አይጠራም። ነገር ግን፣ አንድ ሰው በታማኝነት እግዚአብሔርን በሚያገለግልበት ጊዜ፣ እግዚአብሔር በተወሰነ መንገድ እንዲያገለግል ልቡን ያነሣሣል።

*3) ግለሰቡ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሚያሳስቡት ነገሮች ላይ በማተኮር ብዙ ጊዜ ያሳልፋል።* ሳልዳኑ ሰዎች ሸክም የሚሰማው ከሆነ፣ በምስክርነትና ወንጌላውያንን በመርዳት ብዙ ጊዜ ያሳልፋል። ወይም ሌሎች ወጣቶች አብረውት እንዲመሰክሩ ያደርጋል። መንፈሳዊ እውቀት ለሌላቸው አባላት ካሰበ፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት በመጀመር ወይም በሰንበት ትምህርት ቤት በማስተማር ኃላፊነቱን ይወጣል። በተወሰኑ አገልግሎች ውስጥ በሚሳተፍበት ጊዜ፣ ራሱም ሆነ ሌሎች ሰዎች የእግዚአብሔርን ጥሪ ይለያሉ። በመሆኑም፣ መሪዎች ተጨማሪ አገልግሎት ይሰጡታል። እግዚአብሔር ግለሰቡ ትሑት፣ የአገልጋይ ልብ ያለውና እወጣለሁ ያላቸውን አገልግሎቶች ሁሉ በማከናወን ታማኝ ሆኖ መገኘቱን ይከታተላል።

*4) ግለሰቡ እግዚአብሔርን በበለጠ ለማገልገል ሥልጠናዎችን ይፈልጋል።* በስጦታ የተካኑ ሰዎች ሁልጊዜም በመማር ሂደት ውስጥ ናቸው። በማንበብና ውጤታማ አገልግሎት የሚሰጡትን ሰዎች በመመልከት ይማራሉ። በአገልግሎታቸው ውጤታማ የሆኑትን ነገሮች በማጤንም ይማራሉ። ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር የአገልግሎት ችሎታቸውን ወደሚያሳድግ ትምህርት ቤት ገብተው መደበኛ ሥልጠና እንዲያገኙ ሊፈቅድ ይችላል።

ብዙውን ጊዜ በቤተ ክርስቲያን መሪዎች አንድ ሰው «ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት መግባት እፈልጋሁ» እስኪላቸው ድረስ ይጠብቃሉ። በአብዛኛው ግን እንዲህ ዓይነት ጥያቄ የሚያቀርቡ ሰዎች ትክክለኛ ልባዊ ፍላጎት የሌላቸው ናቸው። ይህ የሚሆነው ደግሞ ተጨማሪ የትምህርት ዕድል፣ የበለጠ ክብር፣

ወይም ገንዘብ በመፈለጋቸው ነው:: ነገር ግን ሽማግሌዎቹ ወደ አንድ ሰው በመሄድ «እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን በዚህ በኩል እንድታገለግል ይፈልጋል ብለን እናምናለን:: እነዚህን ስጦታዎች እንደ ስጦህ አይተናል:: እነዚህ ነገሮች ደግሞ ለቤተ ክርስቲያናችን አስፈላጊዎች ናቸው:: ወደ ትምህርት ቤት ገብተህ ሥልጠና ብታገኝ፣ የበለጠ ውጤታማ ትሆናለህ ብለን እናምናለን፣» ቢሉ የተሻለ ነው:: በዚህ ዓይነት እግዚአብሔር ግለሰቡ ተጨማሪ ሥልጠና እንዲያገኝ ያስችለዋል:: እግዚአብሔር በግለሰቡ ውስጥ በመሥራት ወደ በለጠ ኃላፊነት ይመራዋል:: ለአገልግሎቱ የሚያስፈልግ ክህሎት እንደሌለው ሲረዳ፣ የሥልጠናውን ጥሪ በደስታ ይቀበለዋል::

*ያልተፈተኑትን ወንዶችና ሴቶች ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤተ ከመላክ ይልቅ፣ መንፈሳዊ ባሕርይ፣ ታማኝነት፣* የአገልግሎት ፍላጎትና ሽማግሌዎች ለቤተ ክርስቲያን አስፈላጊ ነው የሚሉት ስጦታ ያላቸው ሰዎች ቢላኩ የተሻለ ነው:: ይህ እግዚአብሔር ሰዎችን የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ለማድረግ ከሚሠራበት መንገድ ጋር የሚስማማ ነው:: (ማስታወሻ:- መደበኛ ትምህርት አንድን ሰው የሚረዱ ጠቃሚ መሣሪያዎችን ሊያጎናጽፍ ይችላል:: ነገር ግን፣ ይህ በእግዚአብሔር ፊት ትልቁ መመዘኛ አይደለም:: አብዛኞቹ ሐዋርያት ብዙ ትምህርት አልነበራቸውም:: አብዛኞቹ ምርጥ መሪዎች ራሳቸውን በራሳቸው ያስተማሩ ናቸው:: ስለሆነም፣ በመደበኛ የሥነ-መለኮት ሥልጠና ላይ ከፍተኛ ትኩረት ማድረግ የለብንም::)

ይህ በተለይ እግዚአብሔር ለአገልግሎት ሊያነሣ ለሚፈልጋቸው ሰዎች «አደገኛ» ዘመን ነው:: ዓለማዊ የትምህርት አስተሳሰብ ሰዎችን ወደ ትዕቢት ይመራል:: ስንት የተማሩ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ናቸው በትሕትና ለማገልገል የሚፈቅዱት? ወደ ትንሽ የገጠር ቤተ ክርስቲያን በመሄድ የአካባቢውን ሰዎች መስለው ለማገልገል ፈቃደኛ የሚሆኑ ስንቶች ናቸው? ብዙዎች እንዳልሆኑ የምናውቀው ነው:: አንድን አገልጋይ ተመልሶ በበለጠ ችሎታ እንዲያገለግልን ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጅ ስንልከው፣



ጭራሽ ሳይመለስ ይቀራል:: ለራሱ ወደሚመቹ ቦታዎች ይሄዳል:: ተመልሶ ቢመጣም አዲስ ባገኘው ዲፕሎማና ዲግሪ ትዕቢት ተከናንቦ ይገኛል:: ከዚያ በኋላ እግዚአብሔር በአገልግሎቱ እንዲረዳው ራሱን ዝቅ አድርጎ በትሕትና የሚጠይቅ አገልጋይ መሆኑ ይቀራል:: ከዚያ ይልቅ፣ በትምህርቱ ላይ በመደገፍ በራሱ ጉልበት መሥራቱን ይቀጥላል:: ይህ መደበኛ ትምህርት ምን ያህል አደገኛ ሊሆን እንደሚችል የሚያሳይ ነው:: አንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ እንደ ጻፈው፣ «የመሪዎችን ፉክክር ለማስናዳት ከፈለግን ምናልባትም እረፍት የሌላቸውን፣ ከሚችሉት በላይ ለማከናወን የሚፈልጉትንና እርካታ ያጡትን ምሁራን ልናፈራ እንችላለን:: አንድን ሰው ለመሪነት ተጠርተሃል ማለቱ መንፈሳዊነቱን ያጠፋዋል:: ምክንያቱም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ጉጉት ከየትኛውም ኃጢአት በላይ የከፋ ሲሆን፣ እጅ የሰጡትን ሰዎች ለአገልግሎት ብቁ እንዳይሆኑ ያደርጋቸዋል:: ዛሬ በጣም የሚያስፈልገው ከምሑሩ ይልቅ መንፈሳዊው ነው::» (ማስታወሻ:- በትምህርት 22 መሪዎችን ስለ ማሠልጠን በበለጠ እንነጋገራለን::)

25ኛ ጥያቄ:- ሀ) እግዚአብሔርን የአንድን ግለሰብ አገልግሎት ለማሳደግ መደበኛ ሥልጠናውን በመሣሪያነት ሊጠቀም የተመለከትከው እንዴት ነው? ለ) አንድ ሰው ፈተናውን በመውደቅ በመደበኛ ትምህርት ምክንያት ትዕቢት አገልግሎቱን እንዲያወድም ሲያደርግ የተመለከትክበትን ሁኔታ ግለጽ:: ሐ) ይህ ስለ መደበኛ ትምህርት ተያያዥ ችግሮች ምን ያስተምረናል? መ) በቤተ ክርስቲያን መሪዎች መደበኛ ትምህርት ያገኙ ሰዎች የሚያሳዩትን ትዕቢት ለመቀነስ ምን ሊያደርጉ ይችላሉ?

5) *ከሠለጠነ በኋላ እግዚአብሔር ተጨማሪ የአገልግሎት ደረጃዎችንና ውጤታማነትን ይሰጠዋል::* ብዙውን ጊዜ ግለሰቡ ውጤታማ የሚሆነው በተወሰኑ አገልግሎቶች ይሆናል:: [ቤተ ክርስቲያን በአንድ አገልግሎት (ለምሳሌ፣ በአስተማሪነት) ብቁ የሆነን ሰው ለሌላ አገልግሎት (ለምሳሌ፣ ለአስተዳደር ሥራ) ብትሾመው፣ ለራሷም ሆነ ለግለሰቡ ትልቅ ጥፋት ነው::] እግዚአብሔርን አንድን ሰው የሚያሳድገው በጥሪውና በስጦታዎቹ ክልል ነው:: ሥልጠናውን ካገኘ በኋላ፣ ግለሰቡ በተወሰነ አገልግሎት ላይ ትኩረት ማድረግ አለበት:: ከዚያ በኋላ እግዚአብሔር የሌሎች አገልግሎቶችን ዕ

ድሎች ይሰጠዋል:: ለምሳሌ፣ በሰባኪነት የሠለጠነ ሰው ብዙ ሰባኪዎች ባሉበት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ቢመደብ፣ የለባኪነቱን ዕድል ላያገኝ ይችላል:: ነገር ግን የሰብከት ዕድሉን በሚያገኝበት ጊዜ በታማኝነት ሰብከቱን አዘጋጅቶ በጥሩ ሁኔታ በማቅረብ የሰዎች ሕይወት የሚቀየርበትን መንገድ ይፈልጋል:: በተመሳሳይ ጊዜ፣ በትሕትና በመመላለስ ከእርሱ በላይ ላሉት ይታዘዛል:: ራሱን ወደ ላይ ለማውጣት አይታገልም:: በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር ሕዝቡን ተጠቅሞ ወደ በለጠና ወደሚታይ የሰብከት አገልግሎት ሲያደርሰው ይችላል:: የራሱም ሆነ የሌሎች አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች እንዲሰብክ ይጠይቁታል:: ክትንሽ ቤተ ክርስቲያን ወደ ትልቅ ያድጋል፣ ወዘተ. . . በእያንዳንዱ የአገልግሎት ዕድል ውስጥ እግዚአብሔር ታማኝነቱንና ባሕርዩን ይፈትናል:: ፈተናውን ሲያልፍ፣ እግዚአብሔር ከፍ ወዳለ ደረጃ ያደርሰዋል::

> 26ኛ ጥያቄ:- *ሀ) እግዚአብሔር አሁን ባለህበት አገልግሎት እንድታድግ እንዴት እንዳስቻለህ ከተሞክሮህ ምሳሌዎችን ስጥ:: ለ) ከላይ የተጠቀሱትን አንዳንድ ነጥቦች በአንተ ሕይወት ውስጥ እግዚአብሔር የተጠቀመው እንዴት ነው?*

መ. እግዚአብሔር የሰውን ባሕርይ ሰመፈተን አስቸጋሪ ነገሮችን ይጠቀማል:: ብዙውን ጊዜ እነዚህ ፈተናዎች የሚያተኩሩት በሚከተሉት አራት የሕይወት ክፍሎች ላይ ነው::

1) *በሥልጣን ላይ ካለ ሰው ጋር የሚያጋጥም ችግር::* እግዚአብሔር ብዙውን ጊዜ አገልጋዮች ከሽማግሌዎች ጋር አስቸጋሪ ጊዜያትን እንዲያሳልፉ ይፈቅዳል:: አገልጋዩ በሥልጣን ላይ ካለው ሰው ጋር በማይስማማበት ጊዜ ሳይቀር ይገዛለት እንደ ሆነ ለማየት ይፈልጋል:: የእግዚአብሔርን ቃል እንድንተላለፍ እስካልጠየቁን ድረስ፣ ከእኛ በላይ ላሉት ለዎች መገዛት እንዳለብን መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል:: የተሳሳቱ ነገሮችን ሲያደርጉና የማንስማማባቸውን ውሳኔዎች ሲሰጡ ጭምር መገዛት አለብን:: [ለምሳሌ፣ ዔሊ ልጆቹን ሰለሚይዝበት መንገድና በመገናኛው ድንኳን ውስጥ ስለሚያገለግሉበት መንገድ ደስተኛ ባይሆንም፣ ሳሙኤል ለዔሊ ይታዘዝ ነበር:: (1ኛ ሳሙ. 2-3::)] ይህንን



የምናደርግበት ምክንያት እግዚአብሔር በሥልጣን ላይ ሰዎችን የማስቀምጠው እኔ ነኝ ስላለ ነው:: መሪዎችን የሚያስነሣውና የሚጥል እርሱ ነው:: በመሪዎች ላይ ማመፅ ብዙውን ጊዜ በእግዚአብሔር ላይ ማመፅ ነው:: በሥልጣን ላይ ላሉት ሰዎች የማይገዙ ሰዎች ብዙውን ጊዜ በትሕትና ለመታበዝ አይችሉም::

2) *እግዚአብሔር ከአስቸጋሪ ሰዎች ጋር በሚኖረን የግንኙነት ችግር ሳቢያ ይፈትነናል::* እግዚአብሔር የሚጎዳንን ሰው ወደ ሕይወታችን ያመጣል:: ይህ ሰው በሐሜት ወይም የምንናገረውን ባለመታዘዝ ችግር ይፈጥርብናል:: ወይም ባሕርዩና አመለካከቱ ከእኛ ጋር የማይገጥም ይሆናል:: በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር በቸርነት ግለሰቡን ማስተናገዳችንን ያያል:: ይህም እኛ ለእርሱ ሳንመች እግዚአብሔር በፍቅሩ እንደሚያኖረን ማለት ነው:: እግዚአብሔር የግንኙነት ችግሮችን ተቋቁመን መዝለቅ መቻላችንን ለማየት ይፈልጋል:: የማይቻል በሚመስልበት ሁኔታ ውስጥ የሰጠንን ራእይ ለመፈጸም መቻላችንን ለማወቅ ይፈልጋል:: ሌሎች ስማችንን ለማጥፋት በሚፈልጉበት ጊዜ፣ እርሱ ስማችንን እንደሚጠብቅ ተማምነን ማገልገል መቻላችንን ለማወቅ ይሻል:: በቁጣ ወይም በበቀል ምላሽ ከመስጠት ይልቅ፣ ገር የይቅርታ መንፈስ ማሳየታችንን ለማወቅ ይፈልጋል::

3) *የበለጠ ኃላፊነት በሚሰጠን ጊዜ፣ ኃላፊነቱን የምንጠቀምበት መንገድ ትልቁ ፈተና ነው::* እግዚአብሔር ልክ እንደ ዓለማውያን ሥልጣናችንን የበለጠ ጥቅም ለማግኘት ወይ ለዎችን ለመቆጣጠር መጠቀማችንን ለማወቅ ይፈልጋል:: ወይስ ሥልጣኑን የምንጠቀመው ሰዎችን ለማገልገል፣ እንዲሁም እግዚአብሔርን እንዲከተሉና በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲያድጉ ለመርዳት ነው? ምእመናንን በሙሉ በፍትሐዊነት እናስተናግዳለን ወይስ ኃይላችንን በመጠቀም ለጓደኞቻችን፣ ለቤተሰቦቻችንና ለጎሳችን አባላት እናዳላለን? ለሚቸገሩ ሰዎች እንራራላቸዋለን ወይስ ግድየለሾች እንሆንባቸዋለን?

4) *እግዚአብሔር ብዙውን ጊዜ በእርሱ ላይ መደገፋችንን ለመፈተን በማደግ ላይ ባሉት መሪዎች ላይ የግል ችግሮችን*

ያመጣል:: ይህ ችግር እግዚአብሔር የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ እንደሚያሟላቸው እንዲተማመኑ የሚያደርግ የገንዘብ ችግር፣ ወይም እግዚአብሔር ነገሮችን በመቆጣጠር ላይ መሆኑን ማመናቸውን የሚፈትን የቤተሰብ አባል መታመም ወይም መሞት ሊሆን ይችላል::

> 27ኛ ጥያቄ:- ሀ) እግዚአብሔር ከላይ የተገለጹትን አስቸጋሪ ሁኔታዎች ወደ ሕይወትህ በማምጣት እንዴት እንደ ፈተንህ ግለጽ:: ለ) ከእነዚህ ፈተናዎች የተማርካቸው ነገሮች ምን ምንድን ናቸው? ሐ) እነዚህ ትምህርቶች እግዚአብሔርን ለማገልገል ለምን እንደሚያስፈልጉ ግለጽ::

ሠ. ግለሰቡ በአገልግሎት ኃላፊነቶች በሚያድግበት ጊዜ፣ በመመርመር ችሎታውም ማደጉን ይፈትናል:: ለእግዚአብሔር ነገሮችን «ከማከናወን» ይልቅ፣ እግዚአብሔር የሚጠቀምበት መሣሪያ «በመሆኑ» ላይ ማተኮር ጀምሯል? በራሱ ጉልበት መሥራቱን በመቀነስ፣ በጸሎት በእግዚአብሔር ላይ መደገፉን እያሳየ ነው? በድክመቱ ውስጥ የእግዚአብሔርን ኃይል እንዴት ሊጠቀም እንደሚችል መማር ጀምሯል? የእግዚአብሔርን ድምጽ ከራሱ ፍላጎት ወይም ከሰዎች ድምጽ ይለያል? እግዚአብሔር አንድን ነገር ያደርጋል ብሎ መገመት በእግዚአብሔር ላይ ከመታመን እንደሚለይ ተረድቷል? ላይ ላዩን ከማየት አልፎ ምእመናን እግዚአብሔርን በሚያስከብር መንገድ እንዲኖሩ የሚያደርጉትን ነገሮች ለመመልከት ችሏል? የራሱም ሆነ የሌሎች ሰዎች አገልግሎቶች እግዚአብሔርን ወይም ሰዎችን በሚያስከብር መንገድ መካሄዳቸውን ይለያል? እነዚህን አገልግሎቶች እንዴት የበለጠ ውጤታማ ማድረግ እንደሚቻል ይገነዘባል? እነዚህን የመሳሰሉትን ጉዳዮች መመርመር ስንጀምር፣ እግዚአብሔር ይህንን ችሎታችንን ለራሱና ለቤተ ክርስቲያን ልንጠቀም ወደምንችልበት ደረጃ ያሳድገናል::

የእያንዳንዱ ሰው ቀጣይ እድገትና ለእግዚአብሔር የሚያበረክተው ጠቀሜታ የእግዚአብሔር «አገልጋይ» በመሆን ለራሱና ለሥራው «ታማኝ» ሆ በመቀጠሉ ላይ የተመሠረተ ነው:: መሪ



ዎች ለዚህ የመሪነት የእድገት ሂደት የተለያዩ ምላሾችን ሊሰጡ ይችላሉ::

በመጀመሪያ፣ ብዙ መሪዎች የባሕርይና የታማኝነት ፈተናዎችን ስለሚወድቁ፣ እግዚአብሔር እነዚህን ነገሮች እስኪማሩ ድረስ ወደ ዳር አውጥቶ ያስቀምጣቸዋል::

ሁለተኛ፣ ሌሎች ደግሞ በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ መሪ መሆን የሚያስከትለውን ችግር ለመቋቋም ይቸገራሉ:: ስለዚህ አገልግሎትን ይተዋሉ ወይም ለእነርሱ በሚመቹ አነስተኛ የአመራር ደረጃዎች ላይ ብቻ ይሠራሉ::

ሦስተኛ፣ አንዳንድ መሪዎች በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ማደጋቸውን ስለሚያቆሙ፣ እግዚአብሔር ከሰጣቸው ችሎታ በታች ይኖራሉ::

አራተኛ፣ ጥቂቶች ደግሞ ማደጋቸውን ስለሚቀጥሉ፣ እግዚአብሔር ወደ በለጠ የአገልግሎት ኃላፊነቶች ይሾማቸዋል::

> 28ኛ ጥያቄ:- የተለያዩ ሰዎች በእነዚህ አራት መንገዶች ምላሽ ሲሰጡ የተመለከትክበትን ሁኔታ ግለጽ::

## ሦስተኛ ቀን

አንድን መሪ ጠቃሚ የቤተ ክርስቲያን መሪ አድርጎ ማሳደግ የሦስት አካላት የጋራ ጥረት ነው:: በመጀመሪያ፣ ትልቁን ሚና የሚጫወተው እግዚአብሔር ነው:: እርሱ ለሰዎች አመራርን የሚያሳድጉ ልዩ ባሕርያትንና መንፈሳዊ ስጦታዎችን ይሰጣል:: እንዲሁም ደግሞ ወደ መንፈሳዊ ብስለትና የአመራር ክህሎቶች እንዲያድጉ የሚያስችሏቸውን ምርጫዎች ያደርጉ ዘንድ ሁኔታዎችን ያመቻችላቸዋል:: ሁለተኛ፣ እግዚአብሔር የሰጠውን ዕድል በመጠቀም ግለሰቡ ወደ አመራር ሊያድግ ወይም ዕድሉን ላለመጠቀም ሊመርጥ ይችላል:: (ማስታወሻ:- በትናንትናው ዕለት እነዚህን ሁለት የእድገት መንገዶች አጥንተናል::) ሦስተኛ፣ እግዚአብሔር በሳል መሪዎችን በመጠቀም ወጣቶች እንዴት

የእግዚአብሔርን ሕዝብ እንደሚመሩ በምሳሌነት የሚማሩበትን መንገድ ያመቻቻል:: ይህንን ዛሬ እናጠናለን::

**3. ስጦታ ያላቸውን አዳዲስ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በማሠልጠኑ በኩል ልምድ ያላቸው የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የሚጫወቱት ሚና::**

*ሀ. የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን እና አገልጋዮችን በማሳደጉ ረገድ አብያተ ክርስቲያናት አራት አመለካከቶችን ሊይዙ ይችላሉ::*

1) አብዛኞቹ የገጠር አብያተ ክርስቲያናት ቤተ ክርስቲያኖቻቸው ሥልጠና ባላገኙ በጎ ፈቃደኞች መመራታቸውን እንዲቀጥሉ ይፈልጋሉ:: የእግዚአብሔርን መንጋ በብቃት በእረኝነት ሊያስተዳድር የሚችል ብቁ ሥልጠና ያገኘ አገልጋይ የማግኘቱ ጉዳይ ብዙም አስፈላጊ መስሎ አይታያቸውም:: «ለብዙ ዓመታት ቤተ ክርስቲያናችን ሥልጠና ባላገኘ መጋቢ ስትመራ ቆይታለች:: አሁን አዲስ መጋቢ የሚያስፈልገን ለምንድን ነው?» ይላሉ:: ጤናችንን በተመለከተ እንዲህ ዓይነት አመለካከት ብንይዝ ምን እንደሚከሰት አስብ:: ክሊኒኮች ከመከፈታቸው በፊት ሲያመን ትንሽ አውቀት ብቻ ወዳላቸው ባህላዊ ሐኪሞች እንሄድ ነበር:: አሁን ወደ ሐኪም ቤት ለምን እንሄዳለን? ልንል አንችላለን:: ወይም ደግሞ ወደ ሐኪም ቤት ስንሄድ ዘበኛው ደስ ያለውን መድኃኒት እንዲሰጠን ብንጠይቀውስ? በርግጥ፣ ይህንን ልናደርግ አንችልም:: በሕክምና ሙያ የሠለጠነ ሰው እንዲያክመን ነው የምንፈልገው:: እንዲህ መንፈሳዊ በሽታዎቻችንንና ችግሮቻችንን በመስኩ የሠለጠኑ ሰዎች እንዳያክሙ የምንከላከለው ለምንድን ነው? ምናልባትም አብያተ ክርስቲያኖቻችን ደካማ ሆነው የሚቀሩበት አንዱ ምክንያት የሠለጠኑ መሪዎችን ስለማንጠቀም ሊሆን ይችላል:: ዛሬ አጅግ ከሚያስፈልጉን ነገሮች አንዱ ለማኅበረሰቡ መንፈሳዊ ችግሮች መፍትሔ የሚሰጡ በቂ ሥልጠና ያገኙ እረኞች መኖራቸው ነው:: ስጦታ ያላቸውን መንፈሳዊ አገልጋዮች ለማሠልጠንና ከዚያም በአግባቡ ለመክፈል ገንዘባችንን ካልተጠቀምን፣ ቤተ ክርስቲያኖቻችን እረኛ እንደሌላቸው በጎች በእግዚአብሔር ጠላቶች መነጠቃቸው የማይቀር ነው::



2) አብዛኞቹ ስለ አገልጋይ የሚያስቡት ያላቸው አገልጋይ ሌላ ቦታ በሚሄድበት ጊዜ ብቻ ነው:: ግለሰቡ ወደ ሌላ ስፍራ ሲሄድ ወይም ሲሞት ማን ያገለግለናል? ብለው ያስባሉ:: የማቀድ ጉድለት ከሚከተሉት ሦስት ነገሮች አንዱን እንድናደርግ ያስገድደናል:: አንደኛ፣ ለተወሰነ ጊዜ ያለ አገልጋይ ልንቆይ እንችላለን:: የቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ሕይወት ይጎዳና ወጣቶቻችን ወደ ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ይሄዳሉ:: ወጣቶቹ እንደ ወጡ የሚቀሩባቸው ሁኔታዎች ይኖራሉ:: ሁለተኛ፣ የማናውቀውና ብቃት የሌለው ሰው እንዲያገለግለን ልናደርግ እንችላለን:: ብዙውን ጊዜ ይህ ብቃት የሌለው ሰው (መንፈሳዊነት ወይም ክህሎት የሌለው) የእረኛ ፍላጎታችንን ስለማያሟላልን ቤተ ክርስቲያን ትጎዳለች:: ሦስተኛ፣ በአገልግሎት ያልተፈተነን ሰው ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት በመላክ ተመልሶ ያገለግለናል ብለን ተስፋ እናደርጋለን::

3) አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ያገኙትን የተማረ ወጣት ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት በመላክ ተመልሶ በመሪነት እንዲያገለግል ይፈልጋሉ:: ይህ አደገኛ ነው:: ምክንያቱም ግለሰቡ በእግዚአብሔር የተጠራና ስጦታ ያለው ወይም ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የሚመች መንፈሳዊ ባሕርይ ያለው ላይሆን ይችላል:: ግለሰቡ የተመረጠው በቅርብ ስለ ተገኘና ወደ ዩኒቨርስቲ ለመግባት ባያስችልም፣ የተወሰነ ትምህርት እንዳለው ስለምናውቅ ብቻ ነው:: ቤተ ክርስቲያንን ለማገልገል የሚያስችል ጥሪ ከእግዚአብሔር ዘንድ ስለሌለው፣ አገልግሎት የተሻለ ነገር እስኪያገኝ ድረስ የሚያከናውነው ሥራ ይሆናል:: የእግዚአብሔርን ሕዝብ በእረኝነት እንዲያገለግል በልቡ ውስጥ የሚገፋፋው ነገር ስለሌለ፣ የእግዚአብሔር ጥሪ የሌለው ሰው አምብዛም ውጤታማ አይሆንም::

4) ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ስጦታ ያላቸውን ሰዎች ቀደም ብላ ለአገልግሎት ማዘጋጀት አለባት:: መንፈሳዊ መሪዎችንና አገልጋዮችን ስለ ማዘጋጀት የሚያስቡ አብያተ ክርስቲያናት ብዙ ዎች አይደሉም:: ይሁን እንጂ፣ ብዙ ሰዎች በአገልግሎት ብቃት

እንዲያድጉ ለመርዳት የምትፈልግ ቤተ ክርስቲያን ስጦታ ያላቸው መሪዎችና አገልጋዮች እንደሚኖሯት እይጠረጠርም። እንዲህ ዓይነት አብያተ ክርስቲያናት እንደ ሙሴ ያለ አገልጋይ ሲሞት፣ ኢያሱ በቀላሱ ይተካዋል። ጠንካራና ከጊዜ ወደ ጊዜ የማይወላከፉ አብያተ ክርስቲያናት እንዲኖሩን ከተፈለገ፣ የወደፊት የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን የሚያሳድግ አመለካከት ሊኖረን ይገባል።

29ኛ ጥያቄ፦ ሀ) ከላይ በተጠቀሱት አራት መንገዶች የተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት ለመሪነት ፍላጎቶቻቸው ምላሽ ሲሰጡ የተመለከትከው እንዴት ነው? ለ) በቤተ እምነታችሁ በጣም የተለመደው አሠራር ከአራቱ መካከል የትኛው ነው?

ሰ. አዳዲስ መንፈሳዊ አገልጋዮችን ማፍራት የሚጀምረው ያሉት የቤተ ክርስቲያን መሪዎችና አገልጋዮች በመሥዋዕትነት እግዚአብሔርንና ቤተ ክርስቲያንን ማገልገል ምን እንደ ሆነ በተግባር ከሚያሳዩበት ሁኔታ ነው። ዛሬ የአገልጋዮችን ልጆች ጨምሮ ብዙ ሰዎች አገልጋይ ለመሆን አይፈልጉም። ለምን? አንደኛው ምክንያት ወጣቶች የሚያደንቋቸውና ሊመስሏቸው የሚፈልጓቸው ምሳሌያዊ አገልጋዮች አለመኖራቸው ሊሆን ይችላል። እግዚአብሔርንና ሕዝቡን የማገልገል ፍላጎት የሚነሣሣው ብዙውን ጊዜ ወጣቶች አገልጋዮችን ከመመልከታቸውና ከእነርሱ ጋር ግንኙነት በመፍጠራቸው ነው። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ወይም አገልጋዮች ከወጣቶች ጋር የማይቀራረቡ ከሆነ፣ ክርስቶስንና ቤተ ክርስቲያኑን በማገልገል የሚገኘውን ደስታ ለማስተላለፍ አይችሉም፣ ምንም እንኳን ቁሳዊ በረከቱ ዓለማዊ ሥራ ላይ ቢሰማሩ ሊያገኙ የሚችሉትን ያህል ሳይሆን ቢችልም።

30ኛ ጥያቄ፦ አንድ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ወይም መሪ በሕይወትህ ላይ ተጽዕኖ በማሳደር በምሳሌነቱ እግዚአብሔርን መከተልና ማገልገል ምን እንደ ሆነ ያሳየበትን ሁኔታ ግለጽ።

ሐ. እንደ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች መንፈስ ቅዱስ ሕዝቡን ይመራ ዘንድ ደስ ያሰውን ሰው የመምረጥ መብት እንዳለው መረዳት አለብን። ይህ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ወይም የምእመናን ምርጫ አይደለም። ለግለሰቡ ለመሪነት የሚያስፈልጉትን ልዩ



ባሕርያትና ስጦታዎች የሚሰጠው መንፈስ ቅዱስ ነው። ግለሰቡ ወደ መንፈሳዊ ብስለት እንዲደርስ ሁኔታዎችን በሕይወቱ ውስጥ የሚቆጣጠረው መንፈስ ቅዱስ ነው። ሕይወቱንና እምነቱን ለማሳደግ የተወሰኑ ሰዎችን ወደ ግለሰቡ ሕይወት የሚያመጣው መንፈስ ቅዱስ ነው። ግለሰቡ መቼ ለአገልግሎት ዝግጁ እንደሚሆንና በምን ዓይነት የአመራር ደረጃ ላይ መቀመጥ እንዳለበት የሚወስነው መንፈስ ቅዱስ ነው። ስለዚህ እኛ መሪዎችን «አንፈጥርም»። ይህንን የሚሠራው መንፈስ ቅዱስ ነው። መሪዎችና ምእመናን ሊያደርጉ የሚችሉት ነገር ቢኖር መንፈስ ቅዱስ ለመሪነት ያዘጋጃቸውን ሰዎች «መለየትና እውቅና መስጠት» ነው። ከዚያ በኋላ የመሪነትና የአገልግሎት ክህሎታቸውን እንዲያሳድጉ ልንረዳቸው እንችላለን።

መ. የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እግዚአብሔር የአመራርና የአገልግሎት ስጦታ የሰጣቸውን ወጣቶች መፈለጋቸውን መቀጠል አለባቸው። ለእግዚአብሔር የሚቀኑ፣ የተፈጥሮ የአመራር ስጦታዎች ያሏቸውንና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚፈለጉ መንፈሳዊ ስጦታዎች ያሏቸውን ወጣቶች በሚያገኙበት ጊዜ፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከእነዚህ ሰዎች ጋር ተጨማሪ ጊዜ ማሳለፍ አለባቸው። ልክ ጳውሎስ ሕይወቱን ለጢሞቴዎስ እንዳካፈለው፣ እነዚህን ሰዎች በደቀ መዝሙርነት በማሳደግ በመንፈሳዊ ሕይወታቸውም ሆነ በባሕርያቸው ጠለቅ ካለ ደረጃ እንዲደርሱ ማድረግ ጠቃሚ ነው። እግዚአብሔርን ለማስከበርና ቤተ ክርስቲያንን ለመጥቀም የሚፈልጉ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ስጦታ ያላቸው ወጣቶችን ሲያዩ «ቦታዬን ሊያስለቅቁኝ ነው» በሚል ፍርሃት ከመራድ ይልቅ፣ ወጣቶቹ ለእግዚአብሔር በሚሰጡት አገልግሎት እንዲያድጉ ሊያበረታቷቸው ይገባል። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በየጊዜው በቤተ ክርስቲያናቸው ውስጥ ስጦታ ያላቸውን ወጣቶች በመለየት ቦታ ቢሰጧቸው መልካም ነው። ከዚያ በኋላ እንዴት እንደሚያሳድጓቸው ዕቅዶችን ሊያወጡ ይችላሉ።

*31ኛ ጥያቄ:- ዘጸአ. 24:12-13፤ 33:7-11ን አንብብ:: ሀ) ሙሴ ኢያሱን ወደ ተራራውና ወደ ድንኳን የወሰደው ለምንድን ነው? ለ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ኢያሱዎችን ለወደፊት አመራር ለማብቃት ምን ዓይነት ሚናዎችን ሊጫወቱ ይችላሉ? ሐ) 1ኛ ቆሮ. 10:31-33፤ 1ኛ ጢሞ. 4:11-13፤ 2ኛ ጢሞ. 3:10-15፤ 1ኛ ጴጥ. 5:2-3ን አንብብ:: እነዚህ ጥቅሶች ሌሎች እንዴት እንደሚኖሩና እግዚአብሔር በሚፈልገው መንገድ እንዲመሩ ስለ መርዳት ምን ያስተምራሉ?*

ሠ. የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሰዎች በባሕርይና በአገልግሎት ክህሎቶች እንዲያድጉ ማሠልጠን/በግል ማሳየት አለባቸው:: ይህ ማለት ሌሎች ሰዎች የሚከተሉትን ምሳሌነት ማሳየት ማለት ነው:: ጳውሎስ ሰዎች እርሱን እንዲመስሉ ነግሯቸዋል (1ኛ ቆሮ. 11:1):: ጢሞቴዎስ አኗኗሩን፣ እምነቱንና ትምህርቱን እንዲከተል አሳስቦታል:: ጴጥሮስም ሽማግሌዎች የእግዚአብሔርን ሕዝብ በመልካም ምሳሌነት እንዲመሩ ነግሮአቸዋል:: ብናስተውልም ባናስተውልም፣ ሁላችንም መሪዎች ይህንን ነገር እናደርጋለን:: ጥያቄው እንግዲህ፣ «ለሌሎች በምሳሌነት የምናሳየው መንፈሳዊ አኗኗርንና ትሕትና የተሞላበትን አገልግሎት ነው ወይስ የመሪነትን ሥልጣን በመጠቀም ሌሎችን መበደል የሚንጸባረቅበትን የራስ ወዳድነት ሕይወት ነው?» የሚለው ነው:: ሁሉም መሪዎች ወደፊት መሪዎች ለሚሆኑ ሰዎች ምሳሌ ዎች ናቸው:: ስለሆነም ትክክለኛውን ምሳሌነት ማሳየታችን ወሳኝ ነው:: እስተዋይ መሪዎች ስጦታ ያላቸውን ሰዎች በመምረጥ እግዚአብሔርን የሚያስከብርና መንግሥቱን የሚገነባ መሪ ማለት ምን ማለት እንደ ሆነ በምሳሌነት ያሳያሉ:: ይህ በምሳሌነት የማስተማር ሂደት አያሌ ነገሮችን ያካትታል:-

1) ግለሰቡ የእግዚአብሔርን ፈቃድ በማወቅና ከእርሱ ጋር ባለው ግንኙነት እንዲያድግ ለማገዝ አብሮ መጸለይና መጽሐፍ ቅዱስ ማጥናት:: ሙሴ ኢያሱን ወደ ተራራውና ወደ ድንኳን የወሰደው ከእግዚአብሔር ጋር ሲገናኝ እንዲያየው በመፈለግ ነበር:: ሐዋርያት ከኢየሱስ የጸሎት ሕይወት የተለየ ነገር በመመልከታቸው ነበር ጸሎት እንዲያስተምራቸው የጠየቁት (ሉቃስ 11:1):: የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የተሟሟቀ የጸሎት



ሕይወት በመምራትና የእግዚአብሔርን ቃል በአግባቡ በመምራት ምሳሌያዊ ሕይወት ማሳየት አለባቸው::

2) መሪዎች ሆነ ብለው እነዚህን ወጣቶች ወደ ራሳቸው ሕይወት ያስጠጋሉ:: መንፈሳዊ ባል እንዴት ከሚስቱና ከልጆቹ ጋር እንደሚኖር እንዲያዩ ወደ ቤቱ ይጋብዛቸዋል:: እግዚአብሔር የሰጠውን ገንዘብ እንዴት በታማኝነት እንደሚይዝ፣ ወዘተ. . . ያሳየዋል:: በሕይወት ውስጥ ደስ የማይሉ ሁኔታዎች በሚከሰቱበት ጊዜ እንዴት ምላሽ እንደሚሰጥ ያሳያቸዋል::

3) የቤተ ክርስቲያን አገልጋዩ ግለሰቡን ወደ ቤተ ክርስቲያን በመጋበዝ አገልግሎቱን እንዲመለከትና እንዲሳተፍ ማድ ረግ ይገባዋል:: አገልጋዩ ወንጌላዊ ከሆነና እግዚአብሔር ለጠፉት ሰ ዎች እንዲያስብ ያደረገውን ሰው ከተመለከተ፣ ለምስክርነት በሚወጣበት ጊዜ ይዞት ይሄዳል:: ወይም አስተማሪ ከሆነ ደግሞ፣ አዲስ አማኝ በደቀ መዝሙርነት በሚያሳድግበት ቦታ ላይ እንዲገኝ ይጋብዘዋል:: ለማያምኑ ሰዎች ስለ ክርስቶስ ለመመስከር በሚፈልግበት ጊዜ ይዞት ይሄዳል:: ወይም ደግሞ የታመሙትን እንዲያጽናና ሆስፒታል ይወስደዋል::

4) የቤተ ክርስቲያን አገልጋዩ (መሪው) የውክልናን ሂደት በመጠቀም፣ ለወደፊቱ አገልጋይ ኃላፊነቶችን ይሰጠዋል:: ውክልና (ምዕ. 11) ሰዎች በአገልግሎት እንደያድጉ ለማስቻል ጠቃሚ መንገድ ነው:: መሪው ውክልናን የሚጠቀመው ሥራውን ለማከናወን ብቻ ሳይሆን፣ ሰዎችን በአገልግሎት ለማሳደግ ጭምር መሆኑን መረዳት አለበት:: አንድ ሰው የሚያድገው የራሱን ውሳኔ ዎች እንዲሰጥ ነጻነት ሲሰጠው መሆኑንም መረዳት ይኖርበታል:: ስለዚህ የቤተ ክርስቲያን መሪው የግለሰቡን ውሳኔዎች በጥብቅ መቆጣጠር የለበትም:: ጥያቄዎችን በማንሣት ግለሰቡ ስለ ነገሮች በጥልቅ እንዲያስብ ሊያደርግ ይችላል:: ጥያቄዎች ከቀረቡለት እስተያየት ሊሰጥ ቢችልም፣ ውክልና የተሰጠው ሰው የተለያዩ አማራጮችን በማገናዘብ የራሱን ውሳኔ እንዲሰጥ ማበረታታት አለበት:: የወደፊቱ እገልጋይ ቤተ ክርስቲያን በማጽዳት ወይም ለኮንፈረንስ ዝግጅት የሚያስፈልጉትን ኃላፊነቶች በመወጣት

ሊጀምር ይችላል። ከዚያም እንደ ድቁና ያሉ ኃላፊነቶች ሊሰጡት ይችላሉ። ከዚያም የስብከትና የአገልግሎት የጊዜ ሠሌዳዎችን እንዲያዘጋጅ፣ የኮንፍረንስ ዝግጅቶችን፣ የሰንበት ትምህርት ቤቶችን መምራት የመሳሰሉትን ኃላፊነቶች እንዲወጣ ሊደረግ ይችሳል።

5) የክትትልና የምዘና ጊዜያትን በመጠቀም፣ የቤተ ክርስቲያን መሪው ግለሰቡ ማሻሻል ያለባቸውን ነገሮች ይጠቁማል። ሰሎሞን ብረት ብረትን እንደሚስል፣ ሰው ሰውን ይስላል ብሏል (ምሳሌ 27:17)። ልምድ ያላቸው የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ወጣት አገልጋዮች አገልግሎትን የሚያወድሙትን የባሕርይ ጉዳዮች እንዲያሸንፉ መርዳት አለባቸው። እንደ ኩራት፣ ያለመታመን፣ ከአገልጋይ የማይጠበቁ ባሕርያት ወይም በሌሎች ላይ የትችትን መንፈስ ማዳበር የመሳሰሉት ተፈጥሮአዊና ዳሩ ግን መንፈሳዊ ያልሆኑ ባሕርያት የሚወገዱበት መንገድ መፈለግ አለበት። ክትትልና ምዘና የግለሰቡን ክህሎቶችም ያሳድጋል። አገልጋዩ ግለሰቡ የአገልግሎት ክህሎቶቹን የሚያሳድግባቸውን መንገዶች ይፈልጋል። ለምሳሌ፣ ወጣቱ አገልጋይ ስብከቱን ካቀረበ በኋላ ከመሪው ጋር ስለ ስብከቱ በመነጋገር ይበልጥ መጽሐፍ ቅዱሳዊ፣ ተግባራዊ፣ ማራኪ፣ ወዘተ. . . ማድረግ ስለሚቻልባቸው መንገዶች ሊነጋገሩ ይችላሉ። ሰዎች ራሳቸውን አይተው እንዲያድጉ ልንረዳቸው የምንችለው በክትትልና ምዘና አማካኝነት ነው።

6) መሪው አዳዲስ አገልጋዮች ቦታ እንዲይዙ ሲያደርግ፣ ሌሎችም አማኞች መንፈሳዊ ስጦታዎቻቸውን ፈልገው ማውጣት ይጀምራሉ። መንፈስ ቅዱስ ይህንን በመጠቀም ግለሰቡ ለመሪነት ወይም ለአገልግሎት እንዲመረጥ ይመራል። ማንም ሰው ሰውን ለመሪነት ወይም ለአገልግሎት ከመምረጥ ይልቅ መንፈስ ቅዱስ ሰ ዎችን (ማለትም ሽማግሌዎችን ወይም ምእመናንን) እንደሚመራ መተማመን አለበት።

32ኛ ጥያቄ:- ልምድ ያላቸው የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችና መሪዎች ከላይ በተጠቀሰው መንገድ አዳዲስ መሪዎችንና አገልጋዮችን ቢያሠለጥኑ፣ በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ አገልግሎት እንዴት እንደሚለወጥ ግለጽ።



ረ. ማንም ሰው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ወሳኝ የአመራር ቦታ ወይም አገልግሎት ከማግኘቱ በፊት፣ የቤተ ክርስቲያን መሪ ዎች የሚከተሉትን ነገሮች ማረጋገጥ አለባቸው:-

1) እግዚአብሔር ግለሰቡን ለአገልግሎት ጠርቶታል? ወይስ ግለሰቡ አገልግሎቱን የተመለከተው እንደ ሥራ ወይም ራሱን እንደሚያሳድግበት መንገድ ነው? አንድ ሰው በእግዚአብሔር መጠራቱን የምናውቀው ያለ ደመወዝ ወይም የግል ጥቅም ለማገልገል ፈቃደኛ የሆነ እንደ ሆነ ነው። «ምን ያህል ደመወዝ ትከፍሉኛላችሁ?» ማለት ወይም ከሰዎች ክብርን የመፈለግ አዝማሚያዎች ካሉ፣ ጥሪው ያን ያህል ጠንካራ ላይሆን ይችላል። እውነተኛ ጥሪ ከሌለው ደግሞ፣ ግለሰቡ የአገልግሎት ሥልጣኑን ለራሱ በመጠቀም፣ ብዙ ጥቅሞችን በመፈለጉ ምክንያት ችግሮችን በመፍጠር ወይም ክብርን በመሻቱ ምክንያት ክፍፍልን ሊፈጥር ይችላል።

2) ግለሰቡ ለተሰጠው ኃላፊነት በቂ እውቀትና ክህሎቶች አሉት? አገልግሎቱ አገልጋዩን ማሳደግ አለበት። ነገር ግን ከአቅሙ ያለፈ አገልግሎት ብንሰጠው፣ አገልግሎቱን ላይወጣው ይችላል። ግለሰቡ ብቃት እንዳለው እርግጠኞች የምንሆነው ተመሳሳይ ሥራ ዎችን ሊያከናውን ከተመለከትን ብቻ ነው። ብዙ አብያተ ክርስቲያናት ችሎታ የሌላቸው ሰዎች ቦታ በመያዛቸው ለችግር ተ ጋልጠዋል። አንድ ሰው የተወሰነ ኃላፊነት ከያዘ በኋላ ብቁ ሆኖ ባይገኝ፣ በፍጥነት ከቦታው ማንሣቱ አስቸጋሪ ነው። እናሳዝነዋለን በሚል ፍርሃት ከመጋፈጥና ከአገልግሎቱ ከማንሣት እንቆጠባለን። ይህ ማለት ግን ቤተ ክርስቲያኒቱ ብቃት በሌለው ሰው በመመራት ለጉዳት ትጋለጣለች ማለት ነው። አንድን ሰው በፍጥነት ከአገልግሎት ስፍራ ላይ ካስቀመጡ በኋላ ተመልሶ ከመጸጸት ይልቅ፣ መጀመሪያ ችሎታውን በተመሳሳይ አገልግሎቶች ማ ረጋገጡ ብልህነት ነው።

3) ግለሰቡ ቀጣይነት ያለው መንፈሳዊ ባሕርይና መንፈሳዊ ብስለት አሳይቶአል? ወይስ አገልግሎቱን ሊያደናቅፉ የሚችሉ የባሕርይ ችግሮች አሉ? በርግጥ፣ ማንም ሰው ፍጹም

አይደለም፣ ነገር ግን የመንፈሳዊ ብስለትና የአገልግሎት ባሕርይ ደረጃው ግለሰቡን ካጨንበት የአገልግሎት ደረጃ ዝቅ ካለ፣ ግለሰቡን ለዚያ አገልግሎት መምረጡ ተገቢ አይሆንም:: እንደ ተመለከትነው፣ የቤተ ክርስቲያን አመራር የተመሠረተው በመሪነት ክህሎቶች ላይ ሳይሆን፣ በመንፈሳዊ ባሕርይና ብስለት ላይ ነው:: መንፈሳዊ ብስለት የሌለውን ሰው ብንመርጥ ዞሮ ዞሮ ቤተ ክርስቲያኒቱን መጉዳቱ ስለማይቀር በምርጫችን መጸጸታችን አሙን ነው::

4) ግለሰቡ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለመሥራት የፈለገው ለምንድን ነው? ልባዊ ፍላጎቱ ምንድን ነው? ለማገልገል የፈለገው ለምንድን ነው? እግዚአብሔርን ስለ ማገልገል የግል ራእዩ ምንድን ነው? የእርሱ ራእይ እኛ ከምንፈልገው በላይ ከሆነ፣ ቤተ ክርስቲያኒቱን ወደምንፈልገው ስፍራ አያደርስልንም ማለት ነው:: ወጣቶችን የሚወድና እግዚአብሔር በዚያ በኩል እንዲጠቀምበት የሚፈልግ ከሆነ፣ ለአስተዳደራዊ ሥራዎች ብቁ ላይሆን ይችላል::

5) ግለሰቡ ከእግዚአብሔር ጋር ያለው ግንኙነት ምን ዓይነት ነው? ከሚስቱና ከልጆቹ ጋር ያለውስ ግንኙነት? ከሌሎች መሪዎች ጋር ያለው ግንኙነትስ? አብረውት ከሚሠሩት ሰዎች ጋርስ? ከምእመናን ጋርስ? የማያምኑ የማኅበረሰቡ አባላት እንዴት ነው የሚመለከቱት? አመራር ከእግዚአብሔርና ከሌሎች ጋር ያለንን ግንኙነት የሚመለከት ጉዳይ ነው:: የአመራርን ኃይልና ምሪት የምናገኘው ከእግዚአብሔር ነው:: ሌሎችን በአረኝነት የምናገለግለው ከእነርሱ ጋር መልካም ግንኙነት ካለን ብቻ ነው::

| |
|---|
| 33ኛ ጥያቄ:- አንድ ሰው የቤተ ክርስቲያን መሪ እንዲሆን በሚጠየቅበት ጊዜ እነዚህን መረጃዎች ማወቅ አስፈላጊ የሚሆነው ለምንድን ነው? |

ለ. የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አገልግሎታቸውን ለማሳደግ ሰዎችን መምረጥ አለባቸው:: የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሊጠቀሙባቸው የሚገቧቸው ሁለት ዓይነት ሥልጠናዎች አሉ:-

<u>አንደኛ</u>፣ አንድን የክህሎት ዓይነት ለማሳደግ የሚሰጥ የአጭር ጊዜ ሥልጠና አለ:: ለምሳሌ፣ አንድ ሰው እምነቱን ለአንድ



የሃይማኖት ቡድን ለማካፈል ቢፈልግ፣ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች በዚህ በኩል እገዛ ወደሚያገኝበት የአጭር ጊዜ ሥልጠና ሊልኩት ይችላሉ:: ወይም ደግሞ ግለሰቡ ስለ አስተዳደር የሚማር ከሆነ፣ የአጭር ጊዜ የአስተዳደር/የአመራር ሥልጠና እንዲያገኝ ማድረጉ ቤተ ክርስቲያንን በበለጠ እንዲያገለግል ሊረዳው ይችላል::

<u>ሁለተኛ</u>፣ ጥቂት ሰዎች ለሙሉ ጊዜ ሥልጠና ሊሳተፉባቸው የሚገቡ መደበኛ ሥልጠናዎች አሉ:: የሙሉ ጊዜ ወንጌላውያንና እረኞች *«በአገልግሎት ዘርፋቸው»* መደበኛ ሥልጠና ቢያገኙ መልካም ነው:: ቤተ ክርስቲያን፣ «ወንጌላዊ ስለምንፈልግ እገሌ ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት ገብቶ መሠልጠን አለበት» ማለት ትክክል አይደለም:: ግለሰቡ ለወንጌል አገልግሎት ፍላጎትም ሆነ ስጦታ ሳይኖረው እንዲህ ዓይነት እርምጃ መውሰዱ ጥሩ አይሆንም:: ሥልጠና ያለንን መንፈሳዊ ስጦታ ያሳድጋል እንጂ፣ የሌለንን ስጦታ አያስገኝልንም:: የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከሚያሠለጥኗቸው ወጣቶች መካከል ስጦታ ያላቸውን ወጣቶች መልምለው ማሠልጠን ይኖርባቸዋል:: የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ይህንን የሚያደርጉት፣ ወጣቶቹ ሥልጠናቸውን ጨርሰው ወደ ቤተ ክርስቲያናቸው በመመለስ አገልግሎት ይሰጣሉ በሚል እምነት ነው:: ወጣቶች የፈለጉትን ዓይነት ሥልጠና እንዲመርጡ ወይም አጠቃላይ ሥልጠናዎች እንዲሰጧቸው ከማድረግ ይልቅ፣ ከወጣቶቹ ጋር በመወያየት መንፈሳዊ ስጦታቸውን የሚያሳድጉና የቤተ ክርስቲያኒቱን ችግሮች የሚቀርፉ ሥልጠናዎችን እንዲያገኙ ቢያደርጉ መልካም ነው:: ቤተ ክርስቲያን በገንዘብ መደገፍ ያለባት ለአገልግሎት ዕቅዷ አስፈላጊ የሆኑትን ብቻ ሊሆን ይገባል:: ድጋፍ መስጠት ያለባት ለቤተ ክርስቲያኒቱ አገልግሎት አስፈላጊ የሆነውን የሥልጠና ደረጃ እስኪያሟሉ ድረስ ብቻ መሆን አለበት:: ግለሰቡ የቤተ ክርስቲያኒቱን የአገልግሎት ፍላጎት ለማሟላት ዲፕሎማ ማግኘት የሚበቃው ከሆነ፣ ለዲግሪ ትምህርት ድጋፍ ማድረጉ አስፈላጊ አይሆንም:: ትምህርት ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች ልጆች ወይም ለተወሰኑ ዓመታት ላገለገሉ ሰዎች የሚሰጥ «ሽልማት» መሆን የለበትም:: ነገር ግን ትምህርት አንድ ሰው

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በተወሰነ አገልግሎት ላይ እንዲሰማራ የሚያስችል መሣሪያ ነው፡፡

ሸ. ግለሰቡ በሚመረቅበት ጊዜ፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ብቃት ባላየበት ዘርፍ እንዲያገለግል ማድረግ አለባቸው፡፡ በመጋቢነት ስለ ሠለጠነ ዋና መጋቢ መሆን አለበት ብለው ማሰብ የለባቸውም፡፡ የተመረቀው አገልጋይ ልምድም ማግኘት አለበት፡፡ ስለሆነም በአገልግሎት ልምድ ወደሚያገኝበት ደረጃ ሊመሩት ይገባል፡፡ ለምሳሌ፣ በተወሰነ የቤተ ክርስቲያኒቱ ክፍል የመጋቢነትን አገልግሎት እንዲሰጥ ሊመድቡት ይችላሉ፡፡ የተሰጠውን ኃላፊነት በብቃት ሲወጣ፣ የቤተ ክርስቲያኒቱ እረኛ የመሆን ኃላፊነት ሊሰጠው ይችላል፡፡ እግዚአብሔር መሪዎችን ወደ ከፍተኛ ደረጃ ለማድረስ በዝቅተኛ ደረጃ ብቃታቸውን እንዲያሳዩ ያደርጋል፡፡ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችም ይህንን የእግዚአብሔርን አሠራር መከተል አለባቸው፡፡

ቀ. የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ለአገልግሎቶች ተጠያቂ መሆን አለባቸው፡፡ መሪዎች የአገልጋዮችን ብቃት ለማሳደግ መጣር ይኖርባቸዋል፡፡ በመሆኑም፣ በየጊዜው አገልግሎቶችን መከታተልና መመዘን አለባቸው፡፡ ግምገማና ክትትል መካሄድ ያለበት አገልጋዮችን ለመቅጣት መሆን የለበትም፡፡ ነገር ግን የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አገልጋዮችን ለማሳደግ የሚረዱበት መንገድ ነው፡፡ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አገልጋዮች የመጋቢነት እንክብካቤ ያቸውን ወይም ስብከታቸውን ወይም የጊዜ አጠቃቀማቸውን፣ ወዘተ. . . የሚያሻሽሉበትን መንገድ ማሳየት ይኖርባቸዋል፡፡ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አገልጋዩ በችሎታው እንዲያድግ ለማገዝ የሚችሉትን ሁሉ ጥረት ከማድረጋቸው በፊት፣ ማንኛውም አገልጋይ ከአገልግሎቱ መነሣት የለበትም፡፡

34ኛ ጥያቄ፡- ሀ) የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ብትሆን፣ የቤተ ክርስቲያን የመሪዎች ክትትልና ምዘና ጠቃሚ የሚሆነው ለምን ይመስልሃል? ለ) ብዙ አገልጋዮች ክትትልና ምዘናን (ግምገማን) የሚፈሩት ለምንድን ነው? ሐ) ለቤተ ክርስቲያናችሁ አገልግሎቶች ምን ዓይነት የክትትልና ምዘና ሂደት ቢኖር ጥሩ ይመስልሃል?



## የአገልግሎት ኃላፊነቶችን ማስተላለፍ

እግዚአብሔር ለአንድ ሰው የአገልግሎት ኃላፊነት (የሰፈር ፕሮግራም መሪ፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ዳይሬክተር) በሚሰጥበት ጊዜ፣ አገልግሎቱን የሚረከብ ሰው ከማዘጋጀቱ በፊት ለግል ግቦቹ በማሰብ አገልግሎቱን መልቀቅ የለበትም፡፡ እግዚአብሔ ር ለሰጠን ኃላፊነት ታማኞች መሆን ካለብን፣ የግል ጉዳዮቻችንን ለእግዚአብሔር ስንል እንሠዋለን፡፡ አንዳንድ ወንጌላውያን፣ መጋቢያን ወይም አስተማሪዎች እግዚአብሔር ለሰጣቸው ኃላፊነት ብዙም የኃላፊነት ስሜት ስለማይሰማቸው፣ የተሻለ የሥራ ወይም የትምህርት ዕድል ካገኙ፣ ወዲያውኑ የነበራቸውን ኃላፊነት ጥለው ይሄዳሉ፡፡ አገልግሎታቸውን የሚረከብ ሰው ሳያዘጋጁ አብያተ ክርስቲያናትን፣ አንድን አካባቢ ወይም የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶችን ጥለው ይሄዳሉ፡፡ ይህ ብዙውን ጊዜ ሥራውንና ቀደም ሲል ለእግዚአብሔር የሰጡትን አገልግሎት ከንቱ የሚያደርግ ድርጊት ነው፡፡ የእግዚአብሔርን መንግሥት ለማስፋቱ ተግባር ቅድሚያ የሚሰጥ ማንኛውም አገልጋይ፣ በገዛ ፈቃዱ ተተኪ ሳያዘጋጅ አገልግሎቱን ሊተው አይችልም፡፡ ተተኪ ሰው እንደሌለ እያወቁ አጣዳፊ ችግር ሳይኖር አገልግሎትን መልቀቅ የምናገለግለው ለተሳሳተ ዓላማ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ ይህ በአገልግሎታችን ታማኞች አለመሆናችንን ያሳያል፡፡ ከእግዚአብሔር ጥሪ ይልቅ በግል የሥራ ግቦቻችን ላይ እናተኩራለን ማለት ነው፡፡

35ኛ ጥያቄ፡- ሀ) አንድ ሰው ተተኪ ሳያዘጋጅ አገልግሎቱን የለቀቀበትን ሁኔታ ግለጽ፡፡ ለ) ይህ አገልግሎቱን እንዴት እንደ ጎዳ አብራራ፡፡ ሐ) ይህ አገልግሎቱን ለለ ለቀቀው ግለሰብ ባሕርይና ጥሪ ምን ያሳያል?

አንዳንድ ጊዜ የአገልግሎት ጊዜያችን እያበቃ መሆኑን ሳናውቅ ብንችልም፣ ብዙውን ጊዜ ግን እግዚአብሔር አንደኛውን የአገልግሎት በር እየዘጋ ሌላ እየከፈተልን መሆኑን እናውቃለን፡፡ በድንገት ብንታመም፣ በቤተሰባችን ላይ ከፍተኛ ችግር በመፈጠሩ ምክንያት በአገልግሎት ለመቀጠል ባንችል፣ ወይም ብንሞት እግዚአብሔር የሰጠንን አገልግሎት በድንገት መልቀቃችን የማይቀር ነው፡፡ ሌሎች የተሻለ ሥራና የትምህርት ዕድል

የመላሰሉት ግን አገልግሎታችንን በድንገት እንድንለቅ ሊያደርጉን አይገባም:: ይህ ዕድል ካመለጠኝ መልሼ አላገኘውም በሚል ፍርሃት የያዝነውን አገልግሎት ለቅቀን ብንሄድ፣ ይህ የአገልግሎት በራችንን ማስፋት የእግዚአብሔር ሳይሆን የእኛ ሥራ ነው የሚል አቋም ይዘናል ማለት ነው:: እግዚአብሔር በሚፈልግበት ጊዜ ሌላ የአገልግሎት ወይም የትምህርት ዕድል እንደሚሰጠን ካመንን ግን፣ እንዲህ ዓይነት እርምጃ እንወስድም:: ሌላ አጋጣሚ ሳንጠብቅ በፍጥነት ለቅቀን እንድንሄድ የሚያደርጉን ዕድሎች ብዙ አይደሉም:: ትምህርታችንን በሚቀጥለው ዓመት የማንጀምርበት ምክንያት ላይኖር ይችላል:: የሚተካንን ሰው እያዘጋጀን፣ ሌላ አገልግሎት ልንፈልግ እንችላለን::

አገልግሎታችንን ለሌላ ሰው ለማስተላለፍ በምንዘጋጅትበት ጊዜ ልናስታውሳቸው የሚገቡ አንዳንድ ነጥቦች ከዚህ በታች ተመልክተዋል:-

1. ሁልጊዜም ሕይወት አጭርና እርግጠኛ የማንሆንባት መሆኗን ማስታወስ አለብን (1ኛ ጴጥ. 1:24-25፤ ያዕ. 4:13-15):: ስለዚህ፣ በድንገት መልቀቅ ካለብን፣ የሚተካን ሰው እንዲኖር ማዘጋጀት አለብን::

ሁልጊዜም እግዚአብሔር የሰጠንን አገልግሎት ልክ እንደ «ጢሞቴዎስ» የሚረከበን ሰው መኖር አለበት:: (ጢሞቴዎስ የጳውሎስን አገልግሎት እንደ ተረከበው ማለት ነው::) አስተዋይ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሥራቸውን ከማከናወኑ በተጨማሪ ተተኪዎችንም ያሠለጥናሉ:: ይህ ደግሞ እግዚአብሔር እንዲለቁ ቢያደርግ የሚተካቸውን ሰው እንዲያዘጋጁ ያስችላቸዋል:: ይህ ማለት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ተተኪዎቻቸውን በአብዛኞቹ ውሳኔዎች ላይ ማሳተፍ አለባቸው ማለት ነው:: የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ኃላፊዎች የሙሉ ጊዜ ወይም የትርፍ ጊዜ አስተማሪዎችን በውሳኔ-ሰጭነቱ ላይ በማሳተፍ፣ መልቀቅ ቢያስፈልጋቸው ራሳቸው ውሳኔ እንዲሰጡ ማስቻል አለባቸው:: አንድ ወንጌላዊ ወደ ሌላ ቦታ ቢሄድ ይተካው ዘንድ የአካባቢውን ሰው ማሠልጠን አለበት::



2. እግዚአብሔር ወደ ሌላ አገልግሎት ወይም ትምህርት እየመራን እንደ ሆነ በምናስብበት ጊዜ፣ ከመሄዳችን በፊት ከቤተ ክርስቲያን መሪዎች ጋር መነጋገር አለብን::

ተጨማሪ ትምህርትን በመላሰሉት አንዳንድ ጉዳዮች ላይ፣ የመልቀቂያ ጊዜያችን መቼ እንደሚሆን ልንደራደር እንችላለን:: ሐምሌ ላይ ደርሰን መስከረም ላይ ትምህርት ቤት እገባለሁ ከማለት ይልቅ፣ ገና ከአንድ ዓመት ቀደም ብለን የመማር ፍላጎት እንዳለን ብንናገር የተሻለ ነው:: ይህ ሁለት ነገሮችን ያከናውናል:

እንደኛ፣ ቤተ ክርስቲያኒቱ ሌላ ሰው በማግኘት አሠልጥነህ አገልግሎትህን እንድታስረክብ ለማድረግ በቂ ጊዜ ይኖራታል::

ሁለተኛ፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ያንተን ስጦታና የወደፊት የትምህርት ፍላጎትህን እንዲያጤኑ ዕድል ይሰጣቸዋል:: ከዚያም መማርህን መደገፍ አለመደገፋቸውን ሊነግሩህ ይችላሉ:: በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ ላለህ አገልግሎት ተጨማሪ ትምህርት የሚያስፈልግህ አይመስለንም ካሉህ፣ አንድም የእነርሱን አሳብ መቀበል፣ አለዚያም አገልግሎቱን ለቅቀህ ለቀጣይ ሕይወትህ በእግዚአብሔር ላይ መደገፍ አለብህ ማለት ነው:: ትልቁ ነገር በምርጫህ እግዚአብሔርን መተማመንህና መታዘዝህ ነው:: ለቤተ ክርስቲያን መሪዎቹ አሳብ ራስህን በማስገዛት እግዚአብሔር ተጨማሪ ትምህርት እንደሚያስፈልግህ በራሱ ጊዜ እንዲያስገነዝባቸው ልትታመን ትችላለህ:: ወይም ደግሞ እግዚአብሔር ለትምህርት ቤት ወጪና ለአዳዲስ የአገልግሎት በሮች ከጎንህ እንደሚቆም ተማምነህ፣ ያለህን አገልግሎት ልትለቅ ትችላለህ:: የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ፍላጎትህን ስላልደገፉ ቂም ልትይዝባቸው አይገባም:: በእግዚአብሔር ፊት ተጠያቂ የሚሆኑት ያንተን የተጨማሪ ትምህርት ፍላጎት በማሟላታቸው ሳይሆን፣ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ምርጥ ውሳኔ በመስጠታቸው ነው:: ከተመረቅክ በኋላም ቤተ ክርስቲያን እንድትቀጥርህ ጫና ማሳደር የለብህም:: ለእነርሱ አሳብ ካልተገዛህ፣ ምርጫው የራስህ ነው:: እነርሱ ሳይፈልጉ ወደ ትምህርት ቤት ከገባህ በኋላ፣ ስትጨርስ ቅጠሩኝ ማለት የማይመስል ነገር ነው::

ከመሄዳችን በፊት የሚተካንን ሰው ለማሠልጠን እንድንችል ቀደም ብለን መናገር አለብን። የምንለቅቀው መሪዎች አዲስ አገልግሎት እንድንጀምር በመጠየቃቸው ምክንያት ከሆነ ደግሞ፣ ከእነርሱ ጋር በመደራደር የበፊት ኃላፊነቶቻችንን ለማረካከብ በቂ ጊዜ እንዲሰጡን መጠየቅ አለብን። ለምሳሌ፣ አንድ ወንጌላዊ ወደ ሌላ ቦታ ሄዶ እንዲያገለግል እናት ቤተ ክርስቲያኑ ታዝዘዋለች። በዚህ ጊዜ በፍጥነት ከመሄድ ይልቅ የተወሰነ ጊዜ ቆይቶ የሚተካውን ሰው እንዲያሠለጥን እንዲፈቅዱለት መጠየቅ ይኖርበታል። ይህ እንደ ሁኔታው ስድስት፣ አንድ ዓመት ወይም ሁለት ወራት የሚፈልግ ተግባር ሊሆን ይችላል። ከልባችን ሥራውን ወደ ቀጣዩ አገልጋይ ለማስተላለፍ የምንሞክር ከሆነ፣ አብዛኞቹ መሪዎች ይረዱናል።

የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የሚተካንን ሰው እንዲያገኙ በተቻለ መጠን ቀደም ብሎ ማሳወቁ የእኛ ኃላፊነት ነው። ነገር ግን መሪዎች ተተኪ አገልጋይ ለማግኘት ጥረት ባያደርጉ፣ ከሄድክ በኋላ ለሚፈጠረው ችግር ተጠያቂ አትሆንም። መሪዎቹ ለማቀድና ውሳኔ ለመስጠት አለመቻላቸው፣ ለዘላለም እዚያው መቆየት አለብህ ማለት አይሆንም።

አገልጋዩ ከመሪነት ቦታው የተመረጠ ወይም በመሪዎች የተተካ ቢሆን እንኳን፣ ኃላፊነቱን ለሌሎች ማስተላለፉ መንፈሳዊ ብስለቱንና በእግዚአብሔር ላይ መታመኑን ሊያሳይ ይችላል።

| |
|---|
| 36ኛ ጥያቄ፦ አገልግሎትን ለሌሎች ለማስተላለፍ ልባዊ ጥረት ማድረግ ከራሳችን ጥቅም ይልቅ የእግዚአብሔርን መንግሥት እንደምንሻ የሚያሳየው እንዴት ነው? |

3. የሚለቅቀው አገልጋይ ከመሄዱ በፊት አዲሱን አገልጋይ በማላመድ በቂ ጊዜ ማሳለፍ አለበት። ይህ በተለይ አገልጋዩ ለአካባቢውና ለሚረከበው አገልግሎት አዲስ ከሆነ ወሳኝ ነገር ነው።

ሀ. አዲሱ አገልጋይ አገልግሎቱን ይዞ እንዲቀጥል ለማድረግ የሚያስችሉትን ክህሎቶች መስጠት አለባቸው። ይህ የአጭር ጊዜ ሥልጠና መስጠትንም ሊጨምር ይችላል። (ለምሳሌ፣ አንድ ሰው



ወንጌል ወዳልደረሰበት ቦታ ሄዶ እንዲያገለግል ከተመደበና ለዚያ አካባቢ ወንጌልን መስበክ ስለሚቻልበት ሁኔታ ባያውቅ፣ ለአካባቢው ሕዝብ ወንጌል መስበክ ስለሚችልበት ሁኔታ ሥልጠና እንዲያገኝ መደረግ አለበት።)

ለ. የሚለቅቀው አገልጋይ ለአዲሱ አገልጋይ ዋና ዋና ጉዳዮችንና ኃላፊነቶችን ማሳወቅ አለበት። አዲሱ አገልጋይ ማስታረቅ ያሰባቸው የተጣሉ አባላት እሱ? ወንጌላዊ መመደብ የሚያስፈልግበት ቦታ አለ? የሚለቅቀው አገልጋይ እነዚህንና ሌሎችንም አስፈላጊ ውሳኔዎች ለአዲሱ አገልጋይ ማሳወቅ አለበት።

ሐ. ቀደም ሲል የተወሰኑትን አስፈላጊ ውሳኔዎች መከለስ። አዲሱ መሪ ውሳኔዎቹን ብቻ ሳይሆን፣ ውሳኔዎቹ የተሰጡበትን ምክንያት ጭምር ማወቅ አለበት። አዲሱ አገልጋይ እነዚህን ውሳኔዎች የሚጻረር ዕቅድ ማውጣት የለበትም። ቤተ ክርስቲያኒቱ ያከናወነቻቸው ቀደምት ስምምነቶች መታወቅና መከበር አለባቸው።

መ. የቀድሞው የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ገንዘብ-ነክ ጉዳዮችን በጥንቃቄ ማብራራት ይገባዋል። በገንዘብ- ነክ ጉዳዮች ላይ በግልጽ ውይይት መደረግ ይኖርበታል፣ የሂሳብ መዝገቦችንም አብረው ማየት ይኖርባቸዋል፣ ከዚያም ሁሉም ገንዘብ ለአዲሱ ሰው መስጠት አለበት።

ሠ. ከቤተ ክርስቲያኒቱ ጋር የሥራ ግንኙነት ያላቸው ሰዎች ከአዲሱ ሰው ጋር እንዲተዋወቁ መደረግ ይኖርበታል። የቀበሌው ሊቀመንበር፣ በከተማው ውስጥ ያለችው የሌላዪቱ ቤተ ክርስቲያን መጋቢ፣ የአብያተ ክርስቲያናት ኅብረት መሪው፣ የቤተ ክርስቲያኒቱን ውሳኔዎች ታሪክ የሚያውቀው ግለሰብ፣ እና የመሳሰሉት ሁሉ አዲሱን ሰው እንዲተዋወቁ መደረጉ እርሱ ችግር በሚያጋጥመው ጊዜ ለእርዳታ እና ድጋፍ ወደ ማን መሄድ እንዳለበት እንዲያውቅ ያስችለዋል።

4. የቀድሞው የቤተ ክርስቲያን መሪ አዲሱ ሰው እንዲሳካለት በታማኝነት ለመርዳት መሞከር ይገባዋል። እግዚአብሔር እርሱን ተጠቅሞ ያከናወነው አገልግሎት ማደጉንና ፍሬ ማፍራቱን

እንቅፋት የሚፈጥሩ ባህላዊ አስተሳሰቦችን ለመዋጋት ምን ዓይነት አሳቦችን ታቀርባለህ?

4. ሀ) እግዚአብሔር አንድን ሰው ለመሪነት ሲያዘጋጀው ያየህበትን ሁኔታ ግለጽ:: ለ) አንድ ግለሰብ በእግዚአብሔር ፈቃድ ለሚሆኑ ሁኔታዎች የሚሰጣቸው ምላሾች እግዚአብሔርን በሚገባ የሚያገለግልባቸውን መንገዶ እንዴት እንደሚወሰኑበት ግለጽ:: ሐ) ስጦታ ያላቸው ወጣቶች እግዚአብሔርን የሚፈሩ ውጤታማ መሪ ዎች እና የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች እንዲሆኑ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በበለጠ አብረዋቸው በሚሠሩባቸው መንገዶች ላይ ተ ወያዩ::

5. ሀ) በዚህ ትምህርት ውስጥ ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች ያስፈልጋል በሚል መረዳት የቀረበውን መደበኛ ትምህርት ብዙ መሪዎች ስለ መደበኛ የሥነ መለኮት ትምህርት ካላቸው የተለመደ አስተሳሰብ ጋር በማነጻጸር ተወያዩበት:: የምትስማማበትን እና የማትስማማበትን ነገር አብራራ:: ለምን እንደምትስማማ እና እንደማትስማማ አብራራ:: ለ) መደበኛ የሥነ መለኮት ትምህርት የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች እግዚአብሔርን በተሻለ ሁኔታ ማገልገል የሚችሉበትን ጥሩ መሣሪያ ሲሰጣቸው ያየህበትን ሁኔታ ግለጽ:: ሐ) መደበኛ የሥነ መለኮት ትምህርት ትልቅ ፈተና ሆኖበት የቤተ ክርስቲያን አገልጋይን ባሕርይ እና የአገልጋይነት መንፈስ ሲሰውጥ እንዴት እንዳየህ ግለጽ:: መ) በሥነ መለኮት ት/ቤቶች የሚማሩ ሰዎች ወደ ትዕቢት እና የግል ፍላጎቶችን ለማሟላት ወደ መፈለግ የሚመራውን ፈተና መቋቋም እንዲችሉ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ማድረግ የሚችሏቸው ነገሮች ምንድን ናቸው?



# ትምህርት አሥራ ዘጠኝ

## ክፍል ሦስት

### አንደኛ ቀን

በቤተ ክርስቲያን አመራር ጥናታችን፣ የውጤታማና መንፈሳዊ አገልጋይን ሁለት ዐበይት ክፍሎችን መርምረናል:: በክፍል አንድ፣ የመንፈሳዊ መሪን ባሕርያትና ብዙውን ጊዜ የቤተ ክርስቲያን መሪ ውን በማጥመድ ስሙን የሚያጎድፉትን ኃጢአቶች አጥንተናል:: ይህ የመንፈሳዊ አመራር ወሳኝ ክፍል መሆኑን ገልጸናል:: እግዚአብሔርን ከሁሉም በላይ የሚያሳስበው ባሕርያችን ነው:: እግዚአብሔር የሚጠቀምባቸው እጅግ ውጤታማ መሪዎች መንፈሳዊ ባሕርይ ያላቸው ናቸው:: በክፍል ሁለት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በሥራቸው ውጤታማ ለመሆን ሊማሯቸው የሚገባቸውን አሥራ ሁለት ክህሎቶች ተመልክተናል:: እነዚህን ክህሎቶች በመማር፣ እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያኑ አገልግሎት የሚጠቀምብን ስለታም መሣሪያ እንሆናለን::

በዚህ የመጨረሻ ክፍል ከቤተ ክርስቲያን አመራር ጋር የተ ያያዙትን የተለያዩ እውነታዎች እንመለከታለን:: ቤተ ክርስቲያን ከዓለማዊ ድርጅቶች የተለየች መሆኗንና ይህም በአመራር ላይ እንዴት ተጽዕኖ እንደሚያሳድር እናጠናለን:: ከቤተ ክርስቲያን ታሪ ክም ስለ አመራርና አስተዳደር መዋቅሮች አንዳንድ ትምህርቶችን ለመውሰድ እንሞክራለን:: በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መጋቢዎች፣ ሽማግሌዎች፣ ዲያቆናትና ወንጌላውያን ምን ምን ዓይነት አገልግሎቶችን ማካሄድ እንዳለባቸው እንመለከታለን:: እንዲሁም መደበኛ የሥነ-መለኮት ትምህርት ሥልጠና ለቤተ ክርስቲያን መሪ ዎች ስለሚያበረክተው አስተዋጽኦ እና ስለ ሴቶች አገልግሎት አንዳንድ መርሖዎችን እናያለን::

(ማስታወሻ:- በዚህ ክፍል ውስጥ የምንመለከተው መሪዎች በአሳብ የሚለያዩባቸውን ትምህርቶች ነው:: በክፍሉ ውስጥ የተጸንባረቀው የደራሲው አመለካከት ነው:: የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እነዚህን